# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 84ኛ ዓመት ቁጥር 075 ኅዳር 15 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “የሀገሪቱን ዕምቅ የማዕድን ሀብት መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይገባል”

- ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ የማዕድን ሀብት በዘመናዊ መንገድ አልምቶ መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ገለጹ።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ 3ኛውን ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ 2024 ትናንት በሚሊኒየም አዳራሽ መርቀው ከፍተዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የማዕድን ሀብት በዘመናዊ መንገድ አውጥቶ መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይገባል።

ሀገሪቱ ያሏትን የማዕድን ሀብት ለመለየት፣ ለማልማትና ለመጠቀም ዘመናዊ ሥርዓትን መከተል እና ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም እንደሚገባ አመልክተው፤ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችም የእውቀት ሽግግር ለማድረግ የሚያስችላቸውን ቴክኖሎጂዎች በስፋት መጠቀም እንዳለባቸው ገልጸዋል።

የማዕድን ሀብት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት እና የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ ወሳኝ እንደሆነ ገልጸው፤ የማዕድን ዘርፉን ለማልማት ከመንግሥት በተጨማሪ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት እገዛ ሊያደርጉ እንደሚገባም ተናግረዋል።

መንግሥት የማዕድን ዘርፉን ለማሳደግ ከአምስቱ ቁልፍ የልማት ምሰሶዎች ውስጥ በማካተት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ

“የሀገሪቱን ዕምቅ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል









# ልዩ የምርመራ ዘገባ

**በሃገራችን ገና በጅምሩ በብዙ ውስብስብ ችግሮች እየተፈተነ ለዜጎች የእሮሮ ምንጭ በሆነው የሪልስቴት ንግድ ዙሪያ ያዘጋጀነውን ልዩ የምርመራ ዘገባ በገጽ 8 ይመልከቱ**

# የጥራት መንደሩ የኢትዮጵያ የማንሠራራት ዘመን ጅማሮ ተደርጎ የሚወሰድ ነው

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ብሔራዊ የጥራት መንደርን መርቀው ከፈቱ

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ የጥራት መንደር የኢትዮጵያ ማንሠራራት ዘመን ጅማሬ ተደርጎ የሚወሰድ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ብሔራዊ የጥራት መንደርን ትናንት መርቀው ከፍተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጥራት መንደር ምረቃ መርሐ ግብር ላይ እንደገለፁት፣ በግብርና፣ በጤና፣ በግንባታና በሌሎች ዘርፍ ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት ለማቅረብ የጥራት መንደሩ ወሳኝ ነው። ይህም መንደሩ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ጥራት በማረጋገጥ በምርት ጥራት ጉድለት የሚያጋጥሙ ጉዳቶችን ያስወግዳል፣ ለዜጎችም ጥራቱ የተረጋገጠ ምርትና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል ብለዋል።

የጥራት መሠረተ ልማት የሌላቸው ሀገራት ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ያዳግታቸዋል ያሉት



ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ምርትና አገልግሎት ለማቅረብ ጥራትን ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባር መሆኑን ገልጸዋል።

የጥራት መንደሩ የኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 5

# ጥንቃቄን የሚሻው የስኳር ህመም

**ነፃነት አለሙ**

**ዜና ሀተታ**

በኢትዮጵያ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች የስኳር ህመም እንዳለባቸው በዓለም አቀፉ የስኳር ፌደሬሽን የተደረገ ጥናት ያሳያል። ከጠቅላላው ሕዝብ 3 ነጥብ 3 ሚሊዮን የሚሆነው ለህመሙ ተጋላጭ መሆኑን የሚያሳየው ጥናቱ፤ በኢትዮጵያ በህመሙ ከሚጠቁት ስልሳ ሰባት በመቶዎቹ ህመሙ እንዳለባቸው እንደማያውቁ ይገልፃል። ለዚህም ምክንያቱ ህመሙ ቅድሚያ ምልክት የማያሳይ በመሆኑ እንደሆነ በጥናቱ ተጠቁሟል።

የስኳር ህመም ታማሚ የሆነችው ፅጌ በቀለ

ጥንቃቄን ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ዜና



በለጠ ሞላ (ዶ/ር)

# ለስታርት አፕ ምቹ ምህዳር ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ለስታርት አፕ ምቹ ምህዳር ለመፍጠር በፖሊሲ የመደገፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ለስታርት አፕ እድገት ተቋማዊና ሕጋዊ አሠራርን የሚዘረጋ ረቂቅ አዋጅ ለሕዝብ ውይይት ቀርቦ ትናንት ምክክር ተደርጎበታል። በምክክሩ ወቅት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የስታርት አፕ እድገትን የሚያሳልጥ ምቹ ምህዳር ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ ነው። ወደፊት ትልቅ ኢኮኖሚ ምንጭ እንደሚሆን በመገመት ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ስታርት አፕ ለብዙዎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥርና በኢኮኖሚ ዕድገቱ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ በፖሊሲ የመደገፍ ሥራ እየተሠራ ነው። ረቂቅ አዋጁ ለስታርት አፕ ተቋማዊና ሕጋዊ ድጋፍን በመስጠት በኢትዮጵያ የዘርፉን እድገትን ያጠናክራል።

ረቂቅ አዋጁ በስታርት አፕ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታትና የፋይናንስ አቅርቦትን ማመቻቸት ሌላው ዓላማው ነው። ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት የምታከናውነውን ተግባርና የምትከተለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በቴክኖሎጂና በፈጠራ ለመደገፍ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወነች እንደምትገኝ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ከሦስት ዓመት በፊት ያልዳበረ የባንክ ሥርዓትን ጨምሮ የስታርት አፕ ፍላጎት ለማሟላት ምቹ ሁኔታ አልነበራትም። አሁን ላይ ፖሊሲዎችን ከማሻሻል ጀምሮ ለስታርት አፕ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ እውን ለማድረግ፣ ዘላቂና አስተማማኝ ኢኮኖሚ ለመገንባት ስታርት አፕን በፖሊሲ መደገፍ የግድ መሆኑን አንስተዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለግሉ ዘርፍ በሰጠው ትኩረት በርካታ ሥራ ፈጣሪዎች ኢኮኖሚውን እየተቀላቀሉ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የስታርት አፕ አዋጁ ሲጸድቅ ለሥራ ፈጣሪዎች ትልቅ እድል ይዞ ይመጣል። መንግሥት ለስታርት አፕ በሰጠው ልዩ ትኩረት በርካታ ሥራ ፈጣሪዎች እየተፈጠሩ በመሆኑ አሠራር ለመዘርጋት ረቂቅ አዋጁን ማዘጋጀት አስፈልጓል ብለዋል።

አዋጁ ሲጸድቅ በዘርፉ ያሉ ውስብስብ ችግሮችን በመፍታት አዳዲስ ፈጠራን ለማሳደግ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

ላለፉት ሦስት ዓመታት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ረቂቅ አዋጁ ወሳኝ ደረጃ ላይ ደርሷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቂ ውይይት ተደርጎበታል። ለስታርት አፕ ምቹ ያልሆኑ መሰናክሎችን በማስወገድ ፈጠራንና ደፋር ሃሳቦችን በማጎልበት ዘርፉን የሚያበረታታ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር መላኩ አለበል በበኩላቸው፤ ስታርት አፕን በፖሊሲ በመደገፍ ኋላ ቀርነትንና ረሃብን ታሪክ ማድረግ ይገባል። እንዲሁም ሥራ ፈጣሪዎችን ለማብዛትና ውጤታማነትን ለማሳደግ እንደሚረዳ ገልጸዋል።

ረቂቅ አዋጁ ለስታርት አፕ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር እንደ ሀገር የተያዘውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ እውን ለማድረግ ያግዛል። ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ጋር በንግድ በማስተሳሰር ዘርፉን ለማሳደግ ወሳኝ ሚናን እንደሚጫወት ገልጸዋል።



# ብልፅግና ፓርቲ ስኬቶችን ለማስቀጠልና ሀገራዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ አበክሮ ይሠራል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የብልፅግና ፓርቲ ስኬቶችን ለማስቀጠልና ሀገራዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ አበክሮ እንደሚሠራ የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ ገለጹ።

የብልፅግና ፓርቲ 5ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል "የሃሳብ ልዕልና ለሁለንተናዊ ብልፅግና" በሚል መሪ ሃሳብ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ትናንት ተከብሯል።

የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት ፤ ብልፅግና በሃሳብ ልዕልና የሚያምን፤ ኢ-ፍትሃዊነት፣ አግላይነት፣ የነጠላ ትርክት የበላይነትና ሌሎች ችግሮችን በሃሳብ ልዕልና ለመፍታት በፅኑ መሠረት ላይ የተመሠረተ ፓርቲ ነው።

ያልተገራ ስሜትና ፅንፈኝነት የሚገራው፤ ዘላቂ ሰላም የሚረጋገጠው፣ የሕዝብ ኑሮ የሚሻሻለው፣ ብሔራዊ ጥቅም የሚከበረው፣ የጥራትና የኢፍትሀዊነት ችግሮች የሚቀረፉት፣ ማህበራዊ ፍትህ የሚነግሰው በሃሳብ ልዕልና ብቻ እንደሆነ አስገንዝበዋል።

ፓርቲው ስር የሰደዱ ሀገራዊ ችግሮችን በመቅረፍ ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ሕልም ሰንቆ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

"መዳረሻችን ሁለንተናዊ ብልፅግና፤ አንድነት፣ ሕብረ ብሔራዊነትና አካታችነት ነው" ያሉት አቶ አደም፤ ሁሉም ሰው በደስታና በክብር የሚኖርበት፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና ማህበራዊ መስኮች በሁሉም ለሁሉም በሆነ አግባብ ስኬት ለማረጋገጥ እየተጋን ነው ብለዋል።

በጋራ ከሠራን ሀገራዊ ብልፅግና ማረጋገጥ እንደሚቻልም የፓርቲው የአምስት ዓመታት ጉዞ በተግባር ማሳየቱን ነው ያስረዱት።

በበሳልና ብቁ መሪ፣ በቁርጠኛ አመራርና አባላት እንዲሁም በሕዝብ ድጋፍ ታጅቦ በፈተናዎች ሳይዛነፍ ስኬቶችን ማስመዝገብ መቻሉን አብራርተዋል።

የፖሊቲካ ምህዳር ማስፋት መቻሉ፣ የአሰባሳቢ ትርክት ግንባታ መጀመሩ፣ እውነተኛ ፌዴራሊዝም እየተገነባ መሆኑ፣ ምርታማነትን እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ዕውን ለማድረግ የተሠሩ ሥራዎች ከስኬቶቹ መካከል በዋቢነት ገልፀዋል።

በኢኮኖሚ መስኮች በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በስንዴ፣ በሌማት ትሩፋት፣ በኮሪደር ልማት የተመዘገቡ ስኬቶች እንዲሁም በማህበራዊ መስኮች የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል የተከናወኑ የማህበራዊ አገልግሎት ተግባራትን ጠቅሰዋል።

በውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ረገድም በዓለም መድረክ ስኬቶች መመዝገባቸውን ጠቅሰው፤ ወዳጅ ሀገራት ማብዛትና የብሪክስ አባልነትን ለአብነት አንስተዋል።

በአጠቃላይ ብልፅግና በተመሠረተ በጥቂት ዓመታት ውስጥ መልከ ብዙ ስኬቶች ያስመዘገበ ፓርቲ ነው ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

በቀጣይም ስኬቶችን ለማስቀጠልና ሀገራዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ አበክሮ እንደሚሠራ አረጋግጠዋል።

# በኢትዮጵያ የፀረ- ተህዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል

**ታምራት ተስፋዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የፀረ- ተህዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ ተገለፀ።

በኢትዮጵያ ምግብና የመድኃኒት ባለሥልጣን መድኃኒት ደህንነት ክትትልና የህክምና ሙከራ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ አስናቀች አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች ደህንነቱ የተጠበቀ የሕክምና ሂደቶችን ለማረጋገጥና ለተለያዩ የሕክምና ሂደቶች ወሳኝ ሚና አላቸው። የውጤታማ ፀረ- ተህዋሲያን መድኃኒቶች እጥረት የሕክምና አገልግሎቶችን በማወክ በተለይ የታካሚዎች ደህንነት አደጋ ላይ በመጣል ለአካል ጉዳት ከፍ ሲል ለሞት ይዳርጋል።

ፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች በተህዋሲያን መላመድም የበሽታ አምጪ ጀርሞችን ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶች አቅም ሲፈተን የሚከሰት ነው። በሰዎች፣ በእንስሳትና በእፅዋት ላይ መድኃኒቶችን ያለ አግባብ መጠቀምም መድኃኒቶች በተህዋሲያን በቀላሉ እንዲላመዱና በሽታ ፈዋሽነታቸውን እንዲያጡ ያደርጋል።

«በኢትዮጵያም የፀረ- ተህዋሲያን መድኃኒቶች በተህዋሲያን መለመድ ችግር አሳሳቢ በሚባል ደረጃ ላይ ደርሳል» ያሉት መሪ ሥራ አስፈፃሚዋ፣ በችግሩ ምክንያት በሀገሪቱ በዓመት ከ106 ሺ በላይ ሰዎች ለህልፈት እንደሚዳረጉ በጥናት መረጋገጡንም አስታውቀዋል። ይህም ከፍተኛ የሚባል የሞት ቁጥር መሆኑን አስገንዝበዋል።



ወይዘሮ አስናቀች አለሙ

ከችግሩ አሳሳቢነት አንፃር የጤና፣ የግብርና እና የአካባቢ ጥበቃን ጨምሮ ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ የጋራ ስትራቴጂ ተቀርፆ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፣ በዚህም የግንዛቤ ፈጠራ፣ የቅኝት ሥራዎች፣ የመድኃኒት ጥራትና ደህንነት እና የግልና አካባቢ ንፅህናን ማስጠበቅ እንዲሁም ከመድኃኒት አግባብአዊ አጠቃቀም ጋር የተዛመዱ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም አብራርተዋል።

ችግሩን ለመከላከል ዓለም አቀፍ ትብብር አስፈላጊ መሆኑንና መንግሥታትም ምርምር ላይ ኢንቨስት ማድረግን ጨምሮ መረጃዎችና ስልቶችን መለዋወጥ አለባቸው» ብለዋል።

በሀገር ደረጃ ችግሩን ለመከላከልም፣ በተለይ በጤና እንክብካቤና በግብርና ላይ ፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች አጠቃቀምን በተመለከተ ጥብቅ ደንቦችን መተግበርና ፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች ተጠያቂነት ባለው አጠቃቀም ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ የግልና የአካባቢ ንፅህናና ጤናን መጠበቅ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የፀረ- ተህዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሳምንት ከህዳር 9 እስከ 15 «እናስተምር፣ እናሳውቅ፣ አሁን እንተግብር» በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ይገኛል።

የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ እንደሚያመላክተው፣ የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች በተህዋሲያን መላመድ ምክንያት እኤአ በ2019 በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ሕይወት ተቀጥፏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በወርቅ ላይ የመጣውን ለውጥ ማጣጣም፣ ለዘላቂነቱም በትኩረት መሥራት!

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እየጨመረ ይገኛል፤ ለውጭ ገበያ ከቀረበ የወርቅ ምርት የሚገኘው የውጭ ምንዛሬም ከፍተኛ መሆን ጀምሯል። ከወርቅ አምራች ክልሎች እንዲሁም ከማዕድን ሚኒስቴር የሚወጡ መረጃዎችም እንዲሁ ወደ ባንኩ የሚገባው የወርቅ መጠን እየጨመረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው።

ይህ ትልቅ ዜና ነው። ለውጡ ሀገሪቱ እምቅ የወርቅ ሀብት እንዳላት እንዲሁም የሀገሪቱን የወርቅ ሀብት በሚገባ በማልማት ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም እንዲሁም በኮንትሮባንድ ሳቢያ የሀገሪቱ የወርቅ ምርት የሕገወጦች ሲሳይ ሆኗል እየተባለ ሁሌም ሲገለጽባት በቆየች ሀገር ይህን ዜና መስማት ትልቅ የምስራች ነው።

አሁን እየታየ ያለው ለውጥ ለብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን ማንሰራራት እያሳየ ነው ከሚለውም በላይ የሚገለጽ ነው። በሩብ አመቱ የታየው ከፍተኛ ለውጥ ነውና። በሩብ ዓመቱ ለውጭ ገበያ ከቀረበው ወርቅ የተገኘው የውጭ ምንዛሬም እንዲሁ ከፍተኛ ነውና ለውጡን ከፍ አድርጎ መመልከት ይገባል።

ይህ ለውጥ እንዴት መጣ ብሎ መጠየቅ ግን ይገባል። የፌዴራል መንግሥት ሕገወጥ የወርቅ ግብይትን ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል በማቋቋም ባለፉት ዓመታት መሥራቱ ለመጣው ለውጥ አንዱ አስተዋጽኦ ያበረከተ ሊባል ይችላል።

በዚህም በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎችና ኢትዮጵያውያን ወርቅ የማውጣትም ሆነ የማዘዋወር ፈቃድ ሳይኖራቸው በዚህ ሕገወጥ ተግባር ውስጥ ተገኝተው በቁጥጥር ሥር መዋላቸው ይታወቃል። በዚህም ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለውጥ እንዲያሳይ ማድረግ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

መንግሥት በ2017 በጀት አመት መጀመሪያ ወደ ሙሉ ትግበራ ባስገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ደግሞ የወርቅ ሕገወጥ ግብይትን አከራካሪ መስበር የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ ምርት እንዲሁም ወደ ውጭ ከተላከ ወርቅ እየተገኘ ያለው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬም ይህንን ይጠቁማል።

በ2016 በጀት ዓመት አራት ቶን ወርቅ ብቻ ነበር ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው፤ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ግን ሰባት ቶን ወርቅ ወደ ባንኩ ገብቷል። በሩብ ዓመቱ ለውጭ ገበያ ከተላከ የወርቅ ምርት የተገኘው ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው። ማዕድን ሚኒስቴር በሩብ ዓመቱ የዓመታዊ እቅዱን 70 በመቶ ፈጽሟል። ይሄ የሚበረታታ ትልቅ ለውጥ ነው።

ከክልሎች የሚወጡ መረጃዎች ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው። ለአብነትም ከዋናው የወርቅ አምራች ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በ2016 በጀት ዓመት ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው የወርቅ ምርት 274 ኪሎ ግራም ሲሆን፣ በዘንድሮው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዚህ እጥፍ 548 ኪሎግራም ወርቅ ወደ ባንኩ ገቢ ተደርጓል። ክልሉ በሩብ ዓመቱ ለባንኩ ገቢ ለማድረግ ከያዘው ዕቅድም በላይ ነው አፈጻጸም የታየው። ይህ ሁሉ በወርቅ ምርት ግብይት ላይ ተፈጥሮ የነበረው ችግር እየተፈታ መምጣቱን ያመለክታል።

በቅርቡ ደግሞ እንደ ሀገር የሚመረተውን የወርቅ መጠን መጨመር የሚያስችል የወርቅ ማምረቱን ሥራም ከባህላዊና ከኋላ ቀር አሠራር ለማውጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል አዲስ የወርቅ ፋብሪካ በጋምቤላ ክልል ሰሞኑን በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቋል። ፋብሪካው በባህላዊ መንገድ ወርቅ በማምረት ወቅት ሊባክን የሚችለውን ወርቅ ከብክነት የሚታደግ መሆኑም ተገልጿል። በቀጣይም ሌሎች ዘመናዊ የወርቅ ፋብሪካዎች ልማቱን እንደሚቀላቀሉ ይጠበቃል።

እነዚህ በወርቅ ሕወገወጥ ግብይት ላይ የተወሰዱ ርምጃዎች፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትግበራው፣ አዲስ የወርቅ ፋብሪካ ወደ ሥራ መግባቱ፣ በወርቅ አምራቾች ዘንድ የተፈጠረው መነሳሳት በወርቅ ምርት መጨመር ላይ ያመጡት እመርታ በቀጣይም ተመሳሳይ እመርታ እንዲመዘገብ ለማድረግ ያስችላል።

ሀገሪቱ ያላትን የወርቅ እምቅ አቅም በሚገባ ማልማት ከተቻለ ወርቅ ለሀገር የውጭ ምንዛሬ ግኝት ትልቁ ሀብት መሆን እንደሚችል ይታመናል፤ በሩብ ዓመቱ የታየው ለውጥም ይህን ያመለክታል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ሕገወጦቹን መገዳደር የሚያስችል አቅም እንደፈጠረም መረዳት ቢታወቅም፣ የሀገሪቱ ሀብት ምን ያህል በሕገወጦች ሲመዘበር እንደቆየ በሚገባ ጠቁሟልና ሕገወጦችን ለመቆጣጠር የሚደረገው ርብርብ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ሀገር ከወርቅ ምርት ብዙ ትጠብቃለች። በተገኘው ለውጥም መዘናጋት አይገባም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር በጋምቤላ የተገነባው ኢትኖማይኒግ የወርቅ ፋብሪካን በመረቁበት ወቅት እንዳስታወቁትም ሀገሪቱ በዚህ በጀት ዓመት ከወርቅ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማምረት አቅዳለች።

በወርቅ ላይ የታየው ለውጥ ሊደነቅ የሚገባው ሆኖ፣ ካለው እምቅ አቅም፣ ከተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች፣ የወርቅ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እየገቡ ያሉበት ሁኔታ ሀገሪቱ የያዘችው እቅድ ሲታሰብ ለለውጡ ዘላቂነት መሥራት የግድ ይሆናል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ያለደረሰኝ ካልሸጥኩ - በፍጥነት መታረም ያለበት ድርጊት

ዘካርያስ

የሀገሪቱ ገቢ አሰባሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። ባለፉት ዓመታት በየአመቱ በመቶ ቢሊዮን ብሮች እያደገ የመጣው ገቢ ዘንድሮ ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ እንደሚደርስ ይጠበቃል። ሀገሪቱም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ተገቢውን ግብር ለመሰብሰብ አሠራሮችን በማዘመንና አዳዲስ አሠራሮችን በመተግበር ስትሠራ ቆይታለች። ይህን ስራዋን ዘንድሮም በተጠናከረ መልኩ እንደምትቀጥልበት አስታውቃለች።

እንደሚታወቀው ገቢ ከተለያዩ ምንጮች ሊሰበሰብ ይችላል። እየተሰበሰበም ነው። ምንም እንኳ ሀገሪቱ የምትሰበስበው ገቢ እየጨመረ ቢመጣም፣ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት አኳያ ሲታይ መሰብሰብ ያለባትን ያህል ገቢ እየተሰበሰበ አይደለም። ይሄ ደግሞ ሁሌም በመንግሥት በኩል ይገለጻል።

ይህ እየሆነ ያለው ደግሞ የግብር መሠረት ባለመስፋቱ ፣ ገቢ መሰወር በስፋት የሚስተዋል በመሆኑ፣ በደረሰኝ ግብይት ሊፈጸምበት የሚገባ ንግድና የመሳሰለው ተግባር ያለደረሰኝ መከናወኑ፣ የግብር አሰባሰቡ ባለመዘመኑ፣ ግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች ላይ በሚስተዋለው የኪራይ ሰብሳቢነትና የመሳሰሉት ችግሮች በመንሰራፋታቸው ስለመሆኑ ሁሌም ይገለጻል።

በተለይ ግብይትን ያለደረሰኝ መፈጸም ግብይት በደረሰኝ በሚፈጸምበት ወቅት መንግሥትና ሕዝቡ ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም ያስቀራል። ለእዚህም እንደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ያሉትን ታክሶችንና የመሳሰሉትን መሰብሰብ አይቻልም። ግብርን በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ ለመወሰንም አያስችልም።

መንግሥት ይህን መሠረታዊ ችግር ለመፍታት በተለይ የንግዱ ማህበረሰብ ሕጉ በሚያዘው መሰረት ሽያጩን በደረሰኝ እንዲያደርግ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፤ በዚህ ጥረት የተወሰኑ ለውጦችም ታይተዋል ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ይሁንና አብዛኛዎቹ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ሊባል በሚችል መልኩ ያለደረሰኝ ግብይት የሚያደርግ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የሚጠበቅበትን ግብር እየከፈለ ስላለመሆኑ ይታወቃል።

በመሠረቱ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ገቢ ለመሰብሰብ ሲታቀድ በግብር መረብ ውስጥ ያለው ግብር ከፋይ ብዙም ሊያሳስብ አይገባም፤ ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል ተፈልጎ ከሆነም በዚያው ላይ የሚሰላ ይሆናል። ያለደረሰኝ ግብይት የሚፈጽሙት የንግዱ ማህበረሰብ አባላትን ግን በሚጠበቀው መልኩ ግብር ለማስከፈል አዳጋች ይሆናል።

ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በመሰብሰብ ሂደት አሳሳቢ ሊሆኑ የሚገባቸው እነዚህ ግብይታቸውን ያለደረሰኝ የሚያካሂዱ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ናቸው። በእርግጥ እነዚህ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ጥቂት አይደሉም፤ ሁላችንም ግብይት ስንፈጽም የሚሆነውን እናውቃለንና እጅግ በርካታ ናቸው።

በሀገሪቱ ትንሽ ገቢ ያለው ሠራተኛ ግብር ይከፍላል፤ ብዙ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ነጋዴ ብዙ ግብር ሲከፍል የማይታይ ስለመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትም ይገልጻሉ። ይህ አይነቱ ሕገወጥ ተግባር በዚህች ሀገር በጣም ተኖሯል፤ ንግዱ አየር ባየር የሚካሄድ ስለሆነ አይደለም ይህ ሲሆን የቆየው፤ መደብር ይዘው፣ መደብ ይዘው የሚነግዱ፣ ንግዳቸው በጣም የሰፋ ነጋዴዎች ይከፍላሉ የሚባለው ግብር በራሱም ያሳፍራል።

እነዚህ አካላት ግብይቱን በደረሰኝ የማይፈጽሙበት አንዱ ምክንያት ግብር ለመሰወር እንዲያመቻቸው ነው፤ ሌላው ደግሞ ሸቀጦችን የሚሸጡበትን ዋጋ መንግሥት እንዳያውቅባቸውና ክትትል እንዳያደርግባቸው ስለሚፈልጉም ነው። በደረሰኝ ግብይት እንዲፈጸም መደረጉ ለህብረተሰቡም ለመንግሥትም ይጠቅማል። ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ዋጋን ለመከታተልም ይረዳል። በደረሰኝ ላይ የተመለከተው ዋጋ አላግባብ ዋጋ የተጠየቀበት ከሆነ ሕገወጦችን ለመጠየቅ ያስችላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እነዚህን ነጋዴዎች ነው ግብይታቸውን በደረሰኝ እንዲያደርጉ ለማድረግ ወደ ሥራ የገባው። ከተማ አስተዳደሩ የንግዱ ሥራ በሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ ከዚያም ተገቢው ግብር እንዲሰበሰብ ለማስቻል ነው እየሠራ ያለው። አሠራሩ የሠለጠነ አካሄድ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል።

መንግሥት በዚህ በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ ለመሰብሰብ እንዲቻል የተለያዩ ተግባሮች እንደሚከናወኑ በአመቱ መጀመሪያ ላይ አሳውቋል። ይህ የከተማ አስተዳደሩ ርምጃም ከዚህ የመንግሥት አቅጣጫ የወጣ ነው። ይህን ገቢ ለመሰብሰብ በቅድሚያ የንግዱ ማህበረሰብ ግብይቱን በደረሰኝ ማድረግ ይኖርበታል። ግብይቱ በደረሰኝ ከተፈጸመ በዚያ ላይ በመመስረት ግብር መጣልና ገቢን መሰብሰብ ይቻላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለይ የመርካቶ ነጋዴዎች ግብይታቸውን በደረሰኝ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ሥራ መጀመሩ የረፈደ ቢሆንም ትክክል ነው፤ ሌላ ምንም ዓላማ የለውም። ሥራው የቱንም ያህል ፈታኝ ቢሆን ከተማ አስተዳደሩ ይፈጽመዋል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ መርካቶ ላይ እየታየ ያለው ማንገራገር ግን ተገቢ አይደለም። ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሥራው አልጋ ባልጋ እንዳይሆን የሚያደርጉ ሁኔታዎች ተከስተዋል። ይህ ግን ተገቢ አይደለም።

መንግሥት አሁን እየተገበረ ያለው አሠራር ከዓመታት በፊት መተግብር የነበረበት ነው። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምንም አሠራሩ ሳይተገበር ቆይቷል። አሁን ቀኑ ደርሶ ትግበራው ተጀምሯል። መንግሥት ለንግዱ ማህበረሰብ የአሠራሩን አስፈላጊነት አስመልክቶ ግንዛቤ እያስጨበጠ፣ ከዚህ ወጣ ያለ ሁኔታም ሲያጋጥም በሕግ እየጠየቀ ሊፈጽመው ይገባል።

ለራሱ ለንግዱ ማህበረሰብም ቢሆን ይጠቅመዋል፤ ነጋዴው ምንም እንኳ ያለውንና የሌለውን የሚያውቅ ቢሆንም፣ በቴክኖሎጂና በደረሰኝ ተጠቅሞ የሸጠውንና ያልሸጠውን በቀላሉ ማወቅም የሚያስችለው ይሆናል። በዚህ ሥራዎች ሁሉ በቴክኖሎጂ በሚሠሩበት ዘመን ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም ማንንም አይጠቅምም።

ሌላው ለእኔ ወሳኙ ጉዳይ ግብር ነው። ተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ ካለበትም እንዲሰበሰብ ያስችላል፤ ከዚያ ውጪ ደግሞ ግብር ክፍያ ሲመጣ በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ ግብሩ እንዲሰላ ያስችላል። በደረሰኝ ግብይት መፈጸም በነጋዴው ላይ ሊያስከትል የሚችለው ችግር የለም። አሁን ጉዳዩን ለማወሳሰብ የሚሞክሩት ሌላ ዓላማ ያላቸው ናቸው።

ይሄ ደግሞ ተገቢ አይደለም። ከተማዋ ሀገሪቱ መሠረተ ልማቶችን እንዲያሟሉ፣ ጤና እንዲጠበቅ፣ ትምህርት እንዲስፋፋ ፣ ወዘተ የሚፈልግ ማህበረሰብ በእዚህ ልክ የመንግሥት አሠራር ላይ ማንገራገር አይደለም የሃሳብ ልዩነት መፍጠር የለበትም። ሃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው እየተፈጸመ ያለው። በፍጥነት መታረም ይኖርበታል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ባለፈው መስከረም ወር የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የ2017 በጀት ዓመት የሥራ መጀመሪያ በሆነው የጋራ ስብሰባ ላይ የመንግሥትን የ2017 በጀት ዓመት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫ ባስታወቁበት ወቅትም የገቢ መሰብሰብ አስፈላጊነትን አጽንኦት ሰጥተው ማመልከታቸው ይታወቃል።

ፕሬዚዳንቱ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ ወደ ግብር መረቡ ያልገቡትን እንዲገቡ እንዲሁም አዳዲስ የታክስ አይነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ፣ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ለማዘመንና ታክስ በመሰብሰብ ሂደት የሚወጣውን ወጪ ውጤታማ ለማድረግ መንግሥት ይሠራል።

በፌዴራል ደረጃ ያሉትን የታክስ ማሻሻያ ሥራዎች ወደ ክልሎችም ማውረድ በክልል ደረጃ የሚሰበሰበውን ገቢ ለማሳደግ የመንግሥትን የአገልግሎት አሰጣጥ በማዘመንና በማሻሻል፣ ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገቢ ለማሳደግ ርብርብ ይደረጋል፤ ለኢንቨስትመንት ማበረታቻነት የሚሰጡ ከታክስ ጋር ግንኙነት ያላቸው ማበረታቻዎች እና ድጎማዎች ውጤታማ እንዲሆኑ እንዲሁም የታክስና ታክስ ያልሆኑ ገቢዎችን ለማሻሻል ይሠራል።

በዚህ ሁሉ ስራም አጠቃላይ የመንግሥትን ገቢ አንድ ነጥብ አምስት ትሪሊዮን ብር ለማድረስ እንዲሁም ገቢ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ወደ ስምንት ነጥብ ሶስት በመቶ እንዲያድግ እንደሚሠራ አስታውቀዋል። ለእዚህ የመንግሥት እቅድ መሳካት ሁሉም ግብር ከፋዮች ፣ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች ፣ የሕግ አካላት ፣ ወዘተ መተባበር ይኖርባቸዋል።

# አዋሽ ባንክ አጠቃላይ የሀብት መጠኑ 282 ቢሊዮን ብር ደረሰ

## - ባንኩ አንድ ነጥብ 52 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ሰብስቧል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- እኤአ በ2023/24 የሂሳብ ዓመት አጠቃላይ የሀብት መጠኑ 282 ቢሊዮን ብር መድረሱን የአዋሽ ባንክ አስታወቀ። ባንኩ አንድ ነጥብ 52 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ መሰብሰቡን ጠቁሟል፡፡

የአዋሽ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክስዮኖች 29ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ትናንት በአዲስ አበባ አካሂዷል። የአዋሽ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ጉሬ ኩምሳ በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ አዋሽ ባንክ እኤአ በ2023/24 የሂሳብ ዓመት አጠቃላይ የሀብት መጠኑ 282 ቢሊዮን ብር ደርሷል።

አዋሽ ባንክ ኢ.ማ በ2023/24 የሂሳብ ዓመት 10 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ያልተጣራ ትርፍ አስመዝግቧል ያሉት አቶ ጉሬ ፤ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር አንድ ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ጭማሪ ተመዝግቧል ብለዋል።

በዓመቱ ውስጥ ባንኩ 45 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰቡን ጠቅሰው፤ የባንኩ አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ ብር 232 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር መድረሱን ተናግረዋል።



**አቶ ጉሬ ኩምሳ**

የባንኩ አጠቃላይ የብድር መጠን 183 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ደርሷል ያሉት ሰብሳቢው፤ በሂሳብ ዓመቱ የባንኩ ጠቅላላ ገቢ 36 ነጥብ 58 ቢሊዮን ብር ተመዝግቧል ብለዋል። ባንኩ በሂሳብ ዓመቱ አንድ ነጥብ 52 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ መሰብሰቡን ጠቁመዋል።

በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ የባንኩ አጠቃላይ የሀብት መጠን ብር 282 ቢሊዮን መድረሱን ጠቅሰው፤ የባንኩ የቅርንጫፍ ቁጥር 947 መድረሱን ገልጸዋል።

አጠቃላይ የደንበኞች ብዛት 12 ነጥብ 41 ሚሊዮን በላይ መሆኑ የገለጹት ሰብሳቢው፤ የባንኩ ባለአክሲዮኖች ቁጥር ከ11ሺ በላይ የደረሰ ሲሆን የተከፈለ የካፒታል መጠኑ ደግሞ ከ20 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ ደርሷል ብለዋል።

ባንኩ የተለየዩ ስትራቴጂዎችን በመቀየስ አበረታች ውጤት ማስመዝገቡን አመልክተው፤ ቦርዱ በዓመቱ የሀገሪቱን የፋይናንስ ሕግና የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን በጠበቀ መልኩ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ማጽደቁን ገልጸዋል።

ባንኩ ለህብረተሰቡ የባንክ አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ በኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አካባቢዎች ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

አዋሽ ባንክ ዘመናዊ አዲስ የዋና መሥሪያ ቤት ህንጻ ለመገንባት 10 ሺህ 500 ካሬ ሜትር መሬት በሊዝ መረከቡን ገልጸው፤ ለህንጻው ግንባታ የፕሮጀክት ቢሮ ተቋቁሞ የግንባታውን ዲዛይን ለማሠራት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

# “የሀገሪቱን ዕምቅ የማዕድን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አውስተው፤ መሠረተ ልማትን ማስፋፋትና ማዘመን ከሚሠሩት ሥራዎች መካከል እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል።

ይህም አምራቾችን ከገዢዎች ለማገናኘት እና የትራንስፖርት ወጪዎችን ለመቀነስ ያግዛል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በሀገሪቱ በቅርቡ ወደ ተግባር የገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የማዕድን ዘርፉን ለማሳደግ ጉልህ ሚና እንዳለው ገልጸዋል።

በሀገሪቱ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች የተለያዩ ማዕድን ሀብቶችን በባህላዊ መንገድ በማውጣት ተጠቃሚ እየሆኑ መሆኑን ጠቁመው፤ ሀገሪቱ ካላት የማዕድን ሀብት አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ስኩየር ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው ቦታ ካርታ እንደተሠራለት አመላክተዋል።

በአፍሪካ ሀገራት ሁሉን አቀፍ የማዕድን ካርታ አለመሠራቱ ለዘርፉ ተግዳሮት መሆኑን አስታውቀዋል።

የማዕድን ሚኒስትር ሀብታሙ ተገኝ (ኢ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በማዕድን ዘርፉ ያሉትን ተግዳሮቶች በመፍታት ሀገሪቱን ተጠቃሚ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እያከናወነ ይገኛል።

ማዕድን አምራቾችና ላኪዎች፣ የማዕድን ተጠቃሚዎች፣ የቴክኖሎጂ አምራችና አቅራቢዎች ምርትና አገልግሎታቸውን በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበት ዓለም አቀፍ ኤክስፖ በየዓመቱ እየተካሄደ መሆኑን አመላክተዋል።

ሶስተኛውን ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ሀገሪቱ ያሏትን ወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የከበሩ ማእድናት፣ ጌጣጌጦች፣ የኢንዱስትሪ ማዕድን፣ ቴክኖሎጂዎችን እና ሌሎች በርካታ ማዕድናትን በማቅረብ የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

# የጥራት መንደሩ የኢትዮጵያ....

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የጥራት መንደሩ መመረቅ ለኢትዮጵያ ትርጉም ብዙ መሆኑን አመልክተው፤ ለሀገር ውስጥ ሆነ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ጥራታቸውን ማረጋገጥ የሚቻለው የተሟላ የጥራት መሠረተ ልማት ሲኖር መሆኑን ተናግረዋል።

ዐለምሳሌም በርካታ የታሸጉ የምግብ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚገቡ ጠቁመው፤ እነዚህ የታሸጉ ምግቦች በጥራት መንደሩ ገብተው ጥራታቸው በቤተ ሙከራ (ላብራቶሪ)ተፈትሾ ችግር ካለበት ወደ ገበያ እንዳይሰራጭ በማድረግ ጉዳቱን ማስቀረት እንደሚቻል ነው የገለጹት።

ዐየጥራት መንደሩ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖረው አመልክተው፤ ተቋሙ በተሟላ አቅም ሥራውን ሲጀምር የወጪ ንግድ እንደሚያድግና ወደ ሀገር ውስጥ የምናስገባቸውም ጥራታቸው የተረጋገጠ ይሆናል ብለዋል። ይህም ኢትዮጵያ በዓለም ገበያ ምርጥ ምርጡን የምትቀበል፣ ጥራቱ የተረጋገጠ ምርት የምትቀበል ሀገር እንደሚያደርጋት ገልጸዋል።

ዐየጥራት መንደሩ ቁልፍ ተቋማትን ያቀፈ ሲሆን፤ እነዚህም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ የኢትዮጵያ የሥነ ልክ ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት እና የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን መሆናቸው ተጠቅሷል።

ብሄራዊ የጥራት መንደሩ የጥራት ማረጋገጫ ቤተ ሙከራዎች (ላብራቶሪዎች) የተሟሉለትና መንደሩም በሰባት ነጥብ ሁለት ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን ዘመናዊ ቤተ ሙከራዎችን ጨምሮ ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ወጪ እንደሆነበት በምረቃ በመርሃ ግብሩ ተገልጿል።

# ጥንቃቄን የሚሻው የስኳር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

(ስሟ የተቀየረ) ህመሙ እንዳለባት ካወቀች ዓመት እንዳልሞላት ትገልፃለች። እንደ እሷ ገለፃ ህመሙ እንዳለባት ሳታውቅ ረጅም ጊዜ ቆይታለች። ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰውነቴ እየቀነሰ ሲሄድ ተደናግጬ የኤች አይቪ ምርመራ እስከማድረግ ደርሻለሁ የምትለው ፅጌ፤ አቅሟ ተዳክሞ መንቀሳቀስ እያቃታት ሲመጣ ወደ ሆስፒታል እንዳቀናች ታስታውሳለች።

ምርመራ ያደረጉላት ሀኪሞችም ስኳሯ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ገልፀው፤ ሆስፒታል ተኝታ እንድትታከም ማድረጋቸውን ትገልፃለች። ከዚህ ጊዜ አንስቶም ኢንሱሊን መጠቀም እንደጀመረች አስታውሳ፤ በቤተሰብ ደረጃ ህመሙ ያለበት ሰው ስላልነበረ፣ ዕድሜዋ ከአርባ ዓመት በታች ስለሆነና ያን ያህል አስጊ የሚባል የሰውነት ክብደት ስላልነበራት ህመሙ ይከሰታል ብላ እንዳላሰበችም ታስረዳለች።

በአንድ ወቅት በህክምና ስህተት ምክንያት በተከታታይ ያስነቀለቻቸው የመንጋጋ ጥርሶች እንደነበሩ አስታውሳ፤ በተለይ የመጨረሻውን ስትነቀል ራሷን እስከ መሳት ደርሳ እንደነበርና ከዚህ ጊዜ በኋላ አቅሟ ሲደክም ጣፋጭ የሆኑ የጁስና የለስላሳ መጠጦችን አብዝታ ትጠቀም እንደነበርም አንስታለች። ለዚህ ህመም የተጋለጠችውም በዛ ወቅት እንደሆነ ታምናለች።

አሁን ላይ መድሃኒቱን በአግባቡ እየተጠቀመች መሆኑን ገልፃ፤ አመጋገብ ላይም በተቻለ መጠን ጥንቃቄ እያደረገች መሆኑን ትገልፃለች።

በረዳት ሄልዝ ኬር የህክምና ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ሞገስ አብርሃ በበኩላቸው ሶስት አይነት የስኳር ህመሞች እንዳሉ ይገልፃሉ። እንደእርሳቸው ገለፃ ሶስቱ የስኳር በሽታ አይነቶች አይነት አንድ፣ አይነት ሁለትና አይነት ሶስት በመባል ይታወቃሉ።

አይነት አንድ ከዘረ መል ጋር ተያይዞ የሚመጣና በለጋ እድሜም ሊከሰት የሚችል፣ አይነት ሁለት ከእድሜ መጨመርና ከመጠን በላይ በሆነ ክብደት ምክንያት እንዲሁም አይነት ሶስት ከእርግዝና ጋር ተያይዞ በሆርሞን ለውጥ ምክንያት ሊፈጠር እንደሚችል ያብራራሉ። በተጨማሪም አንዳንድ መድሃኒቶችም ለስኳር ህመም መነሻ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ።

አንድ ሰው ስኳሩ ከፍ ስላለ ብቻ የስኳር በሽታ አለብህ አይባልም የሚሉት ባለሙያው፤ ጭንቀት እና እንቅልፍ ማጣት ሲኖር፣ የተመገብነው ምግብ ከፍተኛ




የስኳር መጠን ሲኖረው፣ ኀዘን ውስጥ ስንሆን፣ ቀዶ ጥገና ሲኖር እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች የስኳር መጠን ከፍ ሊል እንደሚችል ያስረዳሉ።

አንድ ሰው ስኳሩ ከፍ ብሎ መድሃኒት ከመጀመሩ በፊት የአኗኗር ዘይቤውንና አመጋገቡን እንዲያስተካክል እንዲሁም የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ እንመክራለን ይላሉ።


ሆኖም ከአንድ ዓመትም ሆነ ከስድስት ወር በኋላ በድጋሚ ተመርምሮ የስኳር ህመም እንዳለበት ከተረጋገጠ በአመጋገብ፣ በአኗኗር ዘይቤና በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ብቻ ሊታከም ስለማይችል ኢንሱሊን የተባለውን የስኳር በሽታ መድሃኒት በመጀመር እንደሚገባው ይገልፃሉ።

የስኳር ህመም በተለይም ዓይንን፣ ኩላሊትንና ነርቭን የማጥቃት ባህሪ አለው የሚሉት ባለሙያው፤ ይህንንም ለመከላከል የግድ መድሃኒቱን በአግባቡ መውሰድ ያስፈልገናል ይላሉ።

ከአኗኗር ዘይቤ መቀየርና የታሸጉ ምግቦችን አብዝቶ መጠቀም ጋር ተያይዞ በአሁኑ ሰአት በሀገራችን እንደስኳር፣ ደምግፊት፣ የልብ ችግርና ካንሰርን የመሳሰሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እየጨመሩ እንዳሉ የሚገልፁት ባለሙያው፤ ህብረተሰቡ በሚችለው ልክ የጤና ምርመራ በማድረግ፣ ችግሩ ከተከሰተም መድሃኒቱን በአግባቡ በመውሰድ የሚመጣውን ተጓዳኝ ችግር ማስወገድ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የዕንቁ መንገድ- የጂኦቱሪዝም አሳቤ

ዳግም ከበደ



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

**እርሱ የካምፓኒው ሰራተኞች የእለት ተእለት የሎጅስቲክ ፍላጎት ከማሟላት አንስቶ አስፈላጊ የሚባሉ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ ኃላፊነት ነበረበት**

እንቁ ሙሉጌታ አብርሀም ይባላል። በኢትዮጵያ የቱሪዝምና የማዕድን ዘርፍ ላለፉት 30 ዓመታት አገልግሏል። ‹‹በዓለም ትታይ ኢትዮጵያ›› የአስጎብኚ ድርጅት በመመስረት የኢትዮጵያን የመስህብ ሀብቶች እያስጎበኘ ይገኛል። በተለይ በስነ ምድር ሳይንስና በከርሰ ምድር ሀብት ጥናት እና በጂኦ ቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ልምድ አለው። የጂኦ-ቱሪዝም በኢትዮጵያ በፖሊሲ ተደግፎ ተግባራዊ እንዲሆን፤ የአገሪቱ ሀብቶች ለዓለም እንዲተዋወቁ ተፅዕኖ እየፈጠሩ ከሚገኙ አንጋፋ ባለሙያዎች ቀዳሚው ነው። ለዛሬ የዝግጅት ክፍላችን " የሕይወት ገፅታ " አምድ እንግዳችን አድርጎታል።

### ትውልድ እና እድገት

እንቁ ሙሉጌታ ተወልዶ ያደገው በአዲስ አበባ ነው፤ ግዜው ደግሞ 1963 ዓ.ም። ቤተሰቦቹ ትምህርትን የመቀበል እድሜ ላይ ሲደር በመኖሪያ አካባቢያቸው (መስቀል ፍላወር) ወደሚገኝ ‹‹ፒተር ፓን›› የሚባል መዋለ ሕፃናት አስገቡት። እናቱ ወይዘሮ መፅሄት ተፈራና አባቱ መቶ አለቃ ሙሉጌታ አብርሀም ለትምህርት ልዩ ትኩረት የሚሰጡ ነበሩ። ትምህርት ወዳድ መሆናቸው ደግሞ ለዛሬው የእንቁ የሙያ መንገድን የጠረገም ነበር።

በመዋለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ሲከታተል ቢቆይም አባቱ መቶ አለቃ ሙሉጌታ በደርግ የአውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው ወደ ጎጃም (ደብረ ማርቆስ) ተሹመው በመሄዳቸው ምክንያት ቤተሰቡ አዲስ አበባን ለመልቀቅ ተገደደ። እንቁም የአዲስ አበባን የከተማ ኑሮ ከሁለት ወንድሞቹ ጋር ሆኖ ተሰናበተ።

ባለታሪካችን ‹‹ከዘመናዊው የመዋለ ሕፃናት ትምህርት ወደ ቄስ ትምህርት ቤት ገባሁ›› ይላል በወቅቱ የሕይወት አቅጣጫው የተቀየረበትን አጋጣሚ ሲያስረዳ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያውያንን አብሮነት፣ ፍቅርና መተሳሰብ በገጠሪቱ ክፍል የተማረበትና ልዩ ስብዕናን የገነባበት እንደነበር ይናገራል።

በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኘው ንጉስ ተክለሀይማኖት አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እውቀት ለማስታጠቅ የተቀበለው ነበር። በአዲስ አበባ ያገኘው እውቀት ቋንቋ ላይ እንዲጎብዝ ሲያግዘው፤ በጎጃም ከተማረው የቄስ ትምህርት ጋር ተዳብሎ ጠንካራውን፣ ትምህርት ወዳዱን እንቁ ፈጠሩ።

### የስብዕና ግንባታ

እንቁ ዛሬም ድረስ ለተሰማራበት ሙያው ወዳድነት መሰረት የሆነው እና ስነ ምግባሩን በመልካም የቀረፀው የልጅነት አስተዳደጉ ነው። በግዜው ከመምህራኖቹ ከቤተሰቦቹ ልዩ ድጋፍ ማግኘቱ በእጅጉ እረድቶታል። በተለይ ኢትዮጵያዊ እሴት እና ባሕሉን በሚያከብር ማሕበረሰብ መካከል የመኖር እድል ማግኘቱ አስቸጋሪ የሕይወት አጋጣሚዎችን እንዲቋቋም አድርጎ ቀርፆታል።

በጊዜው በደርግ መንግሥት ምክንያት በኢትዮጵያ የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ስላልነበር ገና በልጅነቱ ነበር አባቱን በሞት የተነጠቀው። ይህ አጋጣሚ የእንቁ የልጅነት የፈተና ወቅት ነበር። መንግሥት እራሱ የሾማቸውን አባቱን ወደ እስርቤት አስገብቶ ለሞት ከዳረጋቸው ወዲህ ለአጭር ወቅትም ቢሆን የልጅነት ጊዜውን አዋክቦታል። አጋጣሚው የባሕሪ ለውጥ ከማምጣት አንስቶ ትኩረቱን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ለመውሰድ ታግሎት ነበር። ነገር ግን የእናቱ፣ የዘመዶቹ እንዲሁም የአካባቢው ማሕበረሰብ ጠንካራ ክትትል የማይሰበረውን እንቁ ሰርተው በትምህርቱ እና በባሕሪው ጠንካራ የሆነውን ማንነቱን ገነቡ። ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አንስቶ ዩኒቨርሲቲ አስኪገባ ድረስም በቀለም ትምህርት ከፍተኛ ውጤት የሚያመጣ ልጅ ሆነ።

### የሕይወት ዝንባሌ

እንቁ ለቀለም ትምህርት ካለው ዝንባሌ ውጪ በሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ነበር። ገና በ14 ዓመቱ በወቅቱ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለምን ተከትሎ ከውጪ ወደ አገር ውስጥ በሚተላለፉ የሞስኮ ራዲዮ (የአማርኛ ድምፅ ዲፓርትመንት)፣ የምስራቅ ጀርመንና የቡልጋሪያ ስርጭቶች ላይ በንቃት ይሳተፍ ነበር። ርዕዮተ ዓለሙን የተመለከተ ፅሁፎችን በመፃፍ ይላላክ ነበር። በተሳትፎው የትምህርት እድሎችን (በእድሜው ማነስ ምክንያት ባይሳካም)፣ የሌኒን ዓርማ ያለው ባጅ እና ሌሎች ሽልማቶቸን ያሸንፍ ነበር።

እንግዳችን የሆነው የዛሬው የስነ ምድር እና ቱሪዝም ባለሙያ በታዳጊነት ዘመኑ ለየት ያለ ዝንባሌም ነበረው። ይህ ፍላጎት ለተፈጥሮ ያለው ልዩ ተመስጦና ቁርኝት ነበር። ከታዳጊነቱ ጀምሮ የተለያየ ቀለማት ያላቸው አፈሮችን አመጣጥ፣ አፈጣጠር ለማወቅ ጥረት ያደርግ ነበር። ከዚያም ባለፈ ራቅ ወዳለው ወደ አያቶቹ መንደር ሲያቀና በተራሮችና ጉብታዎች ላይ የሚያስተውላቸው በየዘመን የተፈጠሩ የአፈር አይነቶችንና አቀማመጣቸውን ይመለከት ነበር፤ በፌስታል ለናሙና በመውሰድ የአፈጣጠር ሚስጢራቸውን ለማወቅ ጥረት ያደርገ እንደነበር ያስታውሳል።

‹‹በምኖርበት አካባቢ ከነበረው ከባሕሉ፣ ከኑሮ ዘይቤና እሴቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ነበረኝ›› የሚለው እንቁ ሙሉጌታ፤ ይህ ተፈጥሮና ሕዝብ ላይ ልዩ ዝንባሌን እንዲያዳብር መሰረት እንደሆነው ይገልፃል። አሁንም ያልተለየውን ጥብቅ የተፈጥሮና የመልከዓ ምድር ወዳጅነት በጠንካራ መሰረት ላይ የታነፀውም በያኔው የልጅነት ዘመኑ ነው። አስተዳደጉ ዛሬም የሚመነዝረው የእውቀት፣ የስነ ምግባርና የማሕበራዊ እሴት ዝንባሌን አጎናፅፎታል።

### ከፍተኛ ትምህርት

መምህራን እንቁን ጨምሮ ሁሉንም ተማሪዎች እንደ ልጆቻቸው የሚመለከቱ ትጉህ ነበሩ። በጊዜው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ከባድ ጥረትና እውቀትን ይጠይቅ ነበር። ይህንን ጉብዝና እንዲያገኙ አስተማሪዎች ከ8ተኛ ክፍል ጀምሮ ክትትልና ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር። በዚህ ምክንያት እንቁ ከራሱ ጥረት ጋር ተዳምሮ ለዩኒቨርሲቲ የሚያበቃ ነጥብ አመጣ። ውጤቱ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መራው።

አዲስ አበባ ገና በልጅነቱ ጥሏት ወደ ጎጃም ቢያቀናም ቂም የያዘችበት አትመስልም። ለትምህርት ተመራጭ የሆነው ዩኒቨርሲቲ ሳያቅማማ ነበር እንቁን የተቀበለው። እርሱም ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ልጅነት ከተማው በመግባት የስነ ምድር (Geology) ጥናት ትምህርት ክፍልን ተቀላቀለ። ይሄኔ ነበር በልጅነቱ የነበረው የአፈረና የመልከዓ ምድር አፈጣጠር የማወቅ ጉጉት በሳይንሳዊ እውቀት የተደገፈውና እውን የሆነው። ‹‹ልጅህን በሄድክበት መንገድ ምራው ይከተልሃል›› የሚለው አባባል ለቤተሰቦቹና እንደራሳቸው ልጅ ቆጥረው ላሳደጉት ነዋሪዎች በተግባር የተገለጠ ነበር።

በ1982 ዓ.ም ጀምሮ የስነ ምድር ጥናት ትምህር ክፍልን የተቀላቀለው የዛሬው የሕይወት ገፅታ እንግዳችን ለአራት ዓመታት በፍላጎት የመረጠውን ትምህርት በውጤታማነት ተከታትሏል። ይሁን እንጂ የወቅቱ የፖለቲካ ትኩሳት፣ የተማሪዎች አመፅና አለመረጋጋት ቆይታውን አልጋ በአልጋ አላደረጉትም። በጊዜው የኢሕአዴግ መንግሥት (የለውጥ ስርዓት መምህራን ለምን ተባረሩ በሚል ተቃውመሀል በሚል) ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለሶስት ወራት አስሮት ነበር። ይህ ጊዜ ፖለቲካን ይበልጥ እንዲርቅና ወደሚወደው የስነ ምድር ጥናት ትኩረት እንዲያደርግ ሌላ ገፊ ምክንያት ሆነው።

በከፍተኛ ትምህርት ቆይታው ሙሉ ትኩረቱን የስነ ምድር ጥናት ላይ አድርጎ በልጅነት አዕምሮ ለሚያነሳቸው ሀሳቦችና ጥያቄዎች ምላሽ ያገኝ ነበር። ትምህርቱም ይበልጥ ሙያውን እንዲወደው እና የሕይወት መንገዱን በዚያው ዙሪያ እንዲቀይስ በር የከፈተለት ነበር።

እንቁ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጨረሻው ዓመት ሲደርስ በተጨማሪነት ከቀድሞው ሲቲቲአይ ከአሁኑ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት በቱር ኦፕሬተርነት በዲፕሎማ ተመረቀ። ከዋናው ትምህርቱ ጋር እንዳይጋጭ መምህራኑ ከኢንስቲቱዩቱ ጋር በመነጋገር ትልቅ ድጋፍ አድርገውለታል። በስነ ምድር ጥናትና በቱር ኦፕሬተር ባለሙያነት መመረቁ ዛሬ ላይ ያልተጠበቀ የሙያ ግጥምጥሞሽና ጥምረት እንዲፈጠርም ምክንያት ሆነ። መልክ እየያዘ የመጣው የልጅነት ሕልሙ የሁለት ሙያ ባለቤቶች አድርጎት ወደ ስራ ሕይወት እንዲገባ መንገዱን ጠረገለት። በባሕል፣ እሴት፣ በሃይማኖት፣ በጠንካራ ስነ ምግባር የታነፀው እንቁ አገርን በእውቀቱ ለማገልገል የሚያስችል አቅምን ገነባ።

### እውቀትን ወደ ተግባር

የእንቁ ሙሉጌታ የዓመታት ትልም እውን ሊሆን ግዜው ፈቀደ። በትምህርት የታገዘው የስነ ምድር ጥናትና የቱር ኦፕሬተር ሙያ መሬት የሚነካበት አጋጣሚ ተፈጠረ። ፅንሰ ሀሳብን እና ሙያዊ እውቀትን ለማሕበረሰብ ሁለንተናዊ እድገት የማዋል ግዴታ በወጣቱ የስነ ምድር ተመራማሪ ላይ ወደቀ። ለታመነለት ሙያ ሙሉ ግዜውን ለመስጠት ያላቅማማው እንግዳችን ለጥቂት ወራት ስራ ለመቀጠር አማትሮ በመጨረሻም ማገሬያውን አገኘ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በውጪ ንግድ እረዳትነት በጀነራል ታፈሰ አያሌው (የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስራ አስኪያጅ የነበሩ) አማካኝነት ተቀጠረ። እርሳቸው የአገር ውስጥ ወኪል ሆነው ይሰሩበት ለነበረው ‹‹ሊፍት ኤር›› የተባለ አስጎብኚ ድርጅትም (የስነ ምድር ጥናት የሚያደርግ ካምፓኒን የሚያካትት ነበር) የመስራት አጋጣሚው ተፈጠረ። በዚህ ግዜ ጎብኚዎችን ወደ መስህብ ስፍራዎች ከመውሰድ አንስቶ በማዕድን ምርምር ላይ በአስተባባሪነት የመስራትን እድል በአንድ ግዜ ማግኘት ቻለ። ከዚያን ግዜ አንስቶ እንቁና የዓለም መልከዓ ምድር ጥብቅ ወዳጅነት ፈጠሩ። የኢትዮጵያን የመስህብ ስፍራዎች ጨምሮ የከርሰ ምድር ሀብት የሚገኝባቸው ጓዳ ጎድጓዳዎች ጋር ተዋወቀ።

### የእንቁ መዳረሻ - ቱሪዝምና ስነ ምድር

በ1988 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የገባውና ‹‹ሀንት አይል›› በሚል ስያሜ የሚታወቅ ነዳጅ አፈላላጊ ካምፓኒ አስተባባሪ ሆኖ መስራት ጀመረ። የስነ ምድር ጥናት ባለሙያ መሆኑ ማዕድን ላይ እንዲሳተፍ ሲያደርገው ቱር ኦፕሬተር መማሩ ደግሞ ሎጅስቲኩንም ደርቦ እንዲይዝ ያስመረጠው ነበር። በዚህ ምክንያት በስራው የረጅም ዓመት ልምድ ባይኖረውም በአለቆቹ ወዲያው ነበር አመኔታን ያገኘው።

እንቁ ከበርካታ የውጪ አገር ዜጎች ጋር መስራት ጀመረ። ከካናዳ፣ ከአውስትራሊያ፣ ከእንግሊዝ አገር የሚመጡ በርካታ ካምፓኒዎችም ጋር የመስራት ልምድ አዳበረ። በሶማሌ ጠረፍ ዶሎ መና (ቦረና አካባቢ) በሚደረግ የነዳጅ ፍለጋ ከተሰማሩ 67 የውጪ አገር ዜጎች ጋር የነበረው ቆይታ ይጠቀሳል። እርሱ የካምፓኒው ሰራተኞች የእለት ተእለት የሎጅስቲክ ፍላጎት ከማሟላት አንስቶ አስፈላጊ የሚባሉ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ ኃላፊነት ነበረበት።

‹‹በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ለውጥ ምክንያት አገሪቱ በሁሉም መስክ ክፈት የሆነችበት ነበር›› የሚለው እንግዳችን እንቁ ሙሉጌታ፤ በጊዜው ሁለት ሙያ ይዞ መገኘት ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኝና የስራ እድል የሚከፍት እንደነበር ይናገራል። አጋጣሚው ከማዕድን ፍለጋና ስነ ምድር ጥናት ባሻገር ከውጪ አገር ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ቱሪስቶችን ወደ ልዩ ልዩ መዳረሻዎች (የመስህብ ቦታዎች) በመውሰድ የማስጎብኘት ልምድ በተደራቢነት እንዲሰራ አስችሎታል። የኢትዮጵያን ጓዳ ጎድጓዳ እንዲያውቅና ሀብቶቿን አብጠርጥሮ እንዲለይ ትልቅ እድል የፈጠረለትም ነበር። ከኢትዮጵያ ባሻገር የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የካምፓኒውን ኃላፊነት ተቀብሎም ሰርቷል።

የስነ ምድር ጥናት ድንበር የለውም የሚል እምነት አለው። የተማረው የስነ ምድር ጥናትም ይህንን ፍሬ ነገር ያስቀምጣል። በዚህ ምክንያት እንቁ በሙያው ለማገልገል በበርካታ የአገር ውስጥና የውጪ አገራት መልከዓ ምድሮችን አካልሏል። ከእነዚህ መካከል፣ አገረ ማሪያም በወለጋ ጊምቢ አካባቢ (በቱሉ ካፒና ቱሉ ዲምቱ በወርቅና በፕላቲኒየም ጥናት)፣ በኤርትራ ከረን፣ ጅቡቲ፣ ኬኒያ፣ ታንዛኒያና ሌሎች አገሮችን ይገኙበታል። ሙያው ፖለቲካዊ ከሆነ ፅንሰ ሀሳብ ውጪ ምድር ድንበር እንደሌላት እንዲረዳ ምክንያት ሆኖታል፤ ከማህበረሰብ እሴት ጋር ተዋድዶ፣ ከባህል ተስማምቶ፣ የሰው ልጆችን አብሮ የመኖር እሳቤ ተረድቶ መኖርን በጥልቅ የተማረበት አጋጣሚ ፈጥሮለታል።

በዚህም በካናዳ ኩባንያ (በጀማሪ የስነምድር ባለሙያ እና በመስክ ካምፕ አስተዳዳሪነት)፣ በወለጋና ጉጂ ዞኖች የወርቅ እና ፕላቲኒየም ምርመራ ስራዎች ላይ፣ ሻኪሶ በሚድሮክ የማዕድን ኩባንያ ውስጥ ለገደንቢ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# የዕንቁ መንገድ- ...

ከገጽ 6 የዞረ

የወርቅ ስራ ቡድን መሪ፣ በቡሌ ሆራ የኢትዮ ዱባይ የወርቅ ፍለጋ ድርጅት ውስጥ የፕሮጀክት ኃላፊ በመሆን እስከ ቁፋሮ የሚደርስ የማዕድን ስራ አብቅቷል።

የእንቁ መንገድ በስነ ምድር ጥናት ላይ ብቻ የተገደበ አልነበረም። ሙያው የፈጠረለት አጋጣሚ ከኢትዮጵያ የመስህብ ሀብቶች፣ የተፈጥሮ ፀጋዎች፣ ባሕልና ታሪክ ጋር ሳያስበው አቆራኝቶታል። በተማሪ ቤት ቆይታው ቱሪዝምን እንደ አንድ ሙያ መማሩ ደግሞ ልምዱን ከእውቀት ጋር አስተሳስሮለታል። በዚህ ምክንያት ከተለያዩ አስጎብኚ ድርጅት ካላቸው (ጓደኞቹ) ጋር ይሰራ ጀመር። ከስነ ምድር ጥናት መስክ ስራ በሚመለስባቸው ማንኛውም አጋጣሚዎች የውጪ አገር ቱሪስቶችን ወደ መዳረሻዎች በመውሰድ ያስጎበኛል።

ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርትነት ወዲህ የማዕድን ኩባንያዎች ስራቸውን አቋርጠው ነበር። በዚህ ምክንያት ለሁለት ዓመት አካባቢም እንቁ አስቸጋሪ ጊዜያትን አሳልፏል። በ1994 ግን ሚድሮክ ኢትዮጵያ ሲቋቋም «ማይን ጂኦሎጂስት» ሆኖ ለሶስት ዓመት በሻኪሶ፣ ክብረ መንግስት እና ሌሎች አካባቢዎች ላይ በመዘዋወር አገልግሏል። ከዚህ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ወደ ቱሪዝሙ በመግባት አዲስ አቅጣጫን አበጀ።

ይህ አጋጣሚ የኢትዮጵያን ሀብቶች (በቱሪዝም ዘርፍ) አብጠርጥሮ እንዲያውቅና ሌላ የሕይወት ልምድ እንዲያዳብር አገዘው። በግዜው አክሱም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር፣ ባሕርዳር፣ የቀድሞው ደቡብ ክልል የሚገኙ መስህቦች፣ የኦሮሚያ፣ ሐረሪና ሌሎችም አካባቢዎች የሚገኙ የተፈጥሮ፣ የባሕል እንዲሁም የታሪክ ስፍራዎች ላይ የውጪ ዜጎችን ይወስድ ነበር።

### ጂኦ-ቱሪዝም

ግዜው በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2005 አካባቢ ነው። እንቁ የጂኦ-ቱሪዝም ፅንሰ ሀሳብን ለማስተዋወቅ ጥረት ያደርግበት የነበረበት ወቅት፤ የስነ ምድር ጥናት የመስክ ስራውንና አስጎብኚነቱን አጠንክሮ የያዘበት አጋጣሚ። በግዜው ሀሳብ በውስጡ በተደጋጋሚ ይመላለስ ነበር። ይህንን ጉዳይ ከውጪ ከሚመጡ በርካታ ቱሪስቶች ጋርም በጨዋታ መልክ አውግቶት ያውቃል። ጉዳዩ በአገራችን ቱሪዝም ውስጥ ያልተለመደም ነበር። የኢትዮጵያን መልከዓ ምድር የሚጎበኙ ቱሪስቶች ከእንቁ ጋር ሲገናኙ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የመልከዓ ምድሩን ሁናቴና ሌሎች የጂኦሎጂ ባለሙያ የሚመልሳቸው ጥያቄዎችን ያነሱ ነበር። ይህን ጊዜ ነበር ከትምህርት፣ ንባብ እና የረጅም ዓመት የስራ ልምድ ያዳበረውን ሙያ ለማጣመር የወደደው።

የጂኦ-ቱሪዝም ፅንሰ ሀሳብ በዓለማችን (እንደ ኢንዶኔዢያ፣ ሜክሲኮ፣ጣሊያን፣ አይስላንድ ያሉ አገራት) ላይ የቆየ ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን አልተለመደም ነበር። ይህንን እሳቤ ነበር እንቁ በኢትዮጵያ ለማስረፅ የፈለገው። የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆዎች፣ የስምጥ ሸለቆ ሀይቆችን (ዝዋይ፣ ላጋኖ፣ አብያታና ሻላ፣ ጫሞ አባያ) አስደናቂ መልከዓ ምድሮች ለሀሳቡ እጅግ ምቹ ነበሩ።

«ኢትዮጵያ ለጂኦ-ቱሪዝም የተመቸች አገር ነች» ይላል እንቁ ስለ ሁኔታው ሲያስረዳ። አፋርን እንደ ምሳሌ ያነሳል። ለዓመታት በአፋር ኤርታሌ፣ ዳሎል፣ ሀዳር (የሉሲ መገኛ) እና ሌሎች አካባቢዎች ቱሪስቶችን በመውሰድ የዓለማችንን ተወዳጅ ስፍራ ሲያስጎበኝ ቆይቷል። በኢትዮጵያ አስደናቂ ውበትና የተፈጥሮ ስጦታዎች የሚደነቁ ጎብኚዎችን ፈጥሯል። አገሪቱ አላት ብለን ከምናስበው በላይ በስነ ምድር ቅርስ፤ የጂኦ-ቱሪዝም የታደለች እንደሆነች ያውቃል። ይህንን እምቅ ሀብት ለዓለም ሕዝብ ገልጦ በማሳየት እንደ አይስላንድና ሜክሲኮ ታዋቂ አገር እንድትሆን ይመኛል። ለዚህም ይመስላል ረጅም ዓመታት ልምዱን አቀናጅቶ በዘርፉ ላይ በስፋት ለመስራት የወደደው።

### ጂኦ-ቱሪዝም እንደ መዳረሻ

እንቁ የአፋር ክልል ለስነ ምድር ቅርስ የተመቸች እንደሆነ ያምናል። እያንዳንዱ የአፋር ቀበሌ በዚህ ሀብት የተጥለቀለቀ መሆኑን ተረድቷል። ይህንን ሀብት ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ማስተዋወቅ ድርሻው እንደሆነ ይገለፃል። የአፋር ሕዝብ እና አገር ከዚህ ፀጋ ተጠቃሚ መሆን አለበት ይላል። ፀጋውን ወደሚጨበጥ ጥቅም ቀይሮ በጂኦ-ቱሪዝም ኢትዮጵያ የታወቀች እንድትሆን እየሰራ ይገኛል።



ሰው መክሊቱን ሲከተል በሙያው፣ ስነ ምግባርና ውጤትን አጣምሮ ሁለንተናዊ ስኬት ላይ እንደሚደርስ ያስረዳል

የእንቁን ሀሳብ የሚጋሩ ባልንጀሮችም በዚህ እሳቤ ውስጥ አብረውት እየሰሩ ነው። የኢትዮጵያን ስነ ምድር እና የመስህብ ሀብቶች በማስጎብኘት ስራ ላይ ተሰማርተዋል። ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታወቀው የጉብኝት እሳቤ በተጨማሪ ጂኦ-ቱሪዝምን እያስተዋወቁም ነው። በዚህ ምክንያት በአፋር ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት እየተገኘ ነው። ለዚህ የእንቁና ጓደኞቹ ድርሻ ላቅ ያለ ነው።

ኢትዮጵያ በስነ ምድር ቱሪዝም ሀብትነት ያላት አቅም በአፋርና ስምጥ ሸለቆ አካባቢን ብቻ እንደማይወሰን እንግዳችን ይናገራል። ለዚህ የሰሜን ተራሮች፣ የባሌ ተራሮች (ወደ 37 የሚጠጉ የመቻራ የዋሻ ስሪቶች) እና ሌሎች ሀብቶችም የዚሁ አካል እንደሆኑ ይገልፃል። ሀብቶቹ በድርብ የዓለም ቅርስነት ከአንድ ግዜ በላይ እውቅና እንዲሰጣቸው እየሰሩ መሆኑንም ያስረዳል። አትዮጵያ እነዚህን ሀብቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲቸራቸው መስራቷ ለቱሪስት ፍሰትና ለኢኮኖሚ እድገት በር ከፋች መሆኑን ነው እንቁ የሚያምነው።

### የእንቁ ስኬቶች

እንቁ የጂኦ-ቱሪዝም እሳቤንና የኢትዮጵያን ሀብቶች ለማስተዋወቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፔን ላንዛሮቲ ግዛት በተካሄደ ኮንግረንስ ላይ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርቧል። በዚህም ኢትዮጵያ ካሏት እምቅ የጂኦ-ቱሪዝም ሀብቶች መካከልም ስምጥ ሸለቆ እና አካባቢው፣ በስምጥ ሸለቆ ጠርዝ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መልከዓ ምድራዊ ገፅታዎች እና የአፋር ንቁ የእሳተ ገሞራ ውጤቶችን ጨምሮ የኢትዮጵያን የስነ ምድር ሀብቶች በጥናታዊ ፅሁፉ ላይ በማካተት አስተዋውቋል።

በተጨማሪ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ ሳይንስና ባሕል ድርጅት ግሎባል የጂኦ-ፓርክስ የሚባለው ክፍል ውስጥ የኢትዮጵያን የስነ ምድር ሀብቶች ለማስመዝገብ ከጓደኞቹ ጋር ቅድመ ሁኔታዎችን እና ዶክመንት ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

እንቁና ጓደኞቹ በኢትዮጵያ ቱሪዝም ውስጥ ጂኦ-ቱሪዝም በፖሊሲ ደረጃ እንዲካተት ሰፊ ጥረት አድርገው በመጨረሻም ተሳክቶላቸዋል። በቅርቡ የቱሪዝም ፖሊሲ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ሙሉ ለሙሉ ዘርፉ በፖሊሲው እንደሚደገፍ ይጠበቃል። ኢትዮጵያ በጂኦ-ቱሪዝም ሀብትና እና የተፈጥሮ ቅርስ የታደለች ሀገር ብትሆንም የሀብቷ ተጠቃሚ ሳትሆን ቀርታለች። ፖሊሲው ይህንን ታሪክ እንደሚቀይር ይጠበቃል።

የዛሬው የሕይወት ገጽታ እንግዳችን እንቁ ጂኦ-ቱሪዝም በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እየተጋ ይገኛል። ይህንን ከግብ ለማድረስ የተለያዩ አደረጃጀቶች ውስጥ በመግባት እየሰራ ነው። ስልጠናዎችንም ይሰጣል። አብሮ ከሚሰራባቸው ድርጅቶች ውስጥ ቮልካኖ ዲስከቨሪ የስነ-ምድርና ንቁ ምድሮችን የሚመረምር ኩባንያ በኢትዮጵያ አስተባባሪ እና ቡድን መሪ፣ የአፍሪካ ቮልካኖሎጂስቶች ማሕበር ፀሀፊ፣ የሕንድ የስነ ምድር ተመራማሪዎች ቡድን በኢትዮጵያ አስተባባሪ፣ የታላቅ ኢትዮጵያ አስጎብኚ ድርጅቶች ማሕበር ምክትል ሊቀመንበር እና በዓለም ትታይ ኢትዮጵያ አስጎብኚ ድርጅት መስራችና ሥራ አስኪያጅ ነው።

በቱሪዝም ዘርፉ ላለፉት 30 ዓመታት በተለይ የአፋር ኤርታሌና ዳሎል የጂኢ-ቱሪዝም ሀብትን እንዲተዋወቅ ላበረከተው አስተዋፆ መቀመጫውን በአሜሪካ ዳላስ ቴክሳስ ያደረገው «አርአያ ሰው ሽልማት» አሸናፊ ሆኗል።

እንቁ ዛሬም ለቆመለት ሙያ እስከመጨረሻው ፀንቶ ለመስራት ለራሱ ቃል ገብቷል። በኢትዮጵያ የሚገኙ ማራኪ የስነ ምድር ሀብቶች ወደ ጂኦ-ፓርክነት እንዲቀየሩ፤ ዓለም እንዲጎበኛቸው ለማድረግ የስራ ዘመን ልምዱን ተጠቅሞ ውጤት ለማምጣት እየተጋ ነው። ሀብቱ እያለ እንደ አገር ተጠቃሚ አለመሆናችን ያስቆጨዋል። ይህ እርሱ ሊያመጣ ላሰበው መነቃቃት ገፊ ምክንያት ነው። ከተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር አብሮ በመስራት የኢትዮጵያ ጂኦ-ቱሪዝም ፀጋ ቦታ እንዲኖረውና እንዲታወቅ፤ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ሀገራችን እና ሕዝቦቿ ተቋዳሽ እንዲሆኑ እየሰራ ይገኛል። በኢትዮጵያ የስነ ምድር ታሪክና አወቃቀር፤ እንዲሁም የስነ ምድር ቅርስና የሚገኙበትንም ዝርዝር መረጃ የያዘ መፅሀፍ በአማርኛ ቋንቋ እንዲሁም በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚተረጎም እያዘጋጀ ይገኛል።

### ትውልዱ እንዲነቃ

«ትውልዱ አቋራጭ መንገድ አይውደድ» ይላል እንቁ፤ በዚህ መንገድ የሚገኝ አንዳችም ስኬት እንደሌለ በእርገጠኝነት እየተናገረ። ንባብን ባሕል ማድረግ እንዲሁ ከሕልማቸው ዳርቻ እንደሚያደርሳቸው ይገልፃል። እርሱ ላለፉት 30 ዓመታት ንባብን ባሕል ማድረጉና አዲስ ነገር ለማወቅ ጉጉት በራሱ ላይ ማሳደሩ ለሙያው ወዳድነት መሰረት እንደሆነው ይገልፃል። ዛሬም ድረስ ይህንን ልምዱን በመቀጠሉ ብዙ እውቀቶች እየገበየ ለመሆኑ በማስረጃነት ይጠቅሳል። ከማንበብም ባሻገር ኢትዮጵያ አስደናቂ የስነ ምድር ባለቤት እንደሆነች በመግለፅ ትውልዱ የአገሪቱን የተፈጥሮ ስጦታዎች ቦታው ድረስ በመሄድና በመጎብኘት እንዲያውቅ ይመክራል።

ትውልዱ ለመረጠው ሙያ ፍቅር ሊኖረው እንደሚገባም ይናገራል። ሰው መክሊቱን ሲከተል በሙያው፣ ስነ ምግባርና ውጤትን አጣምሮ ሁለንተናዊ ስኬት ላይ እንደሚደርስ ያስረዳል። ፖለቲከኛው ፖለቲካውን፣ የስነ ምድር ተመራማሪው እንዲሁ በሙያው ላይ ብቻ ማተኮር እንደሚገባ ይመክራል። «እድሜ ልክ አንኖረም» የሚለው እንቁ የተሰጠንን እድሜ በአግባቡ ተጠቅመን ለተፈጠርንበት ሙያና ዓላማ አውለን ለኢትዮጵያ ቁምነገር ልንሰራ እንደሚገባ ይገልፃል።

እንግዳችን እንቁ ሙሉጌታ ቤተሰብ መስርቶ የሶስት ልጆች አባት ሆኗል። ሴት ልጁ ሜራ እንቁ የአባቷን ፈለግ ተከትላ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ እየሰራች ነው። ወደ ማራኪ ስፍራዎች የእግር ጉዞ (ሀይኪንክ) በማዘጋጀትና የማሕበሩ ፀሀፊ በመሆን ትሰራለች። ሁለት ወንድ ልጆቹም እንዲሁ አርዓያውን ተከትለው በተሰማሩበት የሙያ ዘርፍ ላይ እየተጉ ነው። መኖሪያ ቤቱን በኢትዮጵያ ባሕል፣ እሴትና ኢትዮጵያዊነት በሚገልፁ ጌጣ ጌጦች ያስውባል። ይህ ልምዱ ለልጆቹ የእርሱን ፈለግ መከተል፤ ሀገርን ለመውደድ ምክንያት ከመሆን ባሻገር ለበርካታ ዓመታት ለኖረበት ሙያ መታመኑን የሚያንፀባርቅ ምስክር ነው። ለዚህ ነው ወላጆች ልጆቻቸው ኢትዮጵያዊነትን፣ የማሕበረሰብ ባህልን፣ እሴቶችና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን በማስተዋወቅ ትውልዱ እንዲነቃ የድርሻቸውን ይወጡ የሚል ምክር በንግግሩ መቋጫ ላይ ያነሳው።

## ልዩ የምርመራ ዘገባ

# የሪል ስቴቱ ውስጣ ውስጥ ሲፈተሽ!

(በመልካም አስተዳደርና የምርመራ ዘገባ ቡድን)



### ክፍል ሁለት

### በአማላይ ማስታወቂያዎች የተሸፈኑ የማይፈጸሙ ውሎች እና የዜጎች እንባ

በክፍል አንድ ጽሑፋችን፣ “ የሪል ስቴቱ ውስጣ ውስጥ ሲፈተሽ! “ በሚል ርዕስ፤ የሪል ስቴትን ምንነት፣ የሀገራት ተሞክሮ እና በኢትዮጵያ ያለውን ገጽታ ለማመላከት ተሞክሯል። የሪል ስቴት ዘርፉ በኢትዮጵያ እንዲተገበር ሲደረግ ምንም አይነት የሕግ ማዕቀፍ እንዳልተዘጋጀለት፤ የአሰራር ሥርዓት እንዳልተበጀለት፤ እገሌ የሚባል ተቋም ይምራው ተብሎ እንኳን ባለቤት እንዳልተሰጠው ያመላከተ ዘገባ አቅርበናል።

በዘገባችን ምንም እንኳን የሪል ስቴት ዘርፍ የቤት አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ አስተዋጽኦ እያበረከተ ቢሆንም ዘርፉ ብዙ ችግሮችን እያስከተለ መሆኑን፤ በተለይም ለዜጎች እንግልትና ብዝበዛ፣ ለጥቂቶች ደግሞ የመክበሪያና በአቋራጭ መበልጸጊያ ሰፊ ሜዳ ሆኖ መከሰቱን ጠቁመናል።

ለመሬት ወረራ፣ ለከተሞች ፕላንና ገጽታ መበላሸት፣ ሰፊ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከዚህም አለፍ ያሉ ሥነልቡናዊ ችግሮችን እያስከተለ፤ ከፍ ሲልም ለካፒታል ገበያው ትልቅ ፈተና ስለመሆኑ በመጠቆም፤ ችግሮቹን በቀጣይ ክፍሎች በዝርዝር እንደምናስነብብ ቃል ገብተን ነበር። እነሆ ዛሬ በቃላችን መሰረት የችግሩ አንድ ማሳያ የሆነውን፤ ክፍል ሁለትን አሰናድተናል።

“የባንክ ብድር ተመቻችቷል፤...”፣ “...ኑሮ ቀለል ይላል፤”፣... “ምቾት ስጋ ለብሶ ቅንጡ ቤት ውስጥ ነዎት፣...”፣ እና ከመሰል የማስታወቂያ ማስዋቢያ ሀረጎች በስተጀርባ የሚነገሩ የማይጨበጡ ጉም ቃላት፣ ብዙ ቤት ፈላጊዎችን ተስፋ አልባ አድርገዋል። ምክንያቱም፣ በእነዚህ ቃላት ተከሽነው አምረውና ተውበው የቤት ፈላጊዎችን ቀልብ ገዝተው የሚቀርቡ ማስታወቂያዎች፣ የሪል ስቴት ዘርፉ በማይፈጸም እና በሳቢ ማስታወቂያዎች ማኅበረሰቡን በማማለል ልባቸውን የሚያሸንፉበት፤ በደካማ ጎናቸው ገብተውም የቤት ባለቤት እንሆናለን ብለው የቆጠቡትን አንጡራ ሀብት የሚበዘበዙበት፤ ሕይወታቸውንም ለከፋ ችግር የሚዳረጉበት ስልትና መንገድ እንደሆነ የሚታየው እውነት ይመሰክራል።

ከላይ ለአብነት የተጠቀሱት የማግባቢያ ቃላቶች አንድ አዝማሪ፣ ‹‹የወለዱት ባይሞት ያመኑት ባይከዳ፣ አባይ ቁልቁለቱ ይሆን ነበር ሜዳ...›› ሲል ያዜመውን ያስታውሱናል። መተማመን ቢኖር በአማላይና ሳቢ ቃላት የተዋቡ የቤት ማስታወቂያዎች ቤት ፈላጊዎችን ባለቤት ባደረጉ፤ ሰው የሚወደውን ባላጣ እና ውጣ ውረዱ፤ አስቸጋሪውና የማይቻል የሚመስለው ሁኔታ ሁሉ ቀላልና ቀና እደሚሆን ያሳየበት ነው። በማር ተለውሰው የቀረቡ ማስታወቂያዎች ታምነው ቤት ቢሆኑ መሠረታዊ የሆነውን የቤት እጦት ችግር በማቃለል አስተዋጽኦው ከፍተኛ በሆነ ነበር። ዳሩ ግን ችግሩን ከማቅለል ይልቅ የብዙዎችን ተስፋ ከማጨለም ባሻገር ለእንግልት ዳርጓቸዋል።

ገቢ ማግኘትን ብቻ ታሳቢ ያደረጉ የሪል ስቴት ማስታወቂያዎች ሰፊ ችግር የተስተዋለባቸው ናቸው። በዚህ መልኩ በዘርፉ በተከሰቱ ችግሮች ቤት ይኖረናል ብለው ተስፋ ይዘው ተስፋቸው ከንቱ እንዲሆን ከሆነባቸው ተጠቂዎች መካከል ወይዘሮ ሳራ ዮሃንስ (ስማቸው ለዚህ ጽሑፍ ሲባል የተቀየረ) አንዷ ናቸው።

ወይዘሮዋ፣ ነዋሪነታቸው እዚሁ አዲስ አበባ ሲሆን፤ የቤት ባለቤት የመሆን ትልቅ ሕልማቸውን ለማሳካት በማስታወቂያ በተነገራቸው መረጃ መሰረት ወደ አንድ ታዋቂ ሪል ስቴት ጎራ ይላሉ። ሪል እስቴቱም ቤት ለመገንባት የሚያስችለውን ሁሉ መስፈርት እንዳሟላ እና ቤት ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች ተገቢውን ክፍያ ሲከፍሉ ገንብቶ እንደሚያስረክብ ተስፋ በመስጠት፤ በሽያጭ ባለሙያዎች በኩል ክፍያውን እንዲፈጽሙ ያግባቧቸዋል፤ ያሳምኗቸዋልም።

ወይዘሮ ሳራ፣ ብቸገር እሸጠዋለው፤ ዕድሜዬ ሲገፋም እጦርበታለው፤ እኔ ሳልፍ ደግሞ ለልጅ ልጆቼና ለቤተሰቦቼ ቅርስ ይሆናል በማለት ካለቻቸው ጥሪት ላይ ቤት ለመግዛት በቅርብ ጓደኞቻቸው አማካኝነት አክሲዮን ገዙ። በዚሁ መሰረት 20 በመቶ የሚሆነውን ከፍለው ቀሪውን በየወሩ 38 ሺህ ብር እየከፈሉ ቤታቸው መጠባበቅ ጀመሩ። እንደ ወይዘሮ ሳራ ሁሉ የቤት የባለቤትነት ተስፋን የሰነቁ ሌሎች 27 ሰዎችም ከቤት ሻጭ ሪል እስቴቱ ጋር ውል ተዋውለው የሁልጊዜ ምኞታቸው የሆነውን ቤት ለመረከብ በተስፋ ይጠባበቁ ያዙ።

ስለ ጉዳዩ ያስረዱን እነዚህ የቤት ተስፈኞች እንደሚሉት፤ አብዛኛዎቹ ሰዎች በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ማስታወቂያ እንዳዩና አክሲዮን እንደገዙ ይናገራሉ። ሪል እስቴቱም ለገዥዎች በሰጠው ተስፋ መሰረት እና ከቤት ፈላጊዎች በሰበሰበው ብር የተወሰነ ግንባታ ጀመረ። የግንባታው መጀመር ደግሞ ለገዢዎቹ የበለጠ ቤት የማግኘት ተስፋቸውን ከፍ አደረገው። ይሁን እና ቤቱ እያደገ እና ቤቱ ይደርሰናል ወደ ማለት ደረጃ ላይ ሲደርስ፤ ወይዘሮ ሳራን ጨምሮ ሌሎች ቤት ፈላጊዎችን ተስፋ ያስቆረጠ የቤት ሕልማቸው ያደረቀ ነገር አጋጠማቸው።

“ግንባታው ከተጀመረ በኋላ፣ የከፈሉበትና በገንዘባቸው እየተሠራ ያለውን ቤት ሪል እስቴቱ ለሌላ ሪል እስቴት በውል እና ማስረጃ ተዋውሎ ሸጠው።” ይህ ደግሞ የቤት ባለቤት እንሆናለን ብለው የሰነቁትን ሕልም የነጠቀ አጋጣሚ መሆኑን ነው ባለጉዳዮቹ የሚያስረዱት። ወይዘሮ ሳራ ስለጉዳዩ በቁጭት ሲያስረዱ፤ ይሄ የሆነው እርሳቸውና እና ሌሎች 27 ቤት ፈላጊዎች የመጀመሪያ ገዥዎች ስለነበሩ እንዲሁም የቤቱ ግንባታ ያልተጠናቀቀ ስለነበር፤ የግዥ ውል የፈጸሙት በመንደር ውል ስለነበረ ነው።

ለዚህም ነው ግንባታው ተጀምሮ የይዞታ ማረጋገጫ ሲወጣለት ሪል እስቴቱ ጅምር ቤቶቹን ግንባታ ጨርሶ ለእነርሱ ከማስረከብ ይልቅ በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት በኩል ለሌላ ሪል ስቴት የሸጠው። በእነርሱ ገንዘብ የተሰራውን ቤት የገዛው ሌላኛው ሪል ስቴት ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ለሌሎች ቤት ለሚፈልጉ ሰዎች ሸጦታል። ይህ የሆነው ደግሞ ሪል እስቴትን የተመለከተ ሕግ ባለመኖሩ እንደማንኛውም ቤት ሽያጭ በውልና ማስረጃ መሸጥ የሚችልበት ክፍተት ስለነበር ነው።

እኚህን ባለጉዳይ ጨምሮ ሌሎች ለቤቶቹ የተዋዋሉ ሰዎች አይሆንም ብለው ጠይቀው ተቃውሞ ቢያቀርቡም ምንም ማድረግ ሳይችሉ እንደቀሩ የሚናገሩት ወይዘሮዋ፤ ክስተቱ ከገንዘባቸው አሊያም የዘወትር ሕልማቸው ከነበረው ቤት ሳይሆኑ እንዳስቀራቸው ይናገራሉ።

“እኔ ከሪል ስቴት ቤት ለመግዛት ያሰብኩት ውጣ ውረድ የሌለበት እና በቀላሉ ቤት ማግኘት የሚቻልበት መንገድ ነው ብዬ ስለተማመንኩኝ እና በተለይም በትልልቅ መገናኛ ብዙሃን የሚነገረው ማስታወቂያ አምኜ ነበር። ይሁን እና ያሰብኩት ሳይሆን ያላሰብኩት ነገር ነው የገጠመኝ” ሲሉም ነው ወይዘሮ ሳራ ብሶታቸውን የገለጹት።

ወይዘሮ ሳራ፣ የሪል ስቴት አልሚዎችን የማስታወቂያ ማስነገርና የሌሎችን ልብ የመግዛት አካሄድን፣ የውል አሰራርንና ሌሎች ጉዳዮችን ሲያስረዱም፤ የሪል ስቴት ዘርፉ በዋናነት የተወሰኑ ሰዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ሌሎች ተስበው በመግባት እዲከስሩ የሚደረግበት፤ ግለሰቦች ያለምንም የሕግ ልጓም ዜጎችን የሚበዘብዙበት መንገድ ነው ይሉታል።

ውሉን ከመዋዋላቸው በፊት የሽያጭ ባለሙያዎችን አናግረው፣ “በየወሩ የሠራተኛ ክፍያ ይጨምራል፤ ነገር ግን ቢጨመር በመቶ ብር የሚቆጠር ነው። ስለዚህ ሊደርስቦት የሚችለው ክፍያ በጣም ትንሽ ነው፤” የሚል የማታለያ ማብራሪያ በመጠቀም የሽያጭ ባለሙያዎች እንደነገሯቸውና ትንሽ ብር ከሆነ አይጎዳም በማለት በሀሳቡ ተስማምተው ውሉን መፈረማቸውን ነው ወይዘሮዋ የሚያስረዱት።

ለመሆኑ የሪል ስቴት ዘርፉ እንደ ሀገር ለምን በአሳሳች ማስታወቂያዎች፣ ማብራሪያዎችና በማይፈጸሙ ውሎች ታጅቦ የዜጎች መበዝበዣ መስክ ሆነ የሚለውን በተመለከተ፤ የተለያዩ ባለሙያዎች የየራሳቸውን አስተያየትና ብያኔ ይሰጣሉ። ኢንጂነር ደሳለኝ ከበደ፣ የ“ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ግብይት” የተሰኘ መጽሐፍ ደራሲ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፣ ዘርፉ በትክልል ቢመራና ቁጥጥር ቢደረግበት የቤት ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር መንግስት በዘርፉ ማግኘት የሚገባው ገቢ በትክክል እንዲሰበስብ ያስችለው ነበር። ነገር ግን ይህ ባለመሆኑ ምክንያት መንግስት ከፍተኛ ገቢ ከማጣቱም ባሻገር፣ ዘርፉ ሀይ ባይ አጥቶ ቤት እናገኛለን ብለው አክሲዮን የገዙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እንዲበዘበዙ እያደረገ ነው ይላሉ ።

በኢትዮ-አሊያንስ አድቮኬሲ ማኅበር የሕግ ባለሙያ የሆኑት አቶ ቃለ-እግዚሐብሔር ጎሳዬ እንደሚያስረዱት፤ ዘርፉ በአግባቡ ሕግ ወጥቶለት ባለመመራቱ በማስታወቂያዎች እየተታለሉ የቤት አክሲዮን የገዙ ዜጎች ያሰቡት ቤት ደብዛው ጠፍቶ ቀርቷል። ዘርፉ ትርፋማ እና ብዙ ገንዘብ የሚገኝበት ነው። ሆኖም የዜጎች ተስፋ ከመሆን ይልቅ የሚጎዱበት እና ተስፋቸውን የሚያጡበት እየሆነ ከመጣ ከርሟል። በመደበኛው የሚዲያ ተቋም ሳይቀር ማስታወቂያ ሰምተው የሚጭበረበሩበት፤ የሚበደሉበትና ለበደላቸውም ፍትህ የተነፈጉበት/ያጡበት ዘርፍ ነው።

በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ዳኛ በኃይሉ ተዋበ በበኩላቸው፤ ማጭበርበሩ ማስታወቂዎችን ከማስነገር እንደሚጀምር ተናግረው ጥንቃቄው ከዚህ መጀመር አለበት ይላሉ። ማስታወቂያዎች ሲሠሩና ሲነገሩ በእውነት ላይ የተመረኮዙ እና ተጨባጭ መሆን አለባቸው። ይሁንና በተግባር የሚታየው ግን የሌለን ነገር ያለ አስመስሎ ማስታወቂያ መስራትና ማስነገር ነው። ሕዝቡም በመንግስት ሚዲያዎች ማስታወቂያው መተላለፉን በማየት እነዚህ ሰዎች ያሉት እውነት ነው ብሎ ተቀብሎ ገንዘቡን ካወጣ በኋላ በማስታወቂያ የተነገረው ነገር ሳይሆን እየቀረና ዜጎች እየተበዘበዙ ነው።

በርካታ ሪል ስቴት አልሚዎች ማስታወቂያ የሚያስነግሩት የሕንጻ መሰረት እንኳን ሳይጥሉ ነው። ይሄንን የሚከታታልና የሚከለክል ደግሞ የለም። የሌለን ነገር አለ ብሎ መናገር ማጭበርበር ስለሆነ ጉዳዩ ከፍትሐ ብሔርም በተጨማሪ በወንጀልም የሚያስጠይቅ ነው።

ለምሳሌ የሌለውን መሬት ይህ ይዞታ የኔ ነው፤ ቤት ገንብቼበት ልሸጥ ነው ብሎ ሰዎችን አታልሎ ገንዘብ ቢቀበል በወንጀል ያስጠይቃል። በዚህ ምክንያት (የተባለው እና የከፈሉበት ነገር የተለያየ ሆኖ ችግር ገጥሟቸው) ወደ ፍርድ ቤት ሲሄዱም፤ ችሎቱ የሚታየው በፍትሐ ብሔር ነው።

በዚህ መልኩ ደግሞ የተታለሉ ሰዎች ገንዘባቸውን ለማስመለስ ጥያቄ ሲያነሱ፣ ያጭበረበረው አካል ዋስትና ስለሌለው ለማስፈጸም ችግር ይገጥማል። ምክንያቱም ውሉ ችግር ያለበት ከመሆኑ ባሻገር፤ አልሚው መሬት እንኳን ሳይኖረው ቤት ገንብቼ እሸጣለሁ እያለ ማስታወቂያ የሚያስነግርበትና ከዜጎች ገንዘብ የሚሰበስብበት አግባብ መኖሩ ነው።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር (አሁን የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ስራ አስፈጻሚ) ዶክተር ብሩክ ታዬ እንደተናገሩት፤ በሪል ስቴት ዘርፉ ዙሪያ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን እና በማኅበራዊ ሚዲያዎች የሚለቀቁ ማስታወቂዎች ሳቢ እና አጓጊ ከመሆናቸው የተነሳ በርካታ ሰዎች እንዲሳሳቱና እንዲበዘበዙ አድርጓል። አንዳንዶች ቤት ይሁን አክሲዮን ምን እንኳን እንደሚሸጡ ሳያሳውቁ ነው ዜጎች በተሳሳተ ማስታወቂያ እየበዘበዙ ያሉት።

ችግሩን በመገንዘብ መፍትሄ የሚሆን መንገድ ለመከተል ተሞክሯል። በተለይም በካፒታል ገበያ በኩል ያለው ኃላፊነት በሼር የሚቋቋሙ ማናቸውም ድርጅቶች እንደመሆናቸው፤ ለመነገድ ተቋቁሞ ገበያ ላይ ወጥቶ ገንዘብ ማሰባሰብ የሚፈልግ ማንኛውም ሼር ካምፓኒ ወይም አካል መጀመሪያ ወደ ካፒታል ገበያ መጥቶ የኢንቨስትመንት መግለጫ እና ደንበኛ ሳቢ መግለጫ አስገብቶ ያ ደንበኛ ሳቢ መግለጫው ላይ በካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዕይታ ኑሮት ከተፈቀደ በኋላ ነው ወደ ሕዝብ የሚደርሰው።

ይሁን እንጂ አሁንም ድረስ የተቋቋምንበትን አዋጅ

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## ልዩ የምርመራ ዘገባ

# የሪል ስቴቱ ውስጣ ውስጥ...

ከ8ኛው ገጽ የዞረ

ካለማወቅ፣ ከመዘናጋት፣ አለበለዚያም መመሪያዎችን ካለማየት የተነሳ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ማስወቂያዎችን በሚዲያ ሲያስተዋወቁ አሁንም እየተስተዋለ ነው።

ያለፈውን መመለስ ባይቻል እንኳን አሁን ያለውን ችግር ለመቅረፍም ሆነ በቀጣይ መሰል ችግር እንዳይከሰት ከመገናኛ ብዙሃን አመራሮች ጋር በመነጋገር፣ ማንኛውም ማስታወቂያ (በተለይ የአክሲዮን ሽያጭ ከሆነ) በካፒታል ገበያ ባለስልጣን ታይቶ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ እንዲነገር የሚያደርግ አሰራር ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በእስካሁኑምትግበራበቴሌቪዥንእየወጡይህንያህል ሚሊዮን ብር ታተርፋላችሁ እያሉ የሚያጭበረብሩትን አደብ እንዲገዙ አድርጓል። በተመሳሳይ የሪል ስቴት ካምፓኒ ይሁን የአክሲዮን ካምፓኒ በማይታወቅበት ሁኔታ የተዘበራረቀ ማስታወቂያ እያስነገሩ፣ ገንዘብ ብቻ የሚሰበስቡትንም ከገበያ እንዲወጡ ማድረግ አስችሏል።

የኢትዮ-አሊያንስ የጥብቅና መስራችና የክርክሮች ኃላፊ ጠበቃ አዲስ ሳዲቅ እንደሚያስረዱት፣ የኮንዶሚነየም ቤት የራሱ አዋጅ ኖሮት፣ የሚያስተዳድረው አካል ኖሮ፣ የቤቶች አስተዳደር የሚባል አዋጅ ተቀርጾለት ነው የተጀመረው። ይሁንና ይሄ ሕግ መንግስት የገነባቸውን ቤቶች ከማስተዳደር በዘለለ በግል ዘርፉ አማካኝነት የሚለማውን የሪል ስቴት ዘርፍ የሚያስተዳድር አይደለም።

የሪል ስቴት ዘርፉ የሚመራበት ሕግና አሰራር ባለመኖሩ ማንም አካል ሪል እስቴት እየገነባሁ ነው የሚል ማስታወቂያ በማስነገር፤ ዜጎችን ለመበዝበዣ ተጠቅሞበታል። በአጠቃላይ ዘርፉ የሚመራበት ሕግ እና የሚቆጣጠረው ተቋም ባለመኖሩ ዘርፉ መርህና ባለቤት አልባ ሆኗል። በዚህም ቃላቸውን ጠብቀው የገነቡትን ቤት ለከፈለው ማኅበረሰብ ያስተላለፉ ታማኝ የሆኑ ሪል ስቴት አልሚዎች ያሉ ቢሆንም፤ ዘርፉ ባለቤት የሌለው በመሆኑ ሪል እስቴት ብለው አቋቁመው ከኅብረተሰቡ ገንዘብ ሰብስበው የቤቱ መጨረሻ ሳይታይ ገንዘቡን ይዘው የሚጠፉ በርካቶች ናቸው።

ጠበቃ አዲስ እንደሚሉት፤ ለሪል ስቴት ዘርፍ ተብሎ የሕግ ማሕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት የውል ሕጉ እንደሚዋዋሉት ሰዎች አቅምና በሪል እስቴቱ ብልጠት ላይ የተወሰነ ሆኗል። አንድ ሪል ስቴት አልሚና ቤት ፈላጊ ግለሰብ ውል የመገንዘብ አቅም ደግሞ እኩል አይደለም። በዘርፉ የማኅበረሰቡ የቤት ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑ ገንዘብ አለኝ ብሎ የመጣን ሰው ሁሉ በማግባባት ውል እንዲገባ የማድረግ ልምድ አለ። ለዚህ ደግሞ በርካታ የሪል ስቴት አልሚዎች የሕግ አማካሪ ስላላቸው ያለውን ክፍተት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አውቀው የራሳቸውን ጥቅም ያስጠብቁበታል።

ጠበቃ አዲስ፣ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በክርክር ሂደት ከገጠማቸው ጉዳይ ጋር አገናኝተው ሲያስረዱ፤ አንድ ሪል ስቴት አልሚ ነኝ ባይ ለሃያ ሰባት ሰዎች ቤት ገንብቶ ለመሸጥ የመንደር ውል ያስርላቸዋል። በገዥዎች ገንዘብም የቤት ግንባታውን ጀምሮ ለሌላ ሪል ስቴት ጅምር ቤቶቹን በውልና ማስረጃ ይሸጠዋል። ይሄን ያደረገው ሪል ስቴት አልሚ ታዲያ፣ ከሃያ ሰባቱ ሰዎች ጋር በመንደር ውል ሽያጭ ውል የያዘ ሲሆን፤ ለሪል እስቴቱ ግን በውል እና ማስረጃ በሕጋዊ መንገድ ነው የሸጠለት።

ምክንያቱም፣ ቀደም ሲል ለገዢዎቹ ሲሸጥ ቤት ስላልተገነባ ነው በመንደር ውል ያደረገው። ለሌላኛው ሪል ስቴት ሲሸጥ ግን ቤት ተገንብቷል፤ ካርታም አለው፤ ጅምር ቤት ስለሆነም መሸጥ ይቻላል። በዚህ ሂደት የቀደሙት ገዢዎች ቤቱን አልገዙም አይባልም። ምክንያቱም የመንደርም ውል ቢሆን መግዛታቸውን የሚሳይ ሰነድ አላቸው።

ነገር ግን በውልና ማስረጃ የጸደቀ (ማለትም ሶስተኛ ወገኖች መቃወሚያ ሊያደርጉት የሚችሉት) ውል አይደለም። የሸጠላቸው ሪል ስቴት አምኖ እስካልፈጸመ ድረስ፤ የውልና ማስረጃውን ስምምነት ለመፈጸም ይገደዳሉ፡ ምክንያቱም ሦስተኛ ወገን ውልና ማስረጃ ሄዶ የገዛው ሕጋዊ ማስረጃ አለው። በመሆኑም በዘርፉ ብዙ ተስፋ አድርገው የነበሩ ዜጎች በዚህ አይነት መንገድ ተበዝብዘው ተስፋቸውን አጥተው ቀርተዋል።

ተበዳዮቹ በፍርድ ገንዘባቸው ይመለስ የሚባልበት አግባብ ቢኖር እንኳን ከ10 ዓመት በፊት ስድስት ሚሊዮን ብር ያወጣ ሰው፣ ከአስር ዓመት በኋላ ስድስት ሚሊየን ብሩን ምን ያደርግበታል? የሚለው ሲታይ፤ ኮንዶምንየም ቤት እንኳን ላይገዛለት ይችላል። "የፐርፐዝ ብላክን " ጉዳይ ለአብነት በመውሰድ ጉዳዩን ለማስረዳት የሞከሩት ጠበቃው፤ የተጠቀሰው ድርጅት ቤት የሚገነባበትን መሬት እንኳን በአግባቡ ሳይዝ በባዶ ሜዳ ድርጅት አቋቁሞ ቤትና አክሲዮን እሸጣለሁ እያለ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሃን ያስነገረበት ሁኔታ ማሳያ መሆኑን ይጠቁማሉ። ይህ ሁሉ የሆነበት ዋናው ምክንያት ዘርፉ አዋጅና ሕግ የሌለው በመሆኑ፤ ይህን ተከትሎም የሚቆጣጠርና የሚመራ በገልጽ የሚታወቅ ተቋም ባለመኖሩ ነው።

ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት በባዶ ሪል ስቴት ማቋቋም ቀላሉ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኗል። ምክንያቱም የዘርፉ ቢዝነስ በአንድም በሌላ መንገድ ትንሽ መሬት ከያዙ በኋላ ተስፋ በመሸጥ ገንዘብ መሰብሰብ ነውና። የዜጎች ተስፋ ግን ጉም ሆኖ፣ ብዙ ተስፋዎች እንዲጨልሙ አድርጓል። ዘርፉ በሕግ ቢመራ ግን አልሚው በትክልል ገንብቶ ለተጠቃሚው ስለማቅረቡ ዋስትና ያቀርብ ነበር።

በዚህ መልኩ የሚደረጉ የግዢ ውሎች ገዥዎችን ሜዳ ላይ የሚያስቀሩ ናቸው። ለምሳሌ፣ መሬት አለ ተብሎ የተፈጸመ ውል፣ አፈጻጸም ላይ ሲመጣ መሬቱ በሌላ አልሚ ተይዟል፤ ብሩም የለም። ገንዘብ ሲቀበሉ በሁለት ዓመት እንጨርሳለን ቢሉም፤ በሁለት ዓመት አያሳኩትም። በዚህም ምክንያት አንድ ሚሊዮን ከፍሎ ቤት ለማግኘት የተስማማ ሰው፣ ይህ ሳይሳካ ቀርቶ በፍርድ ቤት ከ20 ዓመት በኋላ አንድ ሚሊየኑ ከወለድ ጋር ይመለስለት ቢባል፤ ይህ ገንዘብ እንኳን ቤት ተራ መኪና ላይገዛበት ይችላል። ጠበቃ አዲስ እንደገለጹት፤ ከአፍሪካ ኬንያ፤ የአውሮፓ ሀገራት፤ አሜሪካ፤ ሕንድና መሰል ሀገራት በሪል ስቴት ዘርፍ ውጤታማ ሆነዋል። ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት ሕግና ስርዓት በማበጀት በመሥራታቸ ነው።

ኢንጅነር ደሳለኝ ከበደ እንደ ሕንድ ባሉ ሪል ስቴትን በተገቢው መንገድ ውጤታማ ያደረጉ ሀገራት የስኬታቸው ሚስጥር ምንጭ የግብይት ወይም የሽያጭ ባለሙያዎች በዘርፉ የሰለጠኑና ትክክለኛ መረጃ ለሕዝቡ በማድረሳቸው ነው ይላሉ። ቤት ፈላጊው ማኅበረሰብ የነቃና ያወቀ በመሆኑም መረጃዎችን አገናዝቦ ስለሚገዛ ብሎም ዘርፉ በአሠራር እና በመመሪያ በመደገፉ ዜጎቻቸውን ከብዝበዛ ታድገዋል።

በእኛ ሀገር ሁኔታ ግን ይህ አልሆነም። እናም አልሚዎች በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን አማራጮች ተጠቅመው ካስተዋወቁ አብዛኛው ሰው ያምናል። እንደ ኢቢሲ፣ ኢቢኤስ፤ ዋልታና ፋናን መሰል ትልልቅ የመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ማስታወቂያዎች ሲነገሩ የሚሰማ ቤት ፈላጊም፣ መገናኛ ብዙኃኑን ስለሚያምን አልሚዎችን አይጠራጠርም። ሆኖም ሪል ስቴት አልሚው የሚያቀርበው ማስታወቂያ፣ የቤት ፈላጊውን ድክመት በተረዳ የማስታወቂያ ስትራቴጂ ነው። በቅርቡ የተከሰተው የፐርፐዝ ብላክ ማስታወቂያም ለዚህ ጥሩ አብነት ነው። ጎጆ ብሪጅ ሀውሲንግም በትልልቅ ሚዲያዎች ጭምር አስነግሮ፤ አሁን ላይ ምን ደረጃ እንዳለ ይታወቃል።

ሕጋዊ ሳይሆኑ ሕግን ያከበሩ በማስመሰል በሕግና በአሰራር በሚመሩ መገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያዎችን ከማስነገር ጋር በተያያዘ "የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 ክፍል ሦስት አንቀጽ ስድስት ንዑስ ቁጥር አንድ ሀ እስከ ሰ ማንኛውም ማስታወቂያ የኅብረተሰቡን ማኅበራዊና ባሕላዊ እሴት፤ የሚያከብር የሸማቹን ማኅበረሰብ የማይጎዳ መሆን እንዳለበት ይገልጻል።

በዚሁ አዋጅ ክፍል አምስት አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ አንድ ማስታወቂያ ለማሰራጨት የተቋቋመ የብሮድካስት አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በብሮድካስት አገልግሎት ተጓዳኝ በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያን፤ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፤ ዓላማ፤ አገልግሎት፤ ምርትና መሰል መልዕክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማንኛውም ማስታወቂያ የሚመደበውን ጊዜ ይደነግጋል። በዚህ ምዕራፍ ንኡስ አንቀጽ ሀ ላይ እንደተመላከተው ከዕለቱ ፕሮግራም ወይም አንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ 20 በመቶ መብለጥ እንደሌለበት ነው።

በአዋጁ ክፍል ሰባት ላይ የማስታወቂያ አስነጋሪ፤ ወኪልና የማስታወቂያ አሰራጭ ግዴታዎች አንጽ 27 ንኡስ አንቀጽ አንድ ሀ እና ለ እንደተመላከተው በማስታወቂያ እንዲሰራጭ በማስታወቂያ አስነጋሪ የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና ማስታወቂያው በቀረበው መልኩ ቢሰራጭ ሕግን የመተላለፍ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ለማስታወቂያ አስነጋሪው እንዲያስተካከል የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል።

ይሄንጉዳይየመቆጣጠርናችግሩንየመከላከልኃላፊነት ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን እንደመሆኑ፤ በዚህ ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጡ የጠየቅናቸው በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የማስታወቂያ ክትትል ዴስክ ኃላፊ አቶ ዮናስ ፋንታዬ፣ የሚከተለውን ብለዋል።

**ማጭበርበሩ ማስታወቂዎችን ከማስነገር እንደሚጀምር ተናግረው ጥንቃቄው ከዚህ መጀመር አለበት ይላሉ። ማስታወቂያዎች ሲሠሩና ሲነገሩ በእውነት ላይ የተመረኮዙ እና ተጨባጭ መሆን አለባቸው። ይሁንና በተግባር የሚታየው ግን የሌለን ነገር ያለ አስመስሎ ማስታወቂያ መስራትና ማስነገር ነው። ሕዝቡም በመንግስት ሚዲያዎች ማስታወቂያው መተላለፉን በማየት እነዚህ ሰዎች ያሉት እውነት ነው ብሎ ተቀብሎ ገንዘቡን ካወጣ በኋላ በማስታወቂያ የተነገረው ነገር ሳይሆን እየቀረና ዜጎች እየተበዘበዙ ነው።**

የማስታወቂያ ዘርፉ በሕግና በስርዓት መመራት ስላለበት፣ እንደ ተቋም የማስታወቂያ ሥራ የሚከናወነው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን እንደመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 759/2004 መሰረት ያስፈጽማል። እንደሀገር በነበረው ተሞክሮ ደግሞ የማስታወቂያ ኢንዱስትሪው በልምድ የሚዘወር፤ ሙያው በሌላቸው አካላት ጭምር የሚሠራ ነበር። በርካታ ባለሀብቶችና ኢንቨስተሮች ምርትና አገልግሎታቸውን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በኅትመት ሚዲያውም የማስተዋወቅ ልምድ አልነበራቸውም፤ ቢኖርም እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም።

ማስታወቂያ ማስነገር ሲባል የራሳቸው ግሳንግስ ምርት እንዲጭኑበት አይደለም የሚሉት አቶ ዮናስ፤ ማስታወቂያ በባህሪው ኢንዱስትሪ እንደመሆኑ የንግድ ውድድሩ ፍትሃዊ ሆኖ ለኅብረተሰቡ ትክለኛ መረጃ ማድረስ ላይ የተመሰረተ ሊሆን እንደሚገባው ነው የጠቆሙት። ይህ በመሆኑ ከተለያዩ የመንግስት ተቆጣቀጣሪ አካላት (ለምሳሌ፣ ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን) ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ምርትና አገልግሎቶች ደረጃቸው የጠበቁ እና የደረጃ መስፈርት ያለፉ ስለመሆናቸው፤ ማስታወቂያው በሚዲያ ሲሰራጭም ጥንቃቄ እንዲደረግ በጋራ ይሠራል።

ለማስታወቂያ አስነጋሪው/ ባለሀብቱ፤ ማስታወቂያ አዘጋጁና ማስታወቂያውን ለሚያሰራጨው ሚዲያ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ይከናወናል። ምክንያቱም እነዚህ ሦስቱ አካላት በየደረጃቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት አግባብ ስላለ ነው፤ በዚህም የተወሰኑ ለውጦች ታይተዋል። በተለይ ሚዲያው በማኅበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ እዲፈጠር በማድረግ ረገድ ትልቅ ኃላፊነት አለበት የሚሉት አቶ ዮናስ፤ በእርሱ ሥራ ምክንያት ችግር ሲፈጠር በሕግ መጠየቅ አለበት። በመሆኑም ሚዲያዎች ማስታወቂያዎችን ሲያሰራጩ በባለቤትነት ስሜት ለሀገርና ለሕዝብ ወግነው መሥራት አለባቸው እንጂ፤ ገንዘብ ስለተከፈላቸው ብቻ ማሰራጨት የለባቸውም።

የሪል ስቴት ኢንዱስትሪው አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእውቀት እና የሕጋዊነት ጉዳይ ክፍተቶች ነበሩ። ገና ጅምር ኢንዱስትሪ ስለሆነ የሚስተዋሉ ጥፋቶችን ለማረም መጀመሪያ የሕግ ማሕቀፉን መሥራትና ግንዛቤ መፍጠር ተገቢ ነው። ምክንያቱም ሚዲያዎቹ በአዋጁ ልክ እርምጃ ይወሰድባቸው ወይም ይኮርኮሙ ቢባሉ ኖሮ እስካሁን አይኖሩም ነበር። ስለዚህ ዘርፉ ገና ጅምር ስለሆነ ማደግ ስላለበት ሆደ ሰፊ ሆኖ እንደሀገርና እንደተቋምም መስራት ስለነበረብን ይሄ ሲሠራ ቆይቷል። አሁን ላይ ግን የሚጠየቁበትን የሕግ ልኬት አውቀዋልና ክትትልና ተጠያቂነት ይኖራል።

እንደ ተቋም ጥፋት መኖሩና አለመኖሩ የሚለካው ማስታወቂያው ከተሰራጨ በኋላ ነው። ፕሮግራምና ማስታወቂያ ከተሰራጨ በኋላ ጉዳዩ ይታያል። መሬት ላይ ወይም ገበያ ላይ የሌለን ነገር ማስተዋወቅ ስህተት ብቻ ሳይሆን ወንጀልም ጭምር ነው። ስለዚህ የማስታወቂያ ወኪሉም ሆነ አሰራጭ ሚዲያውም ምርቱ አለ ወይ? ብሎ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብህ የሚል ጥያቄ በማንሳት ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ አለ። እስካሁን ከካፒታል ገበያ ባለስልጣን ጋር በተሰራው ሥራም ብዙ ነገሮች ቆመዋል፤ ተስተካከልዋል።

አሁን ላይ የማስታወቂያ ወኪሎች ከባለስልጣኑ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፤ ወደ ሚዲያ ሲሄዱ ይህንን ሳያሳዩ አይስተናገዱም። ምርቱ ወይም አገልግሎቱ ፈቃድ አለው፤ የለውም ? የዘመኑን ፈቃድ አድሷል፣ አላደሰም? የሚለውን ይታያል። ይህንን ማስታወቂያ ያዘጋጀው አካል ሕጋዊ ነው ወይ? ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አለው ወይ? የሚለው ሁሉ በሚገባ ይፈተሻል።

ከሪል ስቴት ወይም ደግሞ የመዋዕለ ንዋይ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ከዚህ በፊት የተሳሳተ አካሄድ ነበረው። በራሳቸው ድክመት ወይም ተነሳሽነት ማነስ ሳያረጋግጡ ማስታወቂያውን ሲያሰራጩ ኑረዋል። በዚህ ሳቢያም ሕዝቡ ለአላስፈላጊ ብዝበዛ እንዲዳረግ ሆኗል። የአክሲዮን ሽያጭ ገዥ እንዲመጣ ሲያስተዋውቅ የሚፈተሽ ጉዳይ አለው። ዛሬ ላይ በካፒታል ገበያ ተመዝኖ አልፎ የሚመጣ በመሆኑ መሬት ላይ ያለው ምንድን ነው? ተብሎ ሳይረጋገጥ ማስታወቂያው ወደ ስርጭት አይሄድም። ከዚህ የተነሳም ከማስታወቂያ ጋር የተያያዘ ከዚህ በኋላ የሚመጣ የማኅበረሰብ ስርቆት እና እንግልት የለም። ብር ሰብስቦ መጥፋትም አይቀጥልም።

**ክፍል ሶስት ይቀጥላል**

# የዝነኞች ገጽ

# አውራው ሙዚቃ አምባ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

አንድ ሰው ሙዚቃን ሲጫወት ምናልባትም በግሩም ድምጹ “ከሰማይ ወፍ የሚያረግፍ!” ተብሎለት ይሆናል። ከፒያኖ ፊት ሲቀመጥ “ይሄስ ድንጋዩንም በስሜት ያነዝራል!” የተባለለት ይሆናል። ብቻ ሌላም ይሆናል... የማይሆን የለምና።

ከሙዚቃ አውራዎቹ መካከል ለመሰለፍም በርከት ላሉት ዕድሉ አይጠፋም። ግን ግን...ራስን ችሎ አንድ የሙዚቃ አምባ ለመሆን ግን ዳዊት ይፍሩን መሆንን ይሻል። ሙዚቃ እርሱ ውስጥ ብቻ ሳትሆን እርሱም ሙዚቃ ውስጥ ነው። አምባ የመሆን ሚስጥሩ ከችሎታው ብቻ አይደለም። ከግል ብቃቱ ከፍ ብሎ በሙዚቃ መንደር ከባቢ ላይ ሁሉ እንደተንሰራፋ አየር ነው። ውስጡ ካለው ሙዚቃ ጋር ሙዚቀኞችም አሉበት። በሄደበት ሁሉ አምባውን እንደሠራላቸው ነው፡፡

በድምጹ ባያንጎራጉር ከሚያንጎራጉሩት ጋር አይጠፋም። ማይክ ጨብጦ ድምጹ ባይሰማም ከበስተጀርባ ግን ስምና ሥራው አለ። ሙዚቃ ሲባል ከየትኛውም ቦታና ጊዜ መከሰቱ አይቀርም። ስለሙዚቃ አምባ ካወጉ አውራውን ሳያነሱት አያልፉም። ዙፋን ተቀምጦ የሀገሩ ዳር ድንበር ሁሉ በስሩ እንዳለ ብርቱ ንጉሥ፤ ባይኖር እንኳን አለበት። ትናንትን በደንብ ያውቃታል። ከዛሬም ጋር በደንብ ይግባባል። እላይ ወጥቶ ከታላላቆች ጋር በሠራው ልክ እታች ወርዶም ከታናናሾች ጋር ይታያል። በትልቁና በትንሹ፣ በዘመንና ዘመን፣ በሙዚቃና በሙዚቀኞች መካከል ድልድይ የሆነ ሰው ነው፡፡

ዳዊት ይፍሩን በቃላት ከመግለጽ ይልቅ ሥራዎቹ ይበልጥ ይናገራሉ። ሮሃ ባንድ ሲታወስ ምስሉ የዳዊት ይፍሩ ነው። ቬነስ ባንድንም ቢጠሩት ድምጹ ከዳዊት ይፍሩ ነው። ዳሕላክ ባንድ አፍታ የማይዘነጋው ትዝታው ነው። ... በአጠቃላይ “ባንድ” ሲሉ ዳዊት ይፍሩ ብለው ባይጠሩትም፤ ዳዊት ይፍሩ ግን ከውስጥ አለበት። በርሱ ፊታውራሪነት የተመሠረቱ ባንዶች በርከት ያሉ ናቸው። እርሱ ከሙዚቃ ጋር ያለው ተዛምዶ የተለየ ነው። ማን ይናገር ካሉ የሠራቸው ከ2 ሺህ 500 በላይ የሆኑ ሙዚቃዎቹ ይናገሩታል።

“ኸረ እንደው ግን ሙዚቃን መቼ ይሆን የተዋወቅካት?” ለሚሉት ሁሉ ገና የ11 ዓመት ልጅ ሳለ ጀምሮ እንደሆነ ይናገራል። ገብቶም ወጥቶም፣ ሄዶም ተቀምጦም የሚስበው አየር፣ የሚያስወጣው ትንፋሽ ሁሉ ሙዚቃ ነበር። ልክ እንደመንታ ወንድሙ በሄደበት ሁሉ እሱ አለ። ግን ይህን ሁሉ ነገር ዳዊት አያውቅም። እንዲያው በደመነብስ ወስዶ ሙዚቃ ላይ ይጥለዋል እንጂ ሙዚቀኛ ነው የምሆነው የሚል ሀሳብ እንኳን ውልብ አይልበትም። ደግሞ አሁንም ትልም ሕልም ሳይል ወደ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ቲያትር ቤት ገባ።

ለአምስት ዓመታት ያህልም የሙዚቃ መሣሪያዎችን ተማረ። ጊታር፣ ኪቦርድ፣ አኮርዲዮን፣ ትንሽዬዋን ቲፓኒ ሁሉ ተማረ። “እኔ ሙዚቃን ለመማር ነው የገባሁት። ሂደቱ ነው ሙዚቀኛ ያደረገኝ። ስማርም ለጊዜ ማሳለፊያ፣ ለተዝናኖት ያህል ነበር” ይላል። ሲፈጥረውም የሙዚቃ ጥበብ መርጣ ዘይቱን አፍሳበት ነበርና በችሎታው ከተማሪዎቹ ሁሉ ላቀ፡፡

ሁሉንም በቁንጥ አሳምሮ ሲጫወት ደርሶ ትንፋሽ ላይ ግን ቆም አለ። እስካሁንም ድረስ ያልተፈታተሹት ከትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር ነው። ከእነርሱ ጋር ፍቅርም ሆነ እልክ ያለው አይመስልም፡፡

ዳዊት ይፍሩ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ ማነው? ሁሉም ሰው እርሱ ማለት ብሎ እንደሚመልሰው አንጋፋና ዘመን ተሻጋሪ የሙዚቃ ባለሙያ ነው። ግን ይሄ እውነት ብቻ የርሱን የሙዚቃ ውሃልክ አያመጣውም። ምክንያቱም በሙዚቃ ሕይወቱ ውስጥ ጥንቅቅ አድርጎ የሚያውቀው ሙያውን ብቻ አይደለም። የሙዚቃ ንፋስ የነፈሰባቸውን ባለሙያዎችንም ችሎታ አብጠርጥሮ የሚያውቅ ሰው ነው።

እያንዳንዱን ባለው ነገር ልኬት ሳያዛንፍም ማስቀመጥ የሚችል ነው። ካለፈውም በሉት ካለው ማን፣ በየትኛው ሥራው፣ ምን እንደሆነ በልበሙሉነት ይገልጸዋል። እድሜና ጤና ሰጥቶት የሁሉንም ዘመን ፈርጦች ተመልክቷል። ከመልካሙ ተበጀ እስከ ጥላሁን ገሠሠ፣ ከሙሉቀን መለሰ እስከ ማሕሙድ አሕመድ፣ አልፎም እስከ ኤሊያስ መልካ ከወዲሕኛው ዘመን ከዋክብት አብሮ በጋራ ያልሠራው የለም። ባይሠራ እንኳን የሁሉንም ሥራዎች ነገሬ ብሎ መፈታተሹ አይቀርም። ተማሪም አስተማሪም፣ አባትም ባልደረባም ሆኖ ያልተገናኘው የለም። ሙዚቃንም ሆነ ሙዚቀኛውን በማወቅ ደረጃ ምናልባትም በጣት ከሚቆጠሩት መካከል ፊተኛው ነው፡፡




ከጎበዝ ተማሪ ጀርባ ቢያንስ አንድ ጎበዝ አስተማሪ መኖሩ አይካድም። ውብ ሕንጻ ለማነጽ የሚችለው ውብ የሆነ ሙያ ያለው ብቻ ነው። ዳዊት ይፍሩን ስንመለከትም ከበስተጀርባው ሆነው የምንመለከተውን መልኩንና እሱነቱን የሠሩ ታላላቅ ጠቢባን ስለመኖራቸው ሁሌም የሚናገረው ነው። “የኔታ የሙዚቃው ጌታ!” እያለ ከእግራቸው ስር ቁጭ ብሎ ጥበብን የቀሰመባቸው በሀገራችን ሙዚቃ ውስጥ አውራ ስም ያላቸው ናቸው። አንደኛው ጸጋዬ ደባልቄ ነው። ፒያኖና ቅንብርን ደህና አስቀሰመውታል። ጌታቸው ደገፉም በፒያኖ አሉበት። ግን ከሁሉም በላይ የሆነ አንድ ሰው አለ፤ እሱም ሙሴ ነርሲስ ነው።

ዳዊት ወደ ባንዱ ጠጋ የማለቱን ዕድል ካገኘ በኋላ በቫዮሊን፣ ፒያኖ፣ በጊታር እንዲሁም በሙዚቃ ቅንብር ቀደም ሲል የጀመረውን መንገድ ጠርጎ ወለል አደረገለት። ውስጡ በነበረችው እርሾ አድርሶ፣ እሳቱን አቀጣጥሎ አበሰለው። ዳዊትም ከዚህ በኋላ ስለ ሙዚቃ ወስኖ ሳያንገራግር ስለመኖር እንዲያስብ አደረገው፡፡

የሙዚቃ መሣሪያዎቹን አሳምሮ በብቃት ከመጫወቱ አልፎም፤ ምስጋና ለታላላቅ የኔታዎቹ ይግባና እነርሱን እየተከተለ ሙዚቃ ማቀናበርም ጀማመረ። “ለሠርጓ ጠራችኝ” የመልካሙ ተበጀ ተወዳጅ ሙዚቃ ነች። ይህቺ ሙዚቃ ደግሞ የዳዊት ይፍሩ የአቀናባሪነት አሀዱ ናት። የተማረውን፣ ያየውንና የሰማውን የቅንብር ዕውቀት አሰባስቦ ጥበቡን በማፈርጠም አንድ ብሎ ይቺን ሚዚቃ አቀናበረ። መልካሙ ተበጀ ለጉድ ተሰማለት። ዳዊት ይፍሩም ተጨበጨበለት። “ይችላል!” አሉት። “እችላለሁ!” አለ። ብቃቱን እርሱም እነርሱም አረጋገጡ፡፡

የእርሱ የሙዚቃ ዥረት መፍለቅ የጀመረበት ትልቁ ወንዝ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቲያትር ቤት ነው። በ1950ዎቹ አጋማሽ የሙዚቃ ትምህርቱን ሲማር እንኳን እንደ አቦሸማኔ ፈጣን ነበርና ሲጨርስ ደግሞ እሳት ለበስ ዳይኖሰር መሰለ። በፍጥነት የመልመድና የመከወን ችሎታው ላቅ ያለ ነበር። በነበራቸው ጉብዝና ተማሪውን ሁሉ ከኋላ ከሚያስከትሉት መካከል አንዱ ነበረና እየተማረ በወር 20 ብር ለኪስ ይከፈለው ነበር። የቲያትር ቤቱ ባንድ ሲመሠረትም የፊት መድረክ ተሰላፊ ነበር። ጥቂት የማይባል ጊዜ በባንዱ ውስጥ ሲሠራ ከቆየ በኋላ ቀጥሎ ወደ ሀገር ፍቅር ነበር ያመራው።

በዚያም የሙዚቃ ችሎታውን እያጠነከረው የተወሰነ ቆየ። በጊዜው የነበሩ እውቅ ሙዚቀኞች ሁሉ ሳይረግጡት የማያልፉት አንድ ቤት ነበርና ሦስተኛ መዳረሻውን ወደዚያው አደረገ። አሰገደች አላምረው ቤት የአብዛኛዎቹ ሙዚቀኞቹ መዋያና ማምሻ የነበረና አሁን “ክለብ” እንደምንለው ዓይነት ነበር። ጎበዞቹ ሁሉ ጎራ ብለው ሠርተውበታል። ለዳዊት ይፍሩም እጣ ክፍሉ ሆነና ገባ። ወዲያው እንደገባ ባይሆንም እምብዛም ሳይቆይ በገባበት እግሩ ተመልሶ መውጣቱ ግን አልቀረም፡፡

ዳዊት ይፍሩ ከሙዚቃ መሣሪያዎቹ ጋር ያልደረሰበት የለም። በቅንብር ከሠራቸው አንደኛው ግን የማሕሙድ አሕመድ “ሁሉም ይስማ” የሚለው አልበም ነው። ይህንን አልበም ሲሠራ ብቻውን አልነበረም። ወጣቱ ኤሊያስ መልካም በገሚሱ ላይ አብሮት ነበር። አልበሙ ከያዛቸው አሥር የሙዚቃ ስብስቦች 5ቱን ዳዊት፣ ቀሪ አምስቱን ደግሞ ባለጊታሩ ኤሊያስ መልካ ነበር የሠራው። በሌላ ጊዜም በጸጋዬ ዘርፉ አልበም ላይ ተገናኝተዋል። በጊዜው አልበሙን ሲሠሩ በጣም ተጠበው ከመሆኑም የጸጋዬ የአዘፋፈን ስልትም ግሩም ስለነበረ ገበያ ላይ ሲወጣ ሀገር ምድሩን ያጥለቀልቀዋል ብለው ቢጠብቁም እንዳሰቡት ሳይሆንላቸው ቀርቷል። ባይሆን በዚያው ሰሞን አብሮ የወጣው የንዋይ ደበበ “የጥቅምት አበባ” ግን አቀባበሉና ተወዳጅነቱ የተለየ ነበር፡፡

ዳዊት ይፍሩ ራሱን የቻለ አንድ የሙዚቃ አምባ ነው እንድንል የሚያደርገን ሌላ ቢኖር ባንዶቹ ናቸው። በየበረሃው ድንኳን እንደሚጥል ሰው በሄደበት ሁሉ ባንድ ማቋቋም ይወዳል። ከሀገር ፍቅር ቆይታው በኋላ ከሙዚቃ መሣሪያዎቹ ጋር ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ይገኝ ነበር። በወቅቱም እርሱና የሥራ አጋሮቹ ተጠናክረው “ኤኩኤተርስ” የተሰኘ ባንድ መሠረቱ። የርሱ አሻራ ያረፈባቸው ባንዶች ቁጥር በርከት ያሉ ናቸው። በኋላም አይቤክስና ዳሕላክ ባንዶች ምርጡን ጥምረት ፈጥረው በሕብር ሲቆሙ ከውስጡ ሮሃ ባንድ ተወለደ። የሮሃ ውልደትም ቀዳሚውን ሚና ለዳዊት ይፍሩ ይሰጣል። ባንዱ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ የነበረውን ሥራና ስም ለማንም አይነገረውም። በዚህ ባንድ ውስጥ ዳዊት ብቻ ከ200 በላይ በሆኑ የአልበም ሥራዎች ውስጥ እስትንፋሱን አኑሯል። በ1970ዎቹና 1980ዎቹ ገደማ ከተሠሩ ልብ አቅላጭ ሙዚቃዎች መካከል አብዛኛዎቹ የዳዊት ይፍሩ የጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡

ሁሉም ሰው ወዶ ከሚውልበት ቦታ ላይ ለመገኘቱና ለመቆየቱ ምክንያት የሚሆኑት ነገሮች ይኖሩታል። ታዲያ ዳዊት ይፍሩ ይህን ሁሉ ዘመን ከሙዚቃ ጋር በሙዚቃ የሚኖርበት ምክንያት ምን ይሆን? ብዙዎች ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሉት “ሙዚቃን ስለማፈቅር፣ ያለሙዚቃ መኖር ስለማልችል” ነው። ዳዊት ይፍሩ ግን በሚዲያዎችም ይሁን በጨዋታ “የምንሠራው አንደኛው ለስሜታችን፣ ሁለተኛ ለመታወቅ፣ ሦስተኛ ደግሞ ለገንዘብ ነው” በማለት እቅጯን ያስቀምጣታል። እንዲህ ሲል ግን አንድ ሁለት ብሎ በደረጃ ያስቀመጠው ቅደም ተከተሉ ሳይዛባ ነው። ከስሜቱና ከሙያ ፍቅሩ ወደ ሦስተኛው ዘሎ ገንዘብን አስቀድሞ አያውቅም። ብዙ ጊዜ ጥቅሙን ሳያሰላ የሚሠራ ሰው ነው። በተለይ ደግሞ በሮሃ ባንድ ውስጥ የተሠሩ አብዛኛዎቹ ሥራዎች በዝቅተኛ ክፍያ፣ አልፎም በነጻ የተሠሩ ናቸው፡፡

አሁን እድሜው ገፍቶ፣ ከብዙ ውጣውረድ ተራርፎ እንኳን ሁሉንም ያሰባሰበውን የሙዚቀኞች ማሕበርን በፕሬዚደንትነት ይመራል። በዘመኑ ሁሉ ያጠራቀመውን የሙያ ክሕሎትና የሕይወት መንገድ ፍኖት ማሕበሩንና አባላቱን በእግር ለመቆም መውተርተርን አስተምሯቸዋል። የራሱ የሆነ ቅንጣት የገቢ ምንጭ የሌለው ተቋም ሆኖ ፈተናውን ቢያበዛም የተሻሉ መስመሮችን በማስመሩ ዳዊት የሚታማ አይደለም፡፡

ከምትወደው የሙዚቃ ስልት ምረጥ ቢሉት ነብሲያው ትዝታ ላይ ታርፋለች። ውስጡ በድባቴ ተወቅቶ፣ መከፋት ሆድ ቢያስብሰው፣ ዝም ብሎ በዝምታ ጥቂት ውስጡን ለማድመጥ ቢፈልግ ትዝታ ትራሱ ናት። ትዝታ መውጫና መግቢያው ናት። ለካስ አንዳንዴ ከጣትም ጣት ይመረጣል። በጣም የሚወዱትንና አብዝተው የሚሳሱለት ልጅ ትተው ዙፋኑን ለሌላኛው ልጅ እንድንሰጥ የሚያደርጉን ምክንያታዊ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። አብዝቶ የሚያደምጠው ትዝታን ቢሆንም በሙያዊ ልቦናው ሲመለከት ግን የሚያደንቀው አንቺሆዬን ነው። የአንቺሆዬ ቃናዋ ይበልጥ ያውደዋል።

ከ45 ዓመታት በፊትም በሙዚቃ መሣሪያ ብቻ በተቀነባበሩ ስብስቦች አልበም ሠርቶ ገበያ ቢያውለውም አድማጭ ግን አልነበረውም። ጊዜው በድምጻውያኑ ሙዚቃ ሽር የሚሉበት እንጂ በክላሲካል የሚተክዙበት ስላልነበረ እንደዛሬው አይታወቅም ነበር። አሁን ከዚያ ሁሉ ዓመታት በኋላ ግን “ያንኑ ደግሜ አድምጡልኝ ለማለት ተገድጄያለሁ” አለ እርሱም። ምስጋና ለቴክኖሎጂው ይግባና እኚህኑ ሥራዎቹን እንደ አዲስ በዩትዩብ ማሕደር ላይ አኑሯቸዋል፡፡

ትልቅ ሰው ራሱን ብቻ ሳይሆን ሰውንም ያውቃል። ከዳዊት ይፍሩ መልከ ወርቅ ባህሪያት መካከል አንዱን ቢሉ በየዘመናቱ አሁንም ድረስ ታላቅ ሥራ እየሠሩ ያሉትን አብጠርጥሮ የሚያውቅ መሆኑን ነው። ማወቅ ብቻም አይደለም በብዙ መድረኮች ከራሱ ይልቅ ስለሌሎች ሲያወራ ይደመጣል። አሁን ከሚመለከታቸውና ከሚያደምጣቸው እየጠቀሰ ትልቅነታቸውን ይናገራል። ወደላይ ማንጋጠጥ ብቻ ሳይሆን ወደታች ማቀርቀርም ያውቅበታል። ከጊዜው ወጣት የጥበብ ባለሙያዎች መካከል ላገኘው ሁሉም ይመሰክርለታል። የርሱ የትንሽነትና ትልቅነት ሚዛን ከሥራቸው ላይ ብቻ ነው። ከስር እየመጡ ያሉትን በሙያ ለማብቃት ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ነው። “ወጣት ድምጻውያን ከዳዊት ጋር አብሬ ብሠራ ብለው ከመጡ፤ አብሬያቸው ልሠራ ፈቃደኛ ነኝ። ሥራ ከመጣ እሠራለሁ ግን ሥራ ፈልጌ የምሄድበት እድሜ ላይ አይደለሁም” ሲል ይናገራል፡፡

“እንዴት ነው ዳዊት ይፍሩ ከሌሎች ጋር ሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ በሙዚቀኞቹ ላይ እየቀለደ ይጫወታል ይላሉና?” አለው አንዱ ጋዜጠኛ። “ኸረ በጭራሽ የማይሆነውን...እኔ በማንም ሆነ በሥራ ላይ ቀልጄ አላውቅም” ሲል ዳዊት ይመልሳል። ዳዊት ይፍሩ ለብዙዎች ኮስታራና ዝምተኛ ነው። ሲቀርቡት ግን ቀልደኛና ጨዋታ አዋቂ ነው። ከስድስት ዓመታት ወዲህ ግን የእውነትም ዝምተኛ መስሏል። ባለቤቱን በሞት ከተነጠቀ በኋላ ያለበት ሁኔታ ጥሩ አይደለም። ለተወሰኑ ጊዜያትም መከፋት በርትቶበታል። “መኖር አላሰኘኝም ነበር ግን ለልጆቼ ስል ነው የምኖረው” ነበር ያለው፡፡

የሙዚቃ አባው ዳዊት ይፍሩ ዛሬ ድረስ በሥራው ያገኛቸው ሽልማቶች በርካታ ናቸው። ለአብነትም በ2005 ዓ.ም ከወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬትን ተጎናጽፏል። ትልቁን የሎሬት ሜዳይ ለማጥለቅም ችሏል። በተለያዩ ጊዜያቶች የተበረከቱለት ዋንጫና ሰርተፍኬቶች ከቤቱ ታጭቀዋል።

ዳዊትን ሙዚቀኛ ባትሆን ኖሮ... አትበሉት፤ ምክንያቱም ሙዚቀኛ አለመሆን አይችልም ነበር። የሆነበት አኳኋን መርጦ ሳይሆን ተመርጦ ነው የሚመስለው። በሙዚቃ ሕይወት ውስጥ ገብቶ ሳያስበው ለመመለስ ከማይችልበት ረዥም መንገድ ደርሶ ነበር ሙዚቀኝነቱን አውቆና አምኖ የተቀበለው። አስቦና ሆን ብሎ ሙዚቀኛ ስላልሆነ ከፈቃዱ ውጭ በሆነ በአንዳች የጥበብ ኃይል ነበርና ያለመሆን ምርጫ አልነበረውም። “ሙዚቀኛ ባልሆን ኖሮ የሚለው አይሠራም። ሙዚቀኛ ባልሆን ኖሮ ያው አይደለሁም ማለት ነው” ምላሹ። ገና በጨቅላ ልጅነቱ ሳለ አባቱ ትክ ብለው ይመለከቱትና “ይሄ ልጅ ወታደር ነው የሚሆነው” ይሉት ነበር። ግን አልሆነም። የእርሱ መክሊት ለጦር አውድማ ሳይሆን ለሙዚቃ አምባ ነበርና አውራ የሙዚቃ አምባ ሆኖ ኖረው።

# ባህልና ቱሪዝም

## ‹ይቻላል› በተግባር የተገለጠበት ውብ መንደር

አንተነህ ቸሬ

በአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ ትኩረት ከተሰጣቸውና የምጣኔ ሀብት ምሰሶ ተደርገው ከተለዩ ዘርፎች መካከል አንዱ ቱሪዝም ነው። ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የቱሪዝም ሀብት አንፃር ዘርፉ ትኩረት ከተሰጣቸው የምጣኔ ሀብት ዘርፎች መካከል አንዱ መሆኑ የሚያስገርም አይሆንም። ይህን እምቅ ሀብት በማልማት ዘርፉ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ ድርሻ ያለው አበርክቶ እንዲያድግ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችም እየተከናወኑ ይገኛሉ። በቅርቡ የተመረቀው ‹‹ቤኑና›› መንደርም ከእነዚህ ስራዎች መካከል የሚመደብ ነው።

‹‹ቤኑና›› መንደር ከመተሃራ ከተማ አቅራቢያ፣ ከአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በቅርብ ርቀት፣ በሰቃ ሐይቅ ላይ የተገነባ ድንቅ የቱሪስት መዳረሻ ሀብት ነው። ለመዝናኛ መዳረሻነት ተብሎ የተገነባው ይህ ሀብት፣ ግርማ ሞገስ ባላቸው አዋሽ እና አሰቦት ብሔራዊ ፓርኮች አቅራቢያ ይገኛል። በእነዚህ ዋና ዋና የቱሪስት መስህቦች አቅራቢያ በመገኘት ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ያለው ‹‹ቤኑና›› መንደር የመዝናኛ፣ የኢኮቱሪዝምና ተፈጥሮን ያማከሉ ተሞክሮዎች ማዕከል የመሆን እምቅ አቅም ያለው ሲሆን፣ በኢትዮጵያ እየጨመረ የመጣውን የዘላቂ ቱሪዝም ልማት ፍላጎትን የሚደግፍ ነው። መንደሩ የተገነባው በኢትዮጵያ መንግሥት፣ በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥትና በግሉ ዘርፍ ትብብር ነው።

መንደሩን መርቀው የከፈቱት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ‹‹ቤኑና›› ይቻላል በተግባር የታየበትና የፈተናዎች መብዛት ሀገርን ከመለወጥ የሚያስቆም እንዳልሆነ ማረጋገጫ መሆን የቻለ ድንቅ ስራ እንደሆነ ይገልፃሉ። ‹‹ቤኑና መንደር ‹ይቻላል›ን በዓይናችን ያየንበት፣ በእጃችን የጨበጥንበት፣ የኢትዮጵያን ብልጽግናና የኢትዮጵያን መለወጥ መሰረት ለመጣል ለሚሹ ሀገር ወዳድ ዜጎች ፈተና ሀገርን ከመቀየር የሚያስቆም እንዳልሆነ፤ ሕልም ያለው፣ የሕልም ጉልበትን መመንዘር የቻለና የተባበረ ሁሉ፣ የተዘነጋ ስፍራንም ቢሆን ገነት ማድረግ እንደሚቻል ከፍተኛ ትምህርት የተወሰደበት እና ‹ይቻላል› መፈክር ሳይሆን የሚታይና የሚጨበጥ ነገር መሆኑን በውል ትምህርት የቀሰምንበት ቦታ ነው›› ሲሉ ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ እንደሚያስታውሱት፣ ዛሬ ውብና ጽዱ ሆኖ የሚታየው ‹‹ቤኑና›› በተገነባበት አካባቢ ከሦስት ዓመታት ገደማ በፊት አንዲት ዘለላ ሳር ማየት ብርቅ ነበር። አካባቢው ሙሉ በሙሉ በረሃ ነበር። ‹‹በወቅቱ የነበረን መሪ ቃል ከበረሃ ወደ እርሻ ስፍራ (From Desert to Farmland) የሚል ነበር። ይህን በረሃ ለእርሻ ምቹ ወደሆነ ስፍራ መቀየር፣ አፈሩንና ውሃውን ማከም እንዲሁም አካባቢውን መለወጥ አለብን። እዚህ ቦታ (በሰቃ ላይ) ከተሳካልን የትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ ላይ ሊሳካልን የማይችል ቦታ አይኖርም። በስፍራው ከፍተኛ ሙቀት አለ፤ ለመጠጥ የሚሆን ውሃ የለም፤ አፈሩ በአሲድ የተበላ ነው፤ ለኑሮ ምቹ አይደለም የሚባልን ይህን ስፍራ መለወጥና ምቹ ማድረግ ከቻልን በየትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ ብንሄድ ከዚህ የከፋ ፈተና ሊገጥመን ስለማይችል ለኢትዮጵያ ብልጽግና መሰረት መጣል ይቻላል የሚል ሙሉ እምነት ነበረን። እጅግ በጣም ፈታኝና አድካሚ ስራ ነበር። ከስራውም በተጨማሪ ለሕዝብ እንደሚሰራ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ እንደሚሰራ ስፍራ የሚነገሩ ፕሮፓጋንዳዎች ሲታከሉበት ይህን ስራ በቁርጠኝነት መፈፀም ቀላል አልነበረም›› በማለት ስለስራው ፈታኝነት አስታውሰዋል።

‹‹ቤኑና›› አስቸጋሪ የአየር ፀባይን ብቻ ሳይሆን አሉባልታዎችንም ጭምር ተቋቁሞ ስራን በድል የማጠናቀቅ ምሳሌ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ያብራራሉ። ‹‹ስለ ‹ቤኑና› እንኳን ለሕዝባችን፣ በአካባቢያችን ላሉ ሰዎችም ማሳመን ከባድ ነበር። ከቦታው አስቸጋሪነት የተነሳ ይህ ነገር በዚህ መልክ ሊያልቅ ይችላል ብሎ ያሰበ ብዙ ሰው አልነበረም። ነገር ግን በጽናትና በትብብር እውን ሆኗል›› ብለዋል፡፡

ይህም ከዚህ ቀደም የነበሩ አሉባልታዎች በሙሉ ትክክል እንዳልነበሩ ሰው በዓይኑ በማየት፣ በውስጡ በመሄድ ለመገንዘብ እድል እንዲያገኝ እንደሚያደርግ መሆኑን ገልጸው፣ ‹‹ይህ ስፍራ የተሰራው ለሕዝብ ነው። እስካሁን በደንብ ያልተገለፀበት ምክንያት በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በትብብር የሚሰራ እና በባህሪው በጣም ፈታኝ ስለነበር እንዲሁም የሁሉንም ጉልበት አስተባብረን ሙሉ ውጤት እስከምናመጣ ድረስ በዝምታ ጀምረን



‹‹ቤኑና›› በየትኛውም ዓለም ከሚገኙ ሪዞርቶች ጋር ሊስተካከል የሚችል ጥራት ያለው መሰረተ ልማቶችን የያዘ ነው

**‹‹ቤኑና›› ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን በርካታ ቅንጡ የመዝናኛ ስፍራዎች ካሉባቸው የበለጸጉ ሀገራት የመጡ ሰዎችን ጭምር ያስደነቀ ውብ መንደር መሆን ችሏል**

በዝምታ የጨረስነው ፕሮጀክት ስለሆነ ነው›› ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ መንግሥትና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ትብብር እንዲሁም ከግል ዘርፍ ጥቂቶች በገንዘባቸው፣ በእውቀታቸውና በጉልበታቸው ከፍተኛ ድጋፍ በማድረጋቸው በትብብር መንፈስ በረሃ የነበረውን አካባቢ ገነት ማድረግ ተችሏል። በረሃ የነበረውን ስፍራ ገነት ያደረገ እጅና አዕምሮ መላው ኢትዮጵያን በዚህ መንገድ ገነት ለማድረግ መነሻ የሆነ ትምህርት እንደቀሰመ ምንም ጥርጥር የለውም።

በስፍራው አስቸጋሪ የአየር ፀባይ ምክንያት እርሻው፣ የሌማት ትሩፋቱ፣ ኮንስትራክሽኑና በሌሎች የመንደሩ ግንባታ ሂደት ውስጥ የነበሩ ስራዎች፣ በስራዎቹ ውስጥ የተሳተፉ ተዋንያንን በእጅጉ የተፈተኑ ቢሆንም፣ ባለሀብቶቹም ሆኑ ባለሙያዎቹ የበለጠ እውቀትና ልምድ አግኝተው በረሃን ማልማት እንደሚቻል በተግባር አሳይተዋል፤ ከፍተኛ ድጋፍም አድርገዋል። ‹‹ቤኑና››ን የመሰለ ውብ መንደር እውን ማድረግ የቻለውም ፈተናን በጽናት የመቋቋምና የመተባበር ብቃት ነው።

‹‹ቤኑና›› አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የወተትና ስጋ ውጤቶች የሚመረቱበትን የእርሻና የሌማት ትሩፋት ተግባራትን አካትቶ የያዘ መንደር ነው። አትክልቱና ፍራፍሬው እንዲሁም የወተትና ስጋ ውጤቶቹ የእረፍትና የመዝናኛ ጊዜያቸውን በመንደሩ ለማሳለፍ ወደ መንደሩ ለሚያቀኑ እንግዶች ምግብነት ይውላሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ስለመንደሩ የእርሻና የሌማት ትሩፋት ተግባራት ሲያስረዱ ‹‹ቤኑና ፓፓያ፣ አቮካዶ፣ ዘይቱን፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ መንደሪን እና የመሳሳሉት በስፋት የለሙበትና ለምግብነት የሚውሉበት ሪዞርት ነው‹›› ብለዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ እርሻን ለሪዞርቱ ሙሉ በሙሉ ግብዓት አድርገን ለመጠቀም የሚያስችል ስራ ተሰርቶበት የተሳካ ውጤት ተገኝቶበታል። እርሻው በርካታ ሰዎች የስራ እድል እንዲያገኙ አስችሏል።

ከእርሻው በተጨማሪ የሌማት ትሩፋትን በሚመለከት በዚህ ስፍራ ግመሎች፣ ላሞች፣ ፍየሎች፣ ዶሮዎች እና ሌሎች አሉ። በቀን ከ400 እስከ 500 እንቁላል ይመረታል። ለግቢው የሚያስፈልገው እንቁላል፣ ስጋና ወተት ከዚሁ ይመረታል። እያንዳንዱ ሪዞርት ከእርሻውም ሆነ ከሌማቱም በዚህ መንገድ ስራ እየሰራ ከሄደ ራሱን መመገብ መቻሉ ብቻ ሳይሆን የሚፈጥረው የስራ እድል እና የሚቀይረው አካባቢ ትልቅ እንደሚሆን ማየት ይቻላል፡፡

‹‹ቤኑና›› በየትኛውም ዓለም ከሚገኙ ሪዞርቶች ጋር ሊስተካከል የሚችል ጥራት ያለው መሰረተ ልማቶችን የያዘ ቦታ እንደሆነ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፣ መንደሩ ለትራንስፖርት ምቹ ከመሆኑ ባሻገር፣ በአካባቢው የሚገኙ ሌሎች የቱሪስት መስህቦችን በቀላሉ ለመጎብኘት እድል እንደሚፈጥርም ያስረዳሉ፡፡

ሪዞርቶቹ የተሰሩበት ጥራት በአምስት ኮከብ ደረጃ እንዲታዩ የሚያስችላቸው ነው። ከአዲስ አበባ የሚነሳ ሰው ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል በመኪና ተጉዞ ‹‹ቤኑና›› መድረስ ይችላል። መንደሩ ከደረሰ በኋላም አንድ ሳይሆን ሁለት ብሔራዊ ፓርኮችን የማየት እድል አለው። ወደመንደሩ የሄዱ ሰዎች ወደፊትም ሆነ ወደኋላ ቢጓዙ ሊጎበኙ የሚችሉ በርካታ ቦታዎችን ማግኘት ስለሚችሉ ኢትዮጵያን መጎብኘት ለሚፈልጉ ሰዎች አካባቢው ምቹ ስፍራ ይሆናል።

ከ‹‹ቤኑና›› መንደር በቅርብ ርቀት ላይ የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ይገኛል። እንግዶች ወደ መንደሩ ከመጡ በኋላ ወደ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ሄደው በፓርኩ የሚገኙ አዕዋፍትና እንስሳትን እንዲሁም ፏፏቴዎችንና ፍልውሃዎችን የመጎብኘት እድል ያገኛሉ። ከፓርኩ በቅርብ ርቀት ላይ ደግሞ በአፋር ክልል በገበታ ለትውልድ የሚሰራው ፕሮጀክት ይገኛል። የአሰቦት ፓርክም በአካባቢው የሚገኝ ድንቅ የመስህብ ስፍራ ነው። በአካባቢው ባሉ ቦታዎች ላይ የተፈጥሮ ፍል ውሃዎች፣ ሃይቆችና ፏፏቴዎች ስለሚገኙ ከዚህ ቀደም በውጭ ሀገራት የምናያቸውንና የምንቀናባቸውን ነገሮች በዚህ አካባቢ በስፋት የማየት እድልን የከፈተ ነው። ሰዎች የዱር እንስሳትና ሌሎች ነገሮችን ለማየት ወደ ሌሎች ሀገራት ከመሄድ ይልቅ በሀገራቸው የተሻለ የመጎብኘት እድል እንዲያገኙ ያስችላል። በአጠቃላይ አካባቢው የኢትዮጵያን ልክ ለማወቅ የሚያግዝ ድንቅ ስፍራ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁን መንደሩን ለጎብኚዎች ክፍት በማድረግ እንግዶችን የማስተናገድ ስራው እየተጀመረ በመሆኑ ሰዎች እስከሚለማመዱና የቦታውን ውበት እስከሚያዩ ድረስ የጎብኚዎች ፍሰቱ ውስን ሊሆን እንደሚችል ጠቁመው፣ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ግን በአካባቢ የሚኖረው የቱሪስት አቅም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያድግ ይገልፃሉ።

ስካይላይት ሆቴል የ‹‹ቤኑና›› መንደር ሪዞርቶችን የማስተዳደር ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በ‹‹ገበታ ለሀገር›› የተገነቡ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን እያስተዳደረ የሚገኘው ሆቴሉ፣ በወንጪ፣ በጎርጎራና በሃላላ ኬላ የሚያከናውናቸውን አመርቂ ተግባራቱን በ‹‹ቤኑና››ም እንዲደግማቸው ኃላፊነት ተጥሎበታል።

‹‹እኛ ለሕዝባችን ቃል በገባነው መሰረት ትልቅ ሕልም አለን። ሕልማችን የበለፀገችና የተለወጠች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን ማስረከብ ነው። ይህ ሕልም ግን በየዕለቱ በስራ፣ በትጋት የማይገለጥ ከሆነ ስለማይመነዘር ሕልማችንን በስራና በጥረት በመግለጥ ውጤት በማሳየት፣ ውጤቱም ብዙ ሰዎችን እየሰበሰበ እንዲሄድ በማድረግ የኢትዮጵያን መፃኢ ጉዞና መልክ የማስዋብና የማላቅ ስራችንን እንቀጥላለን። ከቤተሰብና ከወዳጅ ጋር በመምጣት ይህን ስፍራ በማየት የኢትዮጵያን ልክ እንድናውቅና እንድንማር ለብዙዎቻችን ጠቃሚ ስለሚሆን ይህን ስፍራ በማየት የኢትዮጵያን ውበት ማድነቅና መግለጥ የምንችል ሰዎች መሆን አለብን›› ብለዋል።

በአርባምንጭ፣ በጅማ፣ በሱማሌ፣ በገረአልታ፣ በሐይቅ፣ በደምቢና በሌሎች አካባቢዎች የተጀመሩ ስራዎች እንደሚጠናቀቁ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ‹‹በቱሪዝም ሴክተር የጀመርነውን እንቅስቃሴ አጠናክረን በመቀጠል የኢትዮጵያን ልክ ለዓለም እንገልጣለን። ብልጽግናን በኢትዮጵያ ለማየት የሚያስችል መሰረት እንጥላለን። ልጆቻችን ለማኝ ያልሆኑ ኢትዮጵያን እናስረክባቸዋለን። ይህን ከማድረግ ሊያቆመንና ሊገታን የሚችል ኃይል የለም›› ብለዋል፡፡

‹‹ቤኑና›› ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን በርካታ ቅንጡ የመዝናኛ ስፍራዎች ካሉባቸው የበለጸጉ ሀገራት የመጡ ሰዎችን ጭምር ያስደነቀ ውብ መንደር መሆን ችሏል። በመንደሩ ምርቃት ላይ የተገኙ የሀገራት አምባሳደሮችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ለ‹‹ቤኑና›› ያላቸውን አድናቆት ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ የዩናይትድ ኪንግደም አምባሳደር እና የአፍሪካ ኅብረት ቋሚ ተወካይ ዳረን ዌልች፣ በፕሮጀክቱ ውስጥ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ሕልምና ለሀገራቸው ማደግ ያላቸውን ሃሳብ እንዳዩበት ይናገራሉ። ‹‹በስራው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሀገራቸው ኢትዮጵያ ያላቸውን ትልቅ ሕልም አይቻለሁ። ይህን ሀገር ለማሳደግ ያላቸውን ሃሳብም ተመልክቻለሁ። የተገነባው ሪዞርት አስደናቂና ደረጃውን የጠበቀ ስፍራ ነው›› ሲሉ አስታውቀዋል።

ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ ገና ሁለት ወራት ብቻ እንደሆናቸው የሚናገሩት በኢትዮጵያ አውሮፓ ኅብረት አምባሳደር ሶፊ ፍሮም-ኤምስበርገር፣ ኢትዮጵያ የታላላቅ ታሪኮች ባለቤት እንደሆነች ጠቅሰው፣ የተከናወነው ስራ አስደናቂ እንደሆነና በአካባቢው በርካታ አስደሳች ነገሮችን እንደተመለከቱ ይገልፃሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፣ አካባቢው ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ሃብቶች ተሰናስለው ውብ ገጽታን ያላበሱት አስደናቂ ስፍራ በመሆኑ መንደሩ የተላበሰው ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ለቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹ ነው። የመንደሩ ግንባታ ለአካባቢው ነዋሪ የስራ እድል ይፈጥራል። ስፍራው ለማኅበረሰብ ተኮር ቱሪዝም (Community-Based Tourism) ተምሳሌት መሆን ይችላል። ስራው ኢትዮጵያ ቱሪዝምን ከሀገር በቀል የግብርና ስራ ጋር በማጣመር እያከናወነች ያለችው ዘርፈ ብዙ ተግባር ማሳያ ነው።

የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ዳይሬክተር መርየም ሳሊም በበኩላቸው ‹‹ባየሁት ነገር ተደምሜያለሁ። የሚታየው ነገር ሁሉ እረፍትን የሚሰጥ ነው። ከቤተሰቦቼ ጋር በድጋሚ መጥቼ እጎበኘዋለሁ። ሰዎችም ወደዚህ ስፍራ መጥተው እንዲዝናኑ እጋብዛለሁ›› በማለት ስለመንደሩ አስደማሚነት ያስረዳሉ።

# ሳምንቱን በታሪክ

# የ60ዎቹ ግድያ 50ኛ ዓመት

**ዋለልኝ አየለ**

ስያሜውን ያገኘው በሁለት ምክንያት ነው። የመጀመሪያው እና ዋናው የተገደሉት ሰዎች 60 መሆናቸው ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ዘመኑ በ1960ዎቹ መሆኑ ነው። ይህ ክስተት በጥቅሉ በተለምዶ የ60ዎቹ ግድያ እየተባለ ይጠራል። የተገደሉት ሰዎች ሲቆጠሩ 59 ናቸው የሚሉ የታሪክ ፀሐፊዎችም አሉ፤ ሆኖም ግን ቁጥሩን በማጠጋጋት ይመስላል ‹‹60ዎቹ›› እየተባለ የሚጠራው።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 50 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም በደርግ መንግሥት የተፈጸመውን የ60ዎቹን ግድያ እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከሰቱ ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ የታሪክ ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ91 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ጋዜጠኛ፣ የታሪክ ፀሐፊ እና ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ ተወለደ።

ከ61 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 13 ቀን 1956 ዓ.ም (ኖቬምበር 22 ቀን 1963) 35ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት ጆን ፊዝጀራልድ ኬኔዲ (ጆን ኤፍ ኬኔዲ) ተገደሉ። ጆን ኤፍ ኬኔዲ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩ ሲሆን በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያለው ቤተ መጻሕፍት በስማቸው (ኬኔዲ ላይብረሪ) ይጠራል።

ከ19 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም አንጌላ ሜርክል የጀርመን የመጀመሪያዋ ሴት መራሂተ መንግሥት ሆነው ተሾሙ። ሜርክል ለ16 ዓመታት ያህል የጀርመን መራሂተ መንግሥት ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው ከ16 ዓመታት በኋላ ከታኅሳስ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለኦላፍ ሾልዝ ለቀዋል።

ከ138 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 14 ቀን 1879 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ተቆረቆረች። እቴጌ ጣይቱ ፍል ውሃ ፊል ፊል ወደሚልበት መስክ ወርደው ሳሉ፤ ከዚህ በፊት አይተዋት የማያውቋት አንዲት ልዩ አበባ አይተው ስለማረከቻቸው ቦታውን ‹‹አዲስ አበባ›› ብለው በመሰየማቸው የአዲስ አበባ ከተማ መነሻ መሆኑ በታሪክ ይነገራል።

ከ28 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 14 ቀን 1989 ዓ.ም 175 መንገደኞችን አሳፍሮ ከአዲስ አበባ ወደ ናይሮቢ በመጓዝ ላይ የነበረው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር ET961 የመንገደኞች አውሮፕላን፣ በሦስት ኢትዮጵያውያን ጠላፊዎች ተጠልፎ በኮሞሮስ ደሴት ላይ ተከሰከሰ፤ በአደጋው ጠላፊዎቹን ጨምሮ 125 ሰዎች ሞቱ፡፡

ከ50 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 15 ቀን 1967 ዓ.ም 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዓመት ዕድሜ እንዳለው የሚነገርለት የ‹‹ድንቅነሽ›› (ሉሲ) ቅሪተ አካል በኢትዮጵያ፣ አፋር ውስጥ ሐዳራይቶ በሚባል ቦታ ተገኘ። ቅሪተ አካሉን (አፅሙን) ያገኙት ፕሮፌሰር ዶናልድ ካርል ዮሃንሰን የተባሉ አሜሪካዊ የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ ናቸው። ቶም ግሬይ የተባለና በወቅቱ የድህረ ምረቃ ተማሪ የነበረ የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያም የፕሮፌሰር ዶናልድ ዮሃንሰን ረዳት ሆኖ ይሰራ ነበር።

ከ8 እና 4 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 16 ቀን እንደሚዋደዱ የሚነገርላቸው ጓደኞችና ወዳጅ የነበሩት፤ ሁለቱ የዓለማችን ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች፣ ኩባዊው አብዮተኛ ፊደል ካስትሮ እና አርጀንቲናዊው የእግር ኳስ ተጫዋች ማራዶና ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ነው። ፊደል ካስትሮ ኅዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፤ ከአራት ዓመት በኋላ ህዳር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ደግሞ አርጀንቲናዊው ዲዮጎ አርማንዶ ማራዶና ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

አሁን በዕለቱ በዝርዝር ወደምናየው የ60ዎቹ ግድያ ታሪክ እንሂድ፡፡

ለሺህ ዘመናት የኖረውን ንጉሣዊ ሥርዓት በመጣል አዲስ አብዮት የፈጠረው ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ሙስና እና ሌብነትን አጥብቆ በመፀየፍ፣ ከምንም በላይ ደግሞ በቆራጥ አገር ወዳድነቱ ሥርዓቱን የታገሉት ጠላቶቹ ሳይቀር ይመሰክሩለታል። ‹‹ባለአባት›› በሚል ኋላቀር አስተሳሰብ የጌታ እና ሎሌ ሥርዓት የነበረበትን ገርስሶ መሬትን ለአራሽ ገበሬ በመሥጠቱ በድሃው ማሕበረሰብ ሲመሰገን ኖሯል።

በእነዚህ ሁሉ ጥሩ ሥራዎቹ ውስጥ ግን ስሙ በመጥፎ እንዲነሳ ያደረጉት ጥቁር ታሪኮች አሉት። ከእነዚህ የደርግ ታሪኮች አንዱ እና ዋነኛው የ60ዎቹ ጀኔራሎችና ከፍተኛ ባለሥልጣናት ግድያ ነው። ‹‹አብዮት ልጆቿን በላች›› እየተባለም ይገለጻል።

ክስተቶቹን ለማስታወስ፤ የፍሰሐ ያዜን ‹‹የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዓመት ታሪክ ቅጽ 2›› መጽሐፍ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ (የተለያየ ዓመት ዕትም) እና የሌተናል ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ ‹‹አብዮቱና ትዝታዬ›› መጽሐፍ ምንጮቻችን አድርገናል።

ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም የደርግ ሊቀ መንበር ሆነው ከተሾሙ ጊዜ ጀምሮ በደርጉ አባላት መካከል መስማማት አልነበረም። ይባስ ብሎ ወደለየለት ስድድብና አተካራ ውስጥ ገቡ። ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምም ስለ ጀኔራል አማን ጉዳይ ለመወያየት የደርጉን አባላት ሰበሰቡ። ከዚሁ ጎን ለጎንም ከአንደኛው ብርጌድ ስድስተኛ ክፍለ ጦር የተውጣጡ ወታደሮች ጀኔራል አማንን በቁጥጥር ስር እንዲያውሉ ቢታዘዙም ‹‹እንዴት አማንን በሚያህል ጀግና ላይ አፈሙዝ እናነጣጥራለን? ... አናደርገውም!›› ብለው እምቢታቸውን ገለፁ።

በዚህ ምላሽ ክፉኛ የደነገጠው ደርግ፤ ጦሩ አፈሙዙን ወደ ደርግ ሊያዞር እንደሚችል ስጋት ቢገባውም የመጣው ይምጣ በማለት በቅርብ የተገኙ የደርግ ጥበቃ ኮማንዶዎችን ከጥቂት የቡድኑ አባላት ጋር በማጣመር በሻለቃ ዳንኤል አስፋው መሪነት ወደ ጀኔራል አማን መኖሪያ ቤት ላከ። ጀኔራል አማን እጅ እንዲሰጡ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ከነ ሻለቃ ዳንኤል ጋር ተኩስ ገጠሙና የተወሰኑትን ገድለው በመጨረሻ ግን ተገደሉ፡፡

ከደርግ አባላት ጋር ስብሰባ ተቀምጠው የነበሩት ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም የጀኔራሉን መገደል ሲሰሙ፤ አጀንዳውን በቁጥጥር ስር ወዳሉት የንጉሰ ነገሥቱ ባለስልጣናት ጉዳይ አዞሩት። (እርሳቸው ግን በደርግ አባላት ተገድጄ ነው አጀንዳውን ያነሳሁት ብለዋል)

‹‹አማን አንድ ወታደር ነው፤ የእርሱ ጉዳይ ትልቅ አጀንዳ አይደለም፤ ይልቅ የነዚያን ደም መጣጮች ጉዳይ ዳር ሳናደርስ ከዚህ አዳራሽ አንወጣም›› ያሉት ንዑስ የደርግ አባላት፤ ደርግ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለስልጣናት ስማቸው እየተጠራ ‹‹በለው ... ይገደል ... ይሙት ...›› በሚል የወታደሮች ፍርድ የስብሰባው አዳራሽ ድብልቅልቁ ወጣ፡፡

ብዙዎችን አስገርሞና አሳዝኖ የነበረው ‹‹በለው ... ይገደል ... ይሙት ...›› ሲሉ የነበሩት ንዑስ የደርግ አባላት ብዙዎቹን ታሳሪዎች በስምም በመልክም የማያውቋቸው መሆኑ ነው። በእርግጥ ብዙዎቹ ታሳሪዎች በሙስና የነቀዙ ግለሰቦች እንደነበሩ የታሪክ ፀሐፍት ያስረዳሉ። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ሀገራቸው የደከሙ እንደነ አክሊሉ ሀብተወልድ ያሉ ብርቅዬ ሰዎችም ከታሳሪዎቹ መካከል ነበሩ። በሙስና የነቀዙት ግለሰቦች ክስም ቢሆን ጉዳያቸውን ለመመርመር በተቋቋመው መርማሪ ኮሚሽን በኩል መጣራት ይገባው ነበር የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

እንግዲህ በዚህ ዓይነቱ አሳዛኝና አስደንጋጭ ውሳኔ 52 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለስልጣናትና 8 የደርግ አባላት (ባለስልጣናት) ሞት ተፈረደባቸውና ተገደሉ።

በነገራችን ላይ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ‹‹ትግላችን›› በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ስለ ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በሚያትተው ርዕስ፤ ጥፋቱን ወደ ጀኔራሉ ወስደውታል። እርሳቸው የሚሉት፤ ጀኔራሉ ኤርትራን ለማስገንጠል ሲያሴሩ ደርሼባቸዋለሁ ነው። በአንድ ስብሰባ ላይም ኤርትራን ለማስገንጠል እንደሚሰሩ በግልጽ የተናገሩት ነው ብለው የጀኔራል አማን ሚካኤል አምዶን ንግግር በመጽሐፋቸው ላይ በጥቅስ ውስጥ አድርገው አስፍረዋል።

ያም ሆነ ይህ አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚለው እውን ሆና የጦር ልምድ፣ የዲፕሎማሲ ልምድ እና የፖለቲካ ልምድ ያላቸውን ሁሉ የአብዮቱ ሰይፍ



60ዎቹ የጦር መኮንኖችና ባለሥልጣናት፣

አረፈባቸው።

እነዚህ 60 የጦር መኮንኖች እና ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተገደሉት በተለያየ ምክንያት ነው። ኃይላቸውን ከሕግ አግባብ ውጭ ተጠቅመዋል በሚል ውንጀላ የተገደሉ ባለስልጣናት፤ ጸሃፌ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድን ጨምሮ 17 ናቸው። ስልጣናቸውን ከሕግ አግባብ ውጭ ተጠቅመዋል በሚል ውንጀላ ደግሞ 34 ባለሥልጣናትና የጦር መኮንኖች ተገድለዋል፤ አብዛኞቹ የጦር መኮንኖች ናቸው።

‹‹የእርስ በእርስ ጦርነት ለመቀስቀስ በተሸረበ ደባ እና ታላቁን የለውጥ እንቅስቃሴ ለመግታት በተደረገ አሻጥር›› በሚል 5 የተገደሉ ሲሆን ሦስቱ ካፒቴን ናቸው። ‹‹ለመስሪያ ቤት የተገባን ቃል ኪዳን ባለመጠበቅ እና በጦር ኃይሉ ውስጥ ክፍፍል ለመፍጠር ሙከራ ማድረግ›› በሚል ውንጀላ ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ጨምሮ ሦስት ሰዎች ተገድለዋል።

ጸሐፌ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ በደርግ ታጣቂዎች ከመገደላቸው ቀደም ብለው በዕለቱ (ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም) እንዲህ ብለው ነበር። ‹‹እኛን በመግደል ኢትዮጵያን ከድህነቷ የምታወጧት ከሆነ፣ ድርጊታችሁን እንደ ታላቅ በረከት በፀጋ እንቀበላለን›› ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ ከድህነት ወጣች ወይ? የሚለውን ለታሪክ ፍርድ እንተወው!

ባለሥልጣናቱ የተከሰሱበት ጉዳይ ሳይነገራቸው ክስ ሳይመሠረትባቸው ለወራት በእስር ቆይተዋል። ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ግን የደርግ አባላት እና ንዑስ ደርግ በመባል የሚታወቁ በታላቁ ቤተ መንግሥት ተሰበሰቡ። በስብሰባው የደርጉ ተቀዳሚ ሊቀመንበር ጀነራል አማን አንዶም ግን አልተገኙም።

በባለሥልጣናቱ ላይ አንዳችም ክስ ሳይመሠረትባቸው ደርግ ራሱ ከሳሽ ራሱ ፈራጅ ሆኖ ሥልጣኑን ተጠቅሞ በዚሁ ቀን በስብሰባ የግድያ ውሳኔ አሳለፈባቸው። በ60ዎቹም የቀድሞ ባለሥልጣናት ላይ የግድያ እርምጃው የተወሰደው ከርቸሌ ተብሎ በሚታወቀው እስር ቤት ግቢ ውስጥ ሲሆን፣ አስከሬናቸውም እዚያው እንዲቀበር ተደርጎ ዘመድም እንዳይጠይቅ ተከልክሏል።

በዚህ እርምጃ ሁለት ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ጨምሮ አገረ ገዢዎች የካቢኔ ሚኒስትሮችና የጦር ጄኔራሎች ያለፍርድ ውሳኔ ነው የተገደሉት። ‹‹ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም›› ሲል የነበረው ደርግ በትረ ሥልጣኑን እንደጨበጠ ‹‹በደም ተጨመላለቀ›› የሚል ወቀሳ ሲሰነዘርበት ኖረ።

ግድያውን አስመልክቶ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። የሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዝታዎች በሚል ገነት አየለ በጻፉት መጽሐፍ ላይ የግድያ እርምጃውን ለመውሰድ አስቀድሞ የተያዘ አጀንዳ እንዳልነበር ኮሎኔል መንግሥቱ ገልጸዋል። ‹‹ማንም አመነም አላመነም እኔ የምናገረው እውነቱን ነው፤ በበኩሌ የተወሰደውን እርምጃ አልደገፍኩትም፤ ሌሎችም የደርግ አባላት በስልሳዎቹ ግድያ ሊጠየቁ አይገባም፤ ምክንያቱም በተቆጡ በተናደዱ የንኡስ ደርግ አባላት ድምጽ ተውጠን በዚያ ውስጥ ተዘፍቀን የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ። እኛ የተነሳንለትና ቆመንለት የነበረው ዓላማ ይሄ አልነበረም። ያንን የመሰለ ውሳኔ ለመወሰን አላሰብንም ነበር።›› ብለዋል። የዚያን እለት ብቸኛው አጀንዳ የጀነራል አማን ጉዳይ እንደነበረም ጠቅሰው፣ ስለ ኃይለስላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች የሚል ነገር ጨርሶ አልነበረም ተብሏል። ችግሩ ኮሎኔል መንግሥቱ በዚያ ጉዳይ ላይ ‹‹አድርገነዋል›› ይላሉ ወይ የሚለውን የማመን አለማመን ጉዳይ ነው።

በደርግ ዘመን ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ፍስሃ ደስታ ‹‹አብዮቱና ትዝታዬ›› በሚል መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት፤ ኮሎኔል መንግሥቱ ጉባዔውን በሊቀመንበርነት መምራት ብቻ ሳይሆን አጀንዳውን አዘጋጅተው አቅርበዋል ሲሉ ጽፈዋል። ኮሎኔል መንግሥቱ ኅዳር 13 ቀን 1967 ዓ.ም የእስርና የአብዮታዊ እርምጃ ደብዳቤ ጽፈዋል። በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ስምና ፊርማ የተጻፈው ይህ ደብዳቤ ‹‹በቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የተላለፈውን ከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔ ተግባራዊ ስለማድረግ ይመለከታል›› በሚል የተጻፈ ነው።

በዚሁ ደብዳቤ ለ54 ሰዎች መቀበሪያ ጉድጓድ እርምጃው በሚወሰድበት ቦታ በዶዘር እንዲቆፈር ታዝዟል፤ እርምጃው የሚወሰድባቸው ባለሥልጣናት ዝርዝርም ተለይቷል። ኮሎኔል መንግሥቱ እንዳሉት ሳይሆን በእስረኞቹ ላይ ውሳኔ ለማሳለፍ ነው ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ስብሰባ የተካሄደው።

ከጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ በመጀመር የካቢኔ ሚኒስትሮች፣ ጠቅላይ ገዥዎች፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ባልደረቦች፣ የንጉሡ ባለሥልጣናት ስማቸው ሲጠራ ተሰብሳቢዎቹ በወሬ ወይም በአሉባልታ የሰሙትን እየተናገሩ ድምጽ መስጠቱ ቀጠለ። ሃምሳ ዘጠነኛው ተራ ሲደርስ በቃ የሚል ስለተሰማ ሰብሳቢው ለዛሬ እዚህ ላይ እናበቃለን፤ የቀሩ ካለ ሌላ ጊዜ ይታያል በማለት የድምጽ መስጠት ሂደት ቆመ ሲሉ በመጽሐፋቸው አስፍረዋል።

ያም ሆነ ይህ ሁሉም ያመኑት ነገር ቢኖር 60ዎቹ መገደላቸውን ነው። የተገደሉት ሰዎች ደግሞ በየዘርፉ ልምድ እና እውቀት የነበራቸው ናቸው። እንዲህ አይነት ታሪኮችን ስናስታውስ ዋና ቁም ነገሩ ከስህተቶች ለመማር ነው፤ አኩሪ የሆኑ የአባቶቻችንን ጀግንነትና ጥበብ ደግሞ እንድናስቀጥላቸው ነው። እንደ ዓድዋ፣ ጉራዕ፣ ጉንደት፣ ካራማራ የመሳሰሉ የድል ታሪኮቻችንን በኩራት ስንናገራቸው እንደ ሰገሌ ጦርነት እና የ60ዎቹ አይነት የእርስበርስ ግድያዎችን ደግሞ ከስህተቶቻችን እንድንማርባቸው ነው። ምክንያቱም የ60ዎቹ ግድያ የደርግን ታሪክ ጥላሸት ቀብቶታል።

በአኩሪ ታሪኮቻችን እንኩራ፤ ከስህቶቻችን እንማር!

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ራሱ ኅዳር ሲታጠን

አዲስ አበባ ጽዱና ውብ ከተማ እየሆነች ነው። ከቆሻሻ ገንዳው ተርፎ ተዝረክርኮ የሚታይ ቆሻሻ የለም። ጉንፋን አስም ራስ ምታት የሚቀሰቅስ የሚገለማ ሽታ እየጠፋ ነው። የደረቅ ቆሻሻ አወጋገዳችን እየተሻሻለ ይገኛል። ከየቤቱ የሚወጣ ቆሻሻ ከስር ከስር ስለሚነሳ ለመታጠን ለመቃጠል የሚጠብቅ ቆሻሻ የለም። በዘመቻ ቆሻሻ ማቃጠል ትዝታ እየሆነ ነው። ምን አለፋችሁ ሕዳር ሲታጠን ራሱ ዓመቱን ሙሉ እየታጠነ ነው።

የኮሪደር ልማቱ ከተማዋን ጽዱና አረንጓዴ ስለአደረጋት እንደበፊት ቆሻሻ የትም ለመጣል እንዳይመች አድርጎታል። የመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት በተካሄደባቸው ሰፈሮችና መንገዶች ለኅዳር ሲታጠን የሚሆን ቆሻሻ የለም። ሁለተኛው የኮሪደር ልማት ሲጠናቀቅ፤ ፕሮጀክቱ በክልሎች ሲሰፋ፤ ወደ ገጠሩ የሀገራችን ክፍል ሲሻገገር ደግሞ ኅዳር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ታጠነ ማለት ነው። ኅዳር ሲታጠንም ትዝታና ታሪክ ሆነ ማለት አይደለ። ስለ ኮሪደር ልማቱ ትንሽ ልበልና ትዝታችን ወደ ሆነው ኅዳር ሲታጠን እመለሳለሁ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማት እንደ ኮዬ አደባባይ፣ ጎሮ እና ሰሚት ባሉ "የከተማዋ መግቢያ" እና "ማስፋፊያ ላይ በሚገኙ" አካባቢዎች እየተከናወነ ይገኛል። 43 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሁለተኛው ምዕራፍ ግንባታ፤ ከሸገር ከተማ የኮሪደር ልማት ጋር "በማስተሳሰር" እንዲከናወን ታቅዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር "የኮሪደር ልማት" ሲል የጠራውን ዋና ዋና መንገዶችን የማስዋብ፣ የእግረኛ መንገድን የማስፋት፣ መዝናኛ ቦታዎችን የመገንባት እንዲሁም የመንገድ ዳር መብራት እና ቴሌኮሚዩኒኬሽን መስመሮችን በዘመናዊ መንገድ የመዘርጋት ሥራ የፈታችን የካቲት ወር ዓመት ይሆነዋል።

የከተማዋን ታዋቂ እና ነባር አካባቢዎችን የሸፈነው የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት፤ አምስት መስመሮችን የያዘ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ከተከናወነባቸው አካባቢዎች መካከል ፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ ቦሌ፣ መገናኛ፣ ሜክሲኮ እና ሲኤምሲ ይገኙበታል።

የከተማ አስተዳደሩ፤ በድምሩ 48 ኪሎ ሜትር ለሚሸፍነው ለመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት፤ 33 ቢሊዮን ብር ወጪ ማድረጉንም መግለጻቸውም ይታወሳል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ግምገማ እየተደረገበት የተካሄደው ይህ የኮሪደር ልማት፤ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነችን ጨምሮ ከፍተኛ የከተማዋ ኃላፊዎች ግንባታ የሚከናወንባቸውን መስመሮች ተከፋፍለው ሥራውን መርተውታል።

ከኮሪደር ልማቱ መስመሮች ውስጥ ቀድሞ የተመረቀው በከንቲባዋ ክትትል ስር የነበረው ከአራት ኪሎ ፒያሳ የሚደርሰው መንገድ ሲሆን፣ ከመገናኛ ሲኤምሲ የተዘረጋውን ልማት ጨምሮ ሌሎቹ መስመሮች በተለያዩ ጊዜያት ተመርቀው ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል። በመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት 32 የውሃ ፏፏቴዎች እንዲሁም 70 የሕዝብ መናፈሻ ስፍራዎች እና የፈጣን ምግብ አገልግሎት መሸጫ ቦታዎች ተገንብተዋል።

በምዕራፍ ሁለት የሚከናወኑ የኮሪደር ልማት ሥራዎች ላይ የተደረገው ይህ ጥናት በከተማዋ የፕላን እና ልማት ቢሮ የተዘጋጀ ነው። በአጠቃላይ 43 ኪሎ ሜትር ርዝመት የሚኖረው የምዕራፍ ሁለት የኮሪደር ልማት፤ ቦሌ፣ ለሚ ኩራ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞችን እንደሚያካትት የጥናት ሰነዱ ያሳያል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ግንባታ በአምስት መስመሮች ላይ የሚከናወን ነው። ከእነዚህ መስመሮች ውስጥ ከፍተኛ ዝርመት ያለው "ከአንበሳ ጋራዥ - መብራት ኃይል - ጎሮ - ኮዬ አደባባይ" የሚደርሰው መንገድ ነው። ይህ መስመር 14.8 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ነው።

"ከቦሌ ካርጎ - ቡልቡላ - ኮዬ አደባባይ" የሚደርሰው ሁለተኛው ረጅም መስመር ደግሞ 12.8 ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው። በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ውስጥ የተካተተው ሌላኛው መስመር "ከቦሌ ድልድይ" ተነስቶ "በቦሌ ሆምስ - በአየር መንገድ ቪአይፒ መግቢያ" አድርጎ መዳረሻው "ጎሮ" አካባቢ ነው።"ከጎሮ አደባባይ" የሚነሳው አራተኛው መስመር አምስት ኪሎ ሜትር ርዝመት እንደሚኖረው በጥናት ሰነዱ ላይ ሰፍሯል።

ይህ መስመር "ከጎሮ አደባባይ - በሰባ ሁለት አካባቢ - ሰሚት ለስላሳ ፋብሪካ አካባቢ - ፍየል ቤት - ሲ ኤም ሲ አደባባይ" አካባቢዎችን ይሸፍናል።"ከፍየል ቤት - ፊጋ - ሰሃሊተ ምህረት አደባባይ - ጃክሮስ" የሚደርሰው አምስተኛው መስመር ደግሞ 5.9 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ነው።

በከተማዋ የአስተዳደር ወሰን ማብቂያ አካባቢ የሚገኙ አካባቢዎችን ያካተተው ሁለተኛው ምዕራፍ ግንባታ፤ "በትግበራ ላይ ከሚገኙ የሸገር [ከተማ] የልማት ኮሪደሮች ጋር በማስተሳሰር የሚከናወን" እንደሆነ የጥናት ሰነዱ ያመለክታል። ወደ ኅዳር ሲታጠን ሲመለስ፤

«በኢትዮጵያ የኅዳር በሽታ የሚታወቀው የአንደኛውን የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ተከትሎ የተከሰተውና በመላው ዓለም ለ200 ሚሊዮን ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው 'እስፓኒሽ ፍሉ ' ነው:: ወረርሽኙ በ24 ሳምንታት የቀሰፈው ሕይወት፤ ኤች አይ ቪ ኤድስ በ24 ዓመታት ከቀሰፈው በአያሌው ይበልጣል:: ወረርሽኙ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ብዙ ሰው የጨረሰው በኅዳር ወር ስለነበር 'የኅዳር በሽታ' እየተባለ ይጠራ ነበር:: ወረርሽኙ ወደ ወለጋ በመዛመቱ የንፋስ በሽታ 'ዱኩባ ቂሌንሳ' የሚል ስም ወቶለት ነበር::

ይህ መቅሰፍት በሀገራችን በ1911 ዓ.ም ወርዶ ብዙ ሰው ጨርሷል:: ወረርሽኙ በጉንፋን በሳል ይጀምርና ትኩሳት፣ ማስለቀስ፣ ነስር፣ ተቅማጥና ተውከት ከማስከተሉ ባሻገር አእምሮም ያስት ነበር:: ከዚያም በሦስት በአራት ቀን ይገድላል:: የቤተሰቡ አባላት በሙሉ አልጋ ላይ ይውሉ ስለነበር አስታማሚ ስለሚጠፋ በርሀብና በውሃ ጥም ብዙ ሰው ይጎዳ ነበር:: ከአራት ቀን ያለፈ ሕመምተኛ ግን ይድናል:: አፍላው በሽታ ከኅዳር 7 እስከ 20፣ 1911 ዓ.ም ነበር:: በየቀኑም ሁለት ሦስት መቶ ከዚህ በላይም ይሞት ነበር:: በአንድ መቃብር ሁለት ሦስት ሬሳ እስከ መቅበር ተደረሰ::

በዚያ ሰሞን መቃብር የሚቆፍርና ሬሳ ተሸክሞ ወደቀብር የሚወስድ ሰው ማግኘት ችግር ነበር:: ባል የሚስቱን፤ አባት የልጁን ሬሳ እየተሸከመ ቀበረ:: መቃብር ይቆፍርና ቤቱ ሄዶ ሬሳ ይዞ ሲመለስ ሌላው ቀብሮበት ያገኘዋል:: ቤተሰብ በሙሉ የታመመባቸው በየቤታቸው እየሞቱ አውሬ በላቸው:: በበሽታው ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪና ልዕልት ወ/ሮ መነን በጠና ታመው ነበር፤ ንግስት ዘውዲቱም አልጠናባቸውም እንጅ ታመው ነበር:: ከመኳንንት ከንቲባ ወሰኔ ዘአማኒኤል፤ ከካህናትም ሐዲስ አስተማሪው አለቃ ተገኘ ሞቱ:: አለቃ የመምህር ወ/ጊዮርጊስ ደቀ መዝሙር ነበሩ::

በዚያ ወራት በአዲስ አበባ የነበረው ጭንቀት በስፍራው ተገኝቼ ተመልክቼዋለሁ:: የኔታ ወልደ ጊዮርጊስ በሰፈራቸው በጉለሌ ክፍል በየቤቱ እየዞሩ ለበሽተኞችና ለገመምተኞች እንጀራና ውሃ ሲያድሉ ሰነበቱ:: በእግዚአብሔር ቸርነት ከበሽታው አምልጠን ነበርና እኔንና ጎጃሜ ኃይለ ማርያምን ውሃ በገንቦ እያሸከሙ እሳቸው ቁራሽ እንጀራ ይዘው ይሄዱና ከቤቱ ደጃፍ ሲደርሱ እኛን ውጪ አስቀርተው ውሃውንና ቁራሹን ይዘው ይገቡ ነበር:: እኛን ማስቀረታቸው በሽታ እንዳይዘን ስላሰቡልን ነው::

በሌላ ስፍራም የዚህን ዓይነት ትሩፋት የሰሩ መንፈሳውያን ሰዎች ነበሩ:: ለምሳሌ ሙሴ ሴደርኩይስት የተባሉ ስዊድናዊ ሚስዮናዊ አስተማሪ በየሰፈሩ እየዞሩ ለበሽተኞች እህልና ውሃ መድኃኒት በመስጠት ትሩፋት መስራታቸውን ሰምቻለሁ:: እኒህ ሽማግሌ ከጥቂት ቀናት በኋላ በዚሁ በሽታ ታመሙና ሞተው ጉለሌ ተቀብረዋል::

የኅዳር በሽታ (ግሪፕ) በአዲስ አበባ ብቻ አልተወሰነም:: ወደ ባላገር ተላልፎ ብዙ ሰው ፈጅቷል:: ሆኖም በባላገር የአዲስ አበባን ያህል አልጠነከረም ይባላል:: በዚህ በሽታ በመላ ኢትዮጵያ የሞተው የሕዝብ ቁጥር እስከ 40 ሺህ ድረስ መገመቱንም አስታውሳለሁ:: በተለይ ኅዳር 12፣ የሚካኤል ዕለት ብዙ ሰው ሞተ:: ስለሆነም ወረርሽኙ እስከዛሬ በየዓመቱ የኅዳር ሚካኤል ዕለት በየሰፈሩ ቆሻሻ ሰብስቦ በማቃጠል 'ኅዳር ሲታጠን ' በሚል ይዘከራል:: ...» በማለት ' የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ' ደራሲ መርስኤ ኅዘን ወ/ቂርቆስ ይነግሩናል::

በነገራችን ላይ እነ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴ እና ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ያለስስት የመሰከሩለትን ይህን ድንቅ መፅሐፍ ካላነበባችሁት እንድታነቡት እና ከመፅሐፍት መደርደሪያችሁ እንድትጨምሩት በታላቅ ትህትና እጋብዛለሁ::

ሻሎም !

አሜን።

በዚያ ሰሞን መቃብር የሚቆፍርና ሬሳ ተሸክሞ ወደቀብር የሚወስድ ሰው ማግኘት ችግር ነበር:: ባል የሚስቱን፤ አባት የልጁን ሬሳ እየተሸከመ ቀበረ:: መቃብር ይቆፍርና ቤቱ ሄዶ ሬሳ ይዞ ሲመለስ ሌላው ቀብሮበት ያገኘዋል:: ቤተሰብ በሙሉ የታመመባቸው በየቤታቸው እየሞቱ አውሬ በላቸው:: በበሽታው ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪና ልዕልት ወ/ሮ መነን በጠና ታመው ነበር፤ ንግስት ዘውዲቱም አልጠናባቸውም እንጅ ታመው ነበር:: ከመኳንንት ከንቲባ ወሰኔ ዘአማኒኤል፤ ከካህናትም ሐዲስ አስተማሪው አለቃ ተገኘ ሞቱ:: አለቃ የመምህር ወ/ ጊዮርጊስ ደቀ መዝሙር ነበሩ

# ዓለም አቀፍ

## ፑቲን ሩሲያ በውጊያው አዲስ ሚሳኤል መሞከሯን እንደምትቀጥል ጠቆሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ሀገራቸው አዳዲስ ሚሳኤል መሞከር እንደምትቀጥል ተናግረዋል። ፑቲን ዩክሬንን ለማጥቃት ‘አዲስ ሚሳኤል’ መጠቀማቸውን እንደሚቀጥሉ አረጋግጠው የዩክሬን አጋሮች የሆኑትን ምዕራባውያንን በጽኑ አስጠንቅቀዋል።

ሩሲያ የመካከለኛ ርቀት ሚሳይል ባስወነጨፈች ማግስት ፑቲን ባሰሙት ንግግር ሩሲያ ኦሬሽንክ የተባለውን አዲስ ሚሳኤል ያስወነጨፈችው ዩክሬን የአሜሪካ ባለስቲክ ሚሳይልን እና የእንግሊዝን ክሩዝ ሚሳይል ወደ ሩሲያ በማስወንጨፏ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል። ፕሬዚዳንት ፑቲን አክለውም፤ ሩሲያ በጦርነቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ ያዋለችው ኦሬሽንክ ሚሳኤል ስኬታማ ነው ያሉ ሲሆን ሁኔታውን እና



የደህንነት ስጋቱን እየታየ ሙከራዎቹ ይቀጥላሉ ሲሉ ተደምጠዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ሩሲያ እነዚህ አይነት መሳሪያዎች ክምችት አላት። መሳሪያዎቻቸው የሩሲያን ተቋማት እንዲመቱ በሚፈቅዱት ሀገራት ወታደራዊ ተቋማትን ለመምታት እያጤነች ነው። አሜሪካ እና ብሪታኒያ ዩክሬን የረጅም ርቀት መሳሪያዎቻቸውን ተጠቅማ ሩሲያን እንድታጠቃ መፍቀዳቸውን ተከትሎ ጦርነቱ ወደ ዓለም አቀፍ ግጭት እየተሸጋገረ መምጣቱን አብራርተዋል።

የአሜሪካና የብሪታኒያ ሚሳዔሎቻቸው ሩሲያን ለማጥቃት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ተከትሎ ሞስኮ አዲስ የመካከለኛ ርቀት ሃይፐርሶኒክ ባለስቲክ ሚሳኤል በዩክሬን ወታደራዊ ተቋም ላይ በመተኮስ የአጸፈ ምላሽ ሰጥታለችም ነው ያሉት። የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዘለንስኪ በበኩላቸው ኬቭ አዳዲስ አደጋዎችን መከለል እና ይህን መሳሪያ ለማክሸፍ የሚያስችል የአየር ሲስተም እያለማች መሆኑን ገልጸዋል። ኬቭ አዳዲስ አደጋዎችን ለመከለል ከምዕራባውያን አጋሮቿ ጋር እየሰራች መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ፤ አዲሱን የሩሲያ ሚሳኤል ተኩስ ግጭት አባባሽ መሆኑን ገልጸው፤ መከላከያ ሚኒስትራቸው እሳቸውን ወክለው ከምዕራባውያን አጋሮች በአየር መከላከያ ስርአት ዙሪያ እየተወያዩ መሆኑን ጠቁመዋል። ሩሲያ ይህን ብትልም የአሜሪካ ባለስልጣናት ግን ሩሲያ የተጠቀመችው ሚሳይል ለሙከራ ብቻ ነው፤ ያላት ክምችትም የተወሰነ ነው።

ኢንተርሚዲየት ሚሳይል ከ3000-3500 ኪሎ ሜትር ርቀት መምዘግዘግ የሚችል ሲሆን የትኛውንም የአውሮፓ ወይም የአሜሪካ ቦታ መምታት ይችላሉ ተብሏል። በተጨማሪም የደህንነት ባለሙያዎች እንደሚሉት ኦሬሽንክ ሚሳኤል በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታዎችን መምታት እና በርካታ ተተኳሾችን መያዝ የሚችል መሆኑ የተለየ ያደርገዋል፤ ከአህጉር አቋራጭ ባለስቲክ ሚሳይል ጋር የመመሳሰል ባህሪም እንዳለው አል ዓይን ዘግቧል።

## 500 ሺህ የሚጠጉ ተፈናቃዮች በሚገኙበት የሱዳን መጠለያ ጣቢያ ከወራት በኋላ ርዳታ ደረሰ

500 ሺህ የሚጠጉ ተፈናቃዮችን ያስጠለለው የሱዳን ስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ከወራት በኋላ የመጀመሪያው ሰብዓዊ እርዳታ መድረሱ ተገለጸ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጭነት መኪናዎች በሱዳን ለ18 ወራት በዘለቀው የእርስ በርስ ጦርነት ቀያቸውን ለቅቀው የተጠለሉበት ዛምዛም ስደተኞች ካምፕ ሕዳር 13 ቀን 2017 ዓ.ም ደርሰዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ምግብ ፕሮግራም (ደብሊውኤፍፒ) በአቅራቢያው በምትገኘው የዳርፉር ከተማ ኤል ፋሸር በተካሄደው ከባድ ጦርነት እንዲሁም ዝናባማ ወቅት ተከትሎ “ለመሻገር ፈታኝ በሆኑ” መንገዶች የተነሳ የምግብ አቅርቦቱ ለወራት ተቋርጦ ቆይቷል ብሏል።

በሱዳን ጦር ሠራዊቱ እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይል (RSF) መካከል ባለው የሥልጣን ይገባኛል ሽኩቻ የተነሳ በዓለም ትልቁ የሰብዓዊ ቀውስ ተፈጥሯል። ይህ የሱዳን ጦርነት 10 ሚሊዮን ሰዎች ከቤታቸው እንዲፈናቀሉ ሲያደርግ ማሕበረሰቡን ለረሃብ አጋልጧል። በዛምዛም የሚገኙ ተፈናቃዮች ቁጥር ከባለፈው ዓመት ሚያዝያ ወር ጀምሮ፣ የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች አል- ፋሽርን ከአገሪቱ መከላከያ ኃይል ለማስለቀቅ ያደረጉትን ከባድ ውጊያ ተከትሎ፣ ቁጥራቸው በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል ተብሏል።

አል-ፋሽር በምዕራብ ዳርፉር ግዛት በአገሪቱ ወታደር ቁጥጥር ስር ያለች ብቸኛ ከተማ ነች። በነሐሴ ወር፣ ገለልተኛ የሆነ የምግብ ዋስትና ባለሙያዎች ጦርነቱ ዛምዛምን ወደ ረሃብ እንደገፋ ተናግረው ነበር። በረሃብ የተጠቃን አካባቢ ለመመደብ የተቀመጡት መስፈርቶች ቢያንስ 20 በመቶ የሚሆኑ አባወራዎች ለከፋ የምግብ እጦት የተጋለጡ መሆናቸውን፣ 30 በመቶ ሕጻናት በከፍተኛ የምግብ እጥረት የተጎዱ እና ከ10 ሺህ ሰዎች ውስጥ ሁለቱ ሰዎች በየቀኑ በረሃብ ወይም በምግብ እጦት አልያም በበሽታ ይሞታሉ ይላል።



ወደ ዛምዛም የምግብ እርዳታ ጭነው የተንቀሳቀሱ መኪኖች የዓለም የምግብ ድርጅት “ለችግር በከፍተኛ የተጋለጡ እና ከሌላው ተነጥለው ግጭት ያለባቸው አካባቢዎችን ” ለመድረስ የሚያደርገው ጥረት አካል ነው ሲል ገልጿል። በአጠቃላይ ከ700 በላይ የጭነት መኪኖች አንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን ሰዎችን ከአንድ ወር በላይ ለመመገብ የሚያስችል በቂ እርዳታ ይዘው መላካቸውን መግለጫው አመልክቷል። የተወሰኑ የምግብ እርዳታ የጫኑ መኪኖች ወደ ደቡብ ኮርዶፋን ግዛት እያመሩ መሆኑም ታውቋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





# የከሸፈው ታላቅ የእግር ኳስ አብዮት!

**ቦጋለ አበበ**

በአንድ ወቅት በቻይና የተነሳው የእግር ኳስ አብዮት የዓለምን ትኩረት ስቦ ነበር። የሩቅ ምስራቋ አገር ቻይና ሱፐር ሊጓን የዓለም ከዋክብት ተጫዋቾች መገኛና የድንቅ የእግር ኳስ መናኸሪያ የመሆን ውጥን ይዛ ነበር የተነሳችው። አገሪቷ ይህን ውጥኗን እውን ለማድረግ ከስምንት መቶ ቢሊየን ዶላር በላይ ለስፖርቱ ኢንደስትሪ አፍስሳለች።

እግር ኳስን በእጅጉ እንደሚወዱ የሚነገርላቸው የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ዢ ጂፒንግ ድጋፍ፤ ቻይና የዓለማችን ታላላቅ ከዋክብትን በገንዘብ በማማለል ሊጓን የማጠናከር ስራን "ሀ " ብላ ጀመረች። የዓለማችን ስመጥር ከዋክብት በቻይና ክለቦች ከፍተኛ የገንዘብ ክፍያ ወደ ሱፐር ሊጓ መትመም ጀመሩ። ከነዚህም መካከል ብራዚላዊው ኦስካር፣ አርጀንቲናዊው ካርሎስ ቴቬዝ እና ቤልጂዬማዊው አክስል ቪትዝል ይገኙበታል። የነዚህ ተጫዋቾች ሊጉን መቀላቀል ለሌሎች ታላላቅ ተጫዋቾች መምጣት ምክንያት ሲሆኑ ጊዜ አልወሰደም። በ2016 በቻይና የፈነዳው ይህ የእግር ኳስ አብዮት በአውሮፓ እግር ኳስ ላይም ትልቅ ስጋት እስከመደቀን ደርሶም ነበር።

ጣሊያናዊው የቀድሞው የቼልሲ አሰልጣኝ አንቶኒዮ ኮንቴ በወቅቱ በሰጡት አስተያየት፤ "የቻይና ገበያ ለቼልሲ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ክለቦች በሙሉ አደጋ ነው " እስከማለት ደርሰው ነበር። "ቻይና ሁሉንም የአውሮፓ ሊግ ወደ ቻይና ለማዘዋወር የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ያላት ትመስላለች " ሲሉም ታሪካዊው የአርሰናል አሰልጣኝ አርሰን ቬንገር በወቅቱ ስጋታቸውን ገልፀው ነበር።

ጥቂት የማይባሉ ኮከቦች በቻይና ሱፐር ሊግ ወደ ሚገኙት ሲኤስኤል ቻንግቹን፣ ሄቤይ፣ ቤጂንግ ጉዋን፣



ጂያንግሱ ሰኒንግ ክለቦች መትመም ጀመሩ። ሱፐር ሊጉ በርካታ ገንዘብ ማውጣት ሲጀምር አገሪቱን ወደ እግር ኳስ ልዕለ ኃያልነት የመቀየር ፍላጎታቸው እውን መሆን የጀመረ መሰለ። የሱፐር ሊጉ እንቅስቃሴ ጠንካራ ወደ ሚባል ደረጃ መድረስ ቢችልም፤ የእግር ኳስ አብዮቱ የታሰበውን ግብ መምታት እንደማይችል ምልክቶች መታየት ጀመሩ። አንዳንድ ክለቦች በዕዳ ውስጥ የመዘፈቃቸው ዜና ይሰማ ጀመር።

እአአ በ2017 የቻይና ስፖርት ሚኒስቴር የሊጉን ወጪን በተመለከተ ጥያቄ ማንሳት ጀመረ። ወጪዎችን ለመግታት እና "ምክንያታዊ ያልሆነ ኢንቨስትመንት" ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ጀመረ። ክለቦች "ገንዘብ ያባክናሉ" እና ለውጭ ተጫዋቾች "ከልክ በላይ ደመወዝ" ይከፍላሉ ሲል ወደ መክሰስ ተሻገረ። በዚህ ፈታኝ መንገድ ውስጥም ቢሆን በ2019 ሱፐር ሊጉ በጣም ትልቅ ደረጃ ላይ ደረሰ።

በብዙ የተጠበቀው የቻይና እግር ኳስ አብዮት አስር ዓመት ሳይሞላው ጉዞው በተቃራኒው አቅጣጫ ሆኖ ተስፋው መፈረካከስ ጀመረ። የቻይና ክለቦች ተጫዋቾችን ወደ ቻይና ሱፐር ሊግ ለመሳብ በሚል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ቢከፍሉም፤ ትርፋማ መሆን አልቻሉም። ቻይና የጀመረችው መንገድ የተሳሳተ መሆኑን የተረዳችው ግን ዘግይታ ነበር።

የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ዢ ጂፒንግ በገንዘብ ኃይል አገራቸውን ወደ እግር ኳስ ማዕከልነት የመቀየር ፍላጎታቸው የሚሳካ አለመሆኑን ለመገንዘብ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል። እግር ኳስን በገንዘብ አቅም ማላቅ እንችላለን ከሚለው ቅዥት የነቁት ብዙ ኪሳራ ከረደሰባቸው በኋላ ነበር። ፕሬዚዳንቱ አርፍደውም ቢሆን የእግር ኳስ ትዕይንቱ ልጓም እንዲበጅለት ቀጭን ትዛዝ ሰጡ። የቻይና እግር ኳስ ማህበርም ተከተላቸው። ክለቦቻቸው ዕዳ ውስጥ መዘፈቃቸውን ተከትሎ የቻይና እግር ኳስ ማኅበር በ2020 የደመወዝ ጣራ አስቀመጠ።

የባሕር ማዶ ተጫዋቾች በሳምንት የሚያገኙት ከፍተኛ ደመወዝ 52 ሺህ እንዲሆን ሲል ወሰነ። ይህም ቀደም ሲል ለከዋክብት ተጫዋቾች ከቀረቡት ኮንትራቶች እጅግ በጣም ያነሰ ነው።

ከ2021 በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ የፋይናንስ ችግሮች እየተባባሱ መጡ። በዚሁ ዓመት በሱፐር ሊጉ የሚጫወተው ጂያንግሱ ሱኒንግ ክለብ የዓለማችን ውዱ ተጫዋች የነበረውን የሪያል ማድሪዱ ጋሬዝ ቤልን ወደ ጂያንግሱ ሰኒንግ ለማዘዋወር አቀደ። የሦስት ዓመት ኮንትራት በመስጠት በሳምንት አንድ ሚሊዮን ፓውንድ ለመክፈል ነበር ዕቅዱ። ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ግን ጂያንግሱ ሱኒንግ በደረሰበት የፋይናንስ መቃወስ ሥራ አቆመ። የቡድኑን አውቶብስ ለመሸጥ ጨረታ እስከማውጣትም ደረሰ።

እንደ ጂያንግ ሱኒንግ ክለብ ሁሉ አብዛኛዎቹ ክለቦች ለተጫዋቾቻቸው ደመወዝ ለመክፈል እጅ እስኪያጥራቸው የደረሰ የከፋ ችግር ውስጥ ተዘፈቁ። በዚህ ምክንያት በገንዘብ የማለሉት ውድ ተጫዋቾች አገሪቱን ጥለው መውጣት ጀመሩ። በብዙ የተጠበቀው የቻይና እግር ኳስ አብዮት አስር ዓመት ሳይሞላው ጉዞው በተቃራኒው አቅጣጫ ሆኖ ከሸፈ። የፕሬዚዳንት ዢ ቻይና ከእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ የገዘፈ የሊግ ውድድር ባለቤት የመሆን ሕልም ዛሬ ቅዥት ሆኗል። የዓለም መገናኛ ብዙሃን ትኩረት የነበረው የቻይና ሱፐር ሊግም ዛሬ ላይ አስታዋሽ የለውም።